አበበ ገላው በሬገን ማዕከል ያስደነገጣቸው ሰሞን "በድንጋጤ አንገታቸውን ደፍተው ነበር" የሚለውን ለማስተባበል ወይንም "ድንጋጤ ሲያልፍም አይነካቸው" ለማለት ታንክ ላይ ተቀምጠው መጽሐፍ እንደሚያነቡ ተርከውልናል:: ታንኩ በውጊያ ወቅት እንደተዋጊ በሬ መድፉን ወደ ጠላት አቅጣጫ ደግኖ እሳት እየተፋ ከላዩ ላይ ተቀምጠው አንብበው ከሆነ ድፍረት ሣይሆን ደመነፍስነት ነው:: ወይንም ደግሞ ባንዳንድ ፊልሞች እንደምናያቸው መናፍስት ናቸው ማለት ነው:: በሰላም ጊዜ ታንኩ እንዳይግል ወይንም በፀሐይ ጨረር አንፀባርቆ ለጠላት እይታ እንዳይጋለጥ ከዛፍ ሥር ቁሞ ከዚያ ላይ ተቀምጠው አንብበው ከሆነ ጊዜያቸውን በዋዛ ፈዛዛ ባለማሣለፋቸው ሊደነቁ ይገባቸዋል:: አንባቢነታቸውም የኋላ ሥንቅ እንደሆናቸው መገመቱ አይከብድም:: ከዚህ ውጭ ግን መጽሐፍ አንባቢ መሆን የፍርሃትና የድፍረት ማነፃፀሪያ ሊሆን አይችልም:: ለመሆኑ ፋኖ ታንክና መድፍ አለው እንዴ? ጠይቁ ::

ከጓደኞቻቸው ጋር ቁራሽ ፍለጋ ካንድ መንደር ውስጥ ገብተው በንባብ ተጠምደው እማወራዋን ሊጥ አላስቦካ ማለታቸውንም <<መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት>> የተባለው ስብስብ ሥራ አስነብቦናል:: በዚህ አጋጣሚ አንድ ተረት መሠል ቁምነገር ትዝ አለኝ::

አንድ አዳኝ አደን ውሎ ሣይቀናው ይመለሳል:: ጓደኛው ከመንገድ ያገኘውና "የዛሬው ውሎህ እንዴት ነው? አልቀናህም?" ሲል ይጠይቀዋል::

"አንዲት ድኩላ አግኝቼ እግሯንና ጆሮዋን አነባብሬ ባንድ ጥይት መትቼ ገደልኳት" ይለዋል::

"ይህ እንዴት ሊሆንይችላል?"በማለት ሲጠይቀው:-

"በኋላ እግሮቿ ጆሮዋን ስታክ ጠነበዝኳት" ሲለው:-

"አሁን እውነት መሰለልህ" አለው ይባላል:: ያቶ መለስ ፕሮፓጋንዲስቶች አቶ መለስን ልክ ሕዝብ እንደማያውቃቸው የተለየ ፍጡርና ለኢትዮጵያ መድሕን ሆነው የተፈጠሩ በማስመሰል ሲተርኩልን ትንሽ እንኳን ሕዝብ ምን ይለናል ብለው አለ መጨነቃቸው በራሱ ወደፊት ምርምር የሚያሻው ጉዳይ ነው:: የሳቸውን ገድለታሪክ ለታሪክ አቆይቶ ወደ ሥራ ቢገባ እንዴት የተሻለና ያማረ በሆነ ነበር:: ግን ማን ልበሙሉነት ይሰማው? ሁሉም ባለሥልጣናት በሣቸው ሙት መንፈስ በፍርሃት ተዘፍቀው እየበረገጉ ሥራ ትተው ሥራ እያሥተው ናቸው:: ለማንኛውም የሚሻለው ልናስብ የምንችለውን ያህል ብናስብ ነው::





# ያሰብ የባሕር በር

በቅድሚያ የባሕር በር ስንል ምን ማለታችን ነው? "በር" በጥሬ ፍችው መግቢያና መውጫ ማለት ነው:: "የባሕር በር" ስንል ደግሞ ባሕርን ወይንም እውቅያኖስን አቋርጠን ወደ የብስ የምንዘልቅበት ወይንም ከየብስ ወደ ባሕር የምንገባበት ማለታችን ነው::

"ያሰብ የባሕር በር" ስንልስ ምን ማለታችን ነው? ይህንን በተመለከተ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም የሚከተለውን ይላሉ:-

". . .የባሕር በር መብት ስንል ምን ማለታችን ነው?" በማለት ይጠይቁና "በተለምዶ አነጋገር <አሠብ>ሲባል ብዙዎች ወደቡን ብቻ የሚሸፍን አድርገው ይወስዱታል:: በዚህ ጽሑፍ ‹አሰብ› ስንል ግን ከወደቡ ዓለም ዓቀፍ የባሕር በር ሕግ እንደ ሚደነግገው 12 ኖርቲካል ማይልስ ወደ ባሕር ዘልቆ (ገብቶ) ላይ ታቹን፣ የባሕሩንና የመሬቱን አካባቢ የሚሸፍነውን ሲሆን፤ ባፄ ኃይለሥላሴ ‹ያሰብ አውራጃ› በደርግ ጊዜ ‹ያሰብ ራስ ገዝ› ይባል የነበረውን ውሃውንና መሬቱን፣ ደሴቶቹን ሁሉ ያጠቃልላል› *(አሠብ የማናት ገጽ 170 ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም)*

እንግዲህ ስለ አሠብ አውራጃና ራስ ገዝ አሥተዳደር ይህን ያህል ካልን ስለ ወደቡስ ምን እንላለን? ወደብ በጥሬ ፍችው የሸቀጦች ማራገፊያ፣ መጫኛ፣ ማቆያና ማከማቻ ልንለው እንችላለን:: ወደብ ላንዲት አገር ኢኮኖሚ ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: ወደብ ያላት አገር ምንም ያህል ትንሽና የባሕር ዳርቻ አገር ብትሆን እንኳን ወደቧን ወደብ ለሌላቸው አገሮች በማከራየት ሕዝቦቿን መግባ መኖር አይሳናትም:: ባንፃሩ ወደብ የሌላት አገር ምንም ያህል በቆዳ ስፋቷና በሕዝቧ ብዛትና በኢኮኖሚዋ የበረታች ብትሆንም የራሷን ጥሬ እቃዎች የማስወጫና የምትፈልጋቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በፈለገችበት ጊዜ ማስገባት ስለማትችል ለወደብ ኪራይ የምትከፍለው ክፍያ ከምታመርተው እጥፍ ስለሚሆን የትልቅ ድኩማን መሆኗ የግድ ነው:: ኢትዮጵያንና ጅቡቲን በማነፃፀር ሀቁን መረዳት ይቻላል:: ዛሬ ጂቡቲ የትንሽ ትልቅ ስትሆን ኢትዮጵያ ግን የትልቅ ትንሽ ሆና የሷ ገባር ሆናለች:: ያውም ተለማምጠን፣ መብራት ዘርግተን እሷ 24 ሰዓት ስትንቆጠቆጥ እኛ ግን መብራት በፈረቃ እንደ ጨረቃ::

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ከብዙ አቅጣጫ ቃኝተውና ፈትሸው ሀቁን እንዳስቀመጡት ከሆነ ባሁኑ ወቅት ለጂቡቲ በቀን ለወደብ አገልግሎት የምንከፍለው ኪራይ ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ነው፡፡ ወደኛ ምንዛሬ ስንመልሰው ከሃያ ሚሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ በዚህ ስሌት ስንሄድ በወርና ባመት የምንከፍለው ከፍያ የትየ ሌሌ ነው፡፡ ባጭሩ ሠርተን ለጂቡቲ ነው የምናስረክበው ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያን የባሕር በር ለማሣጣትና ወደብ አልባ ለማድረግ የትግራይ ወጣቶች ገና ከማለዳው ጀምረው የተጠናወታቸው መሆኑን ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም እንዲህ ሲሉ ቁጭታቸውን ይገልፃሉ፡-

"የሕወሓት መሪዎች ኤርትራን አስገንጥለው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ እንድትሆን የሠረጸባቸው ምኞት ገና በተማሪነታቸው ‹ማህበረ ገሥገስቲ ብሔረ ትግራይ› የተባለ የተማሪዎች ማህበር ካቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ነበር..." *(እንደ ላይኛው ገጽ 20)*

በነገራችን ላይ ይህ የዶ/ር ያዕቆብ "አሥብ የማናት?" የሚለው መጽሐፍ ከሕግ፣ ከሉዓላዊነትና ከታሪክ አንፃር እያጣቀሱ የሕወሓትን ደባ መነሻና የመዳረሻ ግቡን፣ የግብፆችንም ሴራ ያጋለጡበት በመሆኑ ያገሩ ውርደትና ሞት የሚቆጨው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ገዝቶ ሊያነበው የሚገባ መጽሐፍ ነው፡፡

ለመሆኑ የሕወሓት ከፍተኛ ያመራር አባላት ይህን ያህል ለኢትዮጵያ ጠላት የሆኑትና የባሕር በሯን ዘግተው ጉረሮዋን ያነቋት ለምንድን ነው? ጭካኔቸውስ ከምን የመነጨ ነው? ብለን ብንጠይቅ ለዚህ ዶ/ር ያዕቆብ የሚከተለውን መልስ ይሰጡናል፡-

"‹ዛሬ ኢትዮጵያ የባሕር በር አያስፈልጋትም በጎረቤት አገራት ወደቦች ትጠቀማለች› የሚሉን የሕወሓት መሪዎች ባንድ በኩል ኤርትራን ለማስገንጠል ሲጥሩ በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያ <ታላቋ ትግራይን ፈጥረው> የትግራይን ሪፐብሊክን አቋቁመው የቀይ ባሕር ሰላጤን ከታላቋ ትግራይ ጋር ለመቀላቀል የወጠኑት ነበር" *(ዶ/ር ያዕቆብ እንደላይኛው ገጽ 53)*

እንግዲህ ሀቁ ይኸ ነው፡፡ የሕወሓት አመራሮች 21 ዓመታት ተጉዘው እንኳን "ኢሕአዴግ" ብለው የጠፈጠፉትን ለይመስልም ቢሆን ከግንባርነት ወደ ውህደት አሸጋግረው ኢትዮጵያዊ ካባ ማልበስ አልቻሉም፡፡ ይህም እንዳደፈጡ ለመሆናቸው አንዱ ማረጋገጫ ነው፡፡





ይህንን ሀቅ በተመለከተ ማስታወቂያ ሚንስቴር በ1995 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳና ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ" ብሎ በሣተመው መጽሐፍ የሚከተለውን ይለናል፡-

"ጎረቤቶቻችን ባለወደብ ሲሆኑ እኛ ግን ወደብ አልባ በመሆናችን በኢኮኖሚ እየለማን ስንሄድ በዚያው መጠን ብቃት ያለው አገልግሎት የሚያስፈልገው መሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡" *(ገጽ 63)*

ኢትዮጵያን ጉረሮዋን ያነቃትና ያሣናቃት ድርጅት እንኳን ይህንን ያፈጠጠ ሀቅ መሸሸግ አልሆነለትም፡፡ <እየለማን በሄድን መጠን ሰፊ የወደብ አገልግሎት> እንደሚያስፈልገን የኢሕአዴግ መንግሥት ተገንዝቦታል፡፡ ጥያቄው ታዲያ ምን ይደረግ ነው? ማንስ ነው ወደብ ያሣጣን? እያደግንና እየለማን በሄድን መጠን ወደብ ፍለጋ ማረፊያ ዛፍ እንዳጣ አሞራ መክነፍ ነው? ጠይቁ፡፡

ይኸው ማስታወቂያ ሚንስቴር ያሳተመው መጽሐፍ አያይዞም እንዲህ ይለናል፡-

". . .አደጋው ሁሉም ተባብረው ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት የከለከሉ እንደሆነ ነው . . ." *(እንደላይኛው ገጽ 64)* <ሁሉም ተባብረው የከለከሉን እንደሆነ> የተባሉት ሞምባሳ፣ ፓርት ሱዳን፣ በርበራን . . . ለማለት ነው፡፡

የኢሕአዴግ መንግሥት የወደብን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ከገለፁልን በኋላ መልሶ ደግሞ ወደብ ማስነጠቁን ወይንም ፈቅዶ መልቀቁን ሕጋዊነት ለማላበስ ሲል በተጠቀሰው መጽሐፍ እንዲህ ይለናል፡-

". . .ባንድ በኩል በተለይም ከወደብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የኤርትራ ነፃነት ያልተዋጠላቸው ወገኖች አሉ" በማለት ለመኮነን ይሞክራል፡፡ *(እንደላይኛው ገጽ 69)*

ይኸው መጽሐፍ ከጂቡቲ ጋርም ዘላቂ ወዳጅነት እንደማይኖረን እንዲህ ይለናል "ባሁኑ ወቅት ጎልቶ የሚታይ ችግር ባይኖርም በጂቡቲ በኩል አለመግባባት ተፈጥሮ የወደብ አጠቃቀምን ሊያሰናክል ይችላል፡፡ የተለያዩ የውጭ ጣልቃ ገቦች (ዐረቦችን ለማለት ነው) በጂቡቲ ላይ ተፅዕኖ አሣርፈው አጠቃቀሙን እንዳያሰናክሉት በሩን ሊከፍትላቸው ይችላል. . ." በማለት ኢሕአዴግ ሥጋቱን ሣይደብቅ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ ጂቡቲ እንዳታኮርፍና

ለውጭ ኃይሎች ቀዳዳ እንዳትከፍት በዚሁ ማስታወቂያ ሚንስቴር ባሣተመው መጽሐፍ ማባባል እንዳለብን እንዲህ ይለናል፡-

"የኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኢትዮጵያ በርካሽ ዋጋ ማግኘት ሲችሉ ነው..." ይለናል፡፡ ዛሬ ጅቡቲ በርካሽም ቢሆን ለተጠቀመችበት የመብራት አገልግሎት ምን ያህል እንደምትከፍለን አናውቅም፡፡ እኛ ግን ለወደብ አገልግሎት በቀን በትንሹ ሦስት ሚሊዮን ዶላር እንከፍላለን፡፡

እንግዲህ የኤሌክትሪክ መብራታችን ለጊዜው ዋስ ጠበቃችን ሆኗል፡፡ ግን ደግሞ መብራቱ ድንገት በመብረቅ ወይንም በሌላ ምክንያት ቢቋረጥ የወደብ አገልግሎት ወዲያውኑ እንደሚቋረጥ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

የኢሕአዴግ መንግሥት የኬንያን ወደቦች እንደ አማራጭ ለመጠቀምም ምኞት እንዳለው ቢገልፅም ከዚያም ችግር እንዳለበት አልደበቀም፡፡ "በድንበር አካባቢ በዚህ አሥር ዓመት ውስጥ የከብት ዝርፊያ አለ፡፡ እንዲሁም በሰሜን ኬንያ አነግና መሰሎቹ መጠጊያ የሚያገኙበት አጋጣሚ አለ. . ." በማለት ከኬንያም ጋር አንድ ቀን ግንኙነታችን ሊደፈርስ እንደሚችል ሥጋቱን ይጠቁመናል፡፡ *(አንደላይኛው ገጽ 104)*

ልብ እንበል ወገን፤ ይህን ሁሉ መቅበዝበዝና መባከን ምን አመጣው? አበው እንዲህ አይነቱን መያዣ መጨበጫ ወይንም ውሉ የጠፋ ነገር ሲያጋጥማቸው "ሰዶ ማሳደድ ካማረህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ!" ይላሉ፡፡ ወደብ አስረክቦ ወደብ ፍለጋ ላይ ታች መባከንን ምን አመጣው? ጠይቁ፡፡

የሕወሓት/ኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ባንድ በኩል የወደብን አስፈላጊነትና ጥቅም ይተርኩልናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል ከግንጠላው ማግሥት ጀምሮ "ታላቁ መሪያችን!" አቅልለውና አናንቀው "ግመሎቻቸውን ውሃ ያጠጡበት" ነበር ያሉን፡፡ ይህ ግን እውነት ነው? ታዲያ አሠብን ለናት አገር አሥረክቦ ላለፈ መሪ ዛሬ እኛ አፋችንን ሞልተን "የታላቁ መሪያችንን ራእይ እናሳካለን!" እያልን ስንጮህ አናሳፍርም? መናጀነታችንስ አልበዛም? ወደብ አልባ ራእይ ይዘን ነው የምንጓዘው? ጠይቁ፡፡

<><><>





# ጎሠኝነት ኢድኋዊነት ነው

ጎሰኝነት እጅግ የከፋ አድሏዊነት ነው፡፡ ጎሰኝነት ከቻለ ሌሎቹን አጥፍቶ በዚች ምድር ላይ እኔ ብቻ ልኑር የሚል ህመምተኛ ሥርዓት ነው፡፡ ከዚህ ዝቅ ካለ ደግሞ ሌሎቹን አዳክሞና ማንነታቸውን ቀብሮ በሱ ማንነት ሥር ውጦ እያንጫጫ ከንስሳ ባነሠ መልኩ ረግጦ መግዛት ነው፡፡

ጎሣ ከነገድ ቀጥሎ የሚገኝ የማኅበረሰብ ስብስብ ሲሆን በሕዝብ ቁጥር፣ በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ የበታችነት ስሜት በእጅጉ ያጠቃዋል፡፡ ጎሰኛ ግለሰቦችም በሌሎች የማኅበረሰብ አባላት ላይ የጥላቻ ሥዕል በአእምሮቸው ውስጥ በመሣል ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከመበቀል ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ አገራችን የጎሣ ነቀዝ ዱቄት እያደረጋት ያለው፡፡

ጎሰኝነት ገንግኖ ዘውድ ከመጫኑ የተነሣ እያንዳንዱ ጎሳ ወይንም ብሔረሰብ አገራዊ ራእይ ለቆ ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉም በመንደር ታጥሮ ወይንም ትንሽየ ኩሬ ውስጥ እንደ ሚያንቋርሩ እንቁራሪቶች ቁር ቁር ሲሉ ኢትዮጵያን ረሷት፡፡ በመርሳታቸውም ብልጦች አንጡራ ሀብቷን ሲቦጠብጡ እነሱ የበይ ተመልካች ሆነው ቋንጣ እንዳየች ድመት አንጋጠው እያዩ ሜው! ሲሉ ያሣዝናሉ፤ ወይንም ያናድዳሉ፡፡

እንደሚታወቀው ሕወሓት አንድን ብሔረሰብ ብቻ ገንጥሎ ሉዓላዊት አገር ለማድረግ ለ17 ዓመታት በፋኖነት የቆየ ድርጅት ነው፡፡ በመሆኑም መግዛት እስከቻለ ድረስ እያምታታና በጎሳ ሽፋን ዜጎችን እስበስ አናክሶ እነሱ ሲፋጠጡ እሱ ግን የሥልጣን ዕድሜውን በማራዘም ከወርቅ ማዕድን ጀምሮ መሬትን ለትውልድ እንዳይተርፍ አድርጎ እንደተራ ሸቀጥ በማይመጥን ዋጋ በጭካኔ እየቸበቸበ ይገኛል፡፡ መግዛት ሲሳነው ደግሞ የትግራይን ሕዝብ የሙጥኝ በማለት "አማራና ኦሮሞ መጡብህ!" እያለ ዳግም ወደ በረሃ እስከ መግባት ድረስ ያልማል፡፡

ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ኤርትራ ዘልቀው ንግግር ባደረጉበት ወቅት "በናንተ ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በኔም ጀርባ ላይ አለ" ሲሉ ሠፊና መርዛማ ንግግር አሠምተዋል፡፡ ልብ እንበል፤ አቶ መለስ በናታቸው በኩል ኤርትራዊ ናቸው፡፡ ግን ደግሞ በታሪክ አጋጣሚ የኢትዮጵያ መሪ የመሆን እድል አጋጥሟቸዋል፡፡ ተዋግተው ባስገጠሏት የናት አገር ሄደው ንግግር ሲያደርጉ

ግን ቂምና በቀልን በሚመሩት ሕዝብ ላይ አርግዘው እየወነጀሉና እያሳጡ ነበር፡፡ "ዘር ከልጓም ይስባል" እንደሚባለው ከኤርትራውያን ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በሳቸው ጀርባ እንዳለና እየተበቀሉላቸው መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነበር፡፡ ለዚህም ነው በግንባር ቀደም በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ባማራ ሕዝብ ላይ መቋጫ የሌለው እንግልትና ወከባ እየተፈፀመበት ያለው፡፡

የሕወሓት ሰዎች እውነትን መድፈር አይሆንላቸውም እንጂ በነሱም ሆነ በሻዕቢያ ጀርባ ላይ ያለው ቁስል በሌሎች ኢትዮጵያውያን ጀርባ ላይምኮ አለ፡፡ ጥያቄው ቁስሉ እንዴትና በምን ምክንያት ተፈጠረ? የሚለው ነው፡፡

የሚያሳዝነው ደግሞ ይህ የጀርባ ቁስል ሳይፈርጥ ሌላ የጀርባ እባጭ መፈጠሩ ነው፡፡ የመጀመሪያው እባጭ ወይንም የጀርባ ቁስል ሊፈጠር የቻለው ኤርትራ ሳትገነጠል እንድትኖር ከገንጣዮችና ካስገንጣዮች ጋር ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባደረገው ፍልሚያ ነበር፡፡ ገንጣይና አስገንጣዮች በለስ ቀናቸውና ኤርትራ ተገነጠለች፡፡ ቁስሉ በዚሁ ቢሽር ኖሮ በጎ በሆነ ነበር፡፡ ግን አልሆነም፡፡ ሊሆንም አይችልም፡፡ በመሆኑም ርቀን ሣንሄድ ከ10 ኪሎ ሜትር ለማትሰፋ ባድሜ ያን ያህል ደም ማፍሰስ የጀርባ ቁስል ብቻ ሣይሆን የጭንቅላት ካንሠርም ነው፡፡ ሕወሓት የፈጠረው ስለሆነ ግን ሕጋዊና ተገቢም ነው፡፡

ይህ የከፋ ከፋፋይ የጎሳ ሥርዓት እንዲቀጥልም ያቶ መለስ ቅምጥሎች ዛሬ "የታላቁ መሪያችን ራእይ ከግቡ እናደርሳለን!" እያሉ በጎሳ መጋረጃ ውስጥ ሆነው ማሽሟጠጣቸው ደግሞ አንጀት ያቆስላል፡፡

አቶ መለስ የጎሳ በሽታ የተጣባቸው መሆኑ የሚታወቀው ገና ከማለዳው ሥልጣን ላይ እንደ ወጡ ልክ ባንዲራን "ጨርቅ" እንዳሉ ሁሉ "ያክሱም ሐውልቶች ለወላይታው ምኑ ናቸው? የጎንደር የነገሥታት ግንቦች ለኦሮሞው ምኑ ናቸው? የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ለደቡብ ሕዝብ ምኑ ናቸው?" በማለት መናገራቸው ነበር፡፡ እሳቸው እንዲህ ይበሉ እንጂ ኢጣሊያ በወረረችን ጊዜ ካክሱም ነቅላ የወሰደችው ሐውልት ወደ አገሩ ተመልሶ ሲተከል በክብር እንግድነት የተገኙት የወላይታው ተወላጅ የወቅቱ የተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባዔ የተከበሩ አቶ ተሾመ ቶጋ ነበሩ፡፡ ይህስ እንዴት ይታይ ይሆን? ጠይቁ፡፡

አቶ መለስ "ያክሱም ሐውልቶች ለወላይታው ምኑ ናቸው?. . ." ሲሉ ተራና እንደ ቀልድ የተናገሩት አይደለም፡፡ የምራቸውን ነበር፡፡ በረሃ ሳሉ





ይንተከተከባቸው የነበረውን ጥላቻና ትግራይን የመገንጠሉ በሽታ ከአእምሯቸው ውስጥ ያልተፋቀ መሆኑን ማረጋገጫ ነበር፡፡ በሌላ በኩልም የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን የባለቤትነት መብት ለመሸርሸርና ለማጥፋት የታለመ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ሌላው ያቶ መለስ ጎሰኛነትና አድሏዊነት ከጢስ ዓባይ ተጎትቶ ወደ ትግራይ የተወሰደው የኤሌክትሪክ መሥመር በጋይንት አድርጎ ሲያልፍ ጋይንቶች "እባካችሁን ትንሽ ለኛም ትረፉን" ሲሉ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ የግፍ ግፍ ጥያቄ ማቅረባቸውም ጥርጣሬን ፈጥሮ በኤሌክትሪክ ገመዱ ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ በሚል ስጋት በእያንዳንዱ ምሰሶ ስር ሦስት ሦስት አባወራዎች እንዲጠብቁ ይበየንባቸዋል፡፡ እናም በምሽት በዚያ የሚያልፉ መንገደኞች በየምሰሶዎቹ ስር ቁመው ሲያዩዋቸው ገርሟቸው፡-

"በምሽት ከግንድ ሥር ቁማችሁ ምን እየጠበቃችሁ ነው?" ብለው ሲጠይቋቸው፡-

"የሕወሓት መኳንንት ራታቸውን ሲበሉ ቁመን መብራት እያበራን ነው!" አሉ፡፡ ይህ አባባል እንደ ቀልድ የተነገረ ይምሰል እንጂ የምሬትና የቁርሾ መሆኑ ግን የሚካድ አይደለም፡፡ ወይንም በሌላ ምክንያት ማስተባበል አይቻልም፡፡

በሌላ ጊዜ በሌላ ጉዳይ ስለ ኤሌክትሪክ መብራት ለጠ/ሚንስትሩ ጥያቄ ሲቀርብላቸው "ይህ የጋይንት ሕዝብ ጥያቄ ነው" ሲሉ በቁጣ ነበር የመለሱት፡፡ ይህ አባባላቸውም የሚያመለክተን ምን ያህል በከፋት እያኘኩ ይዘውት የቆዩ መሆናቸውን ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የባድሜ ጦርነት ይከሰታል፡፡ የጋይንት ወጣቶች ለውትድርና ሲሆን ይፈለጉና ወታደር ካልሆናችሁ ተብለው መግቢያ መውጫ ያጣሉ፡፡ በዚህ ወቅት ወላጆች "እባካችሁን እንደ መብራቱ ውትድርናውንም ዝለሉን" አሉ ይባላል፡፡

ሌላው ሣይጠቀስ መታለፍ የሌለበት፤ ኢጣሊያ ባምስቱ ዓመት የግፍ ወረራ ለፈፀመችው የጦር ካሣ እንድትከስ ተበይኖባት የቆቃን ግድብ ሠርታ ከሳለች፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በብዛት የሚያውቀው ሌላ የጦር ካሣም ክሣ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራን ጨምሮ በ1933 ዓ.ም ነፃ ሲወጡ የጎንደር ሕዝብ ግን ነፃ የወጣው ካንድ ዓመት በኋላ 1934 ዓ.ም ነበር፡፡ የዚህን ምክንያት "ጎንደር ያነዬ" በሚል ርእስ (ገና

ያልታተመ) የጻፍኩት ስለሆነ ከዚህ ላይ የማነሣው ነገር የለም። የሆነ ሆኖ ኢጣሊያ ለጎንደር ሕዝብ ስንት ሜጋ ዋት )እንደሚያመነጭ አላውቅም እንጂ አንድ ግዙፍ ጄኔሬተር ከሳ ነበር። ይህንን ጄኔሬተር ጎንደሮች በደም ባጥንታቸው ያገኙትን ወይንም የደማቸው ካሣ የሆነውን "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሠብራል!" እንዲሉ ጀግናው ሕወሓት በሌሊት ነቅሎ ወስዶ ትግራይ ውስጥ ተክሎታል። ይህንን እብሪትና ከፋትስ በምን ቃል መግለፅ ይቻላል? ግፉና በደሉ ወይንም የጎሰኝነት አድሏዊነቱ በዚህም አያበቃም።

ተከዜን የሚያህል ዓለም ዓቀፍ ወንዝ ወሰን ሆኖ እያለ ሴቲቱ ሁመራን፣ ወልቃይት ጠገዴን፣ ማይፀምሬን ወደ ትግራይ ክልል ከልለዋቸዋል። ይህንን በተመለከተ እውቁ አቀንቃኝ ፋሲል ደመወዝ፡-

*"ሴቲቱን ወሰዱት ያውም የኛን እጣ*
*እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ!"*

ብሎ ቁጭቱን በመግለጹ ቀጠቀጡት። ከሞት ቢተርፍም ዳግም ወደ ሚወደው የኪነት ሙያ እስካሁን አልተመለሰም። ይህንንስ በምን ቋንቋ መግለፅ ይቻላል? ጠይቁ።

እነዚህ ሠፋፊ ወረዳዎች በየትኛው ዘመን፣ በየትኛው ንጉሥ ጊዜ የትግራይ የግዛት ክልል ሆነው እንደነበርና ጎንደሮች ከፍ ሲልም አማራዎች ከትግራይ ሕዝብ ጋር ተፋልመው ተነጥቀው ወደ ጎንደር ተከልለው ስለመቆየታቸው የሚጠቁም የታሪክ ማስረጃ የለም። ይህ አድሏይነትና ጎሰኝነትም ሁለቱን እህትማማች ሕዝቦች በመልካም ጉርብትና እንዳይኖሩ የከፋ ቁርሾ ለመትከል ነው።

የሕወሓት ፋኖዎች የጎንደርን ለም መሬት (ሰሊጥ፣ ጥጥ፣ ማሽላና የሙጫ ዛፍ) አብቃይ የሆኑ ወረዳዎችን በጊዜ አጋጣሚ ነጥቀዋል። ሌላ ዳኛና የታሪክ ምስክር አያስፈልግም። የተከዜ ወንዝ ራሱ የተፈጥሮ ምስክር ነው። ከዚህ ውጭ ለጊዜው የሚባል ነገር የለም። ይኸ ሁሉ ግፍ እየተፈፀመ ያለውም "በታላቁ መሪያችን" ዘመን ነው።





# ባማራ ሕዝብ ላይ በቀልተኛው ሕወሓት

የሕወሓት መሪዎችና ካድሬዎች ወንድማማች የሆነውን ያማራንና የትግራይን ሕዝብ ለምን ዘለዓለሙን በባላንጣነት በማፋጠጥ ሲያደሙት ለመኖር ታጥቀው እንደተነሱ መነሻ ምክንያታቸው ከነሱ በስተቀር ማንም ሊያውቅ አይችልም። እንደኔ የጥላቻ መነሻ ምክንያታቸው ግራ የገባው ከብሮም ብርሃነ (ከመቀሌ) እንዲህ ይለናል፡-

"ሁሌ የሚያሳስበኝ አንድ ነገር አለ። ይኸውም የሕወሓት ካድሬዎች ያማራ ሕዝብን ‹በነፍጠኝነት ስም› መወንጀል የዘር ፕሮፓጋንዳ በየቀበሌው ሲያወርዱበት እንደሚውሉ የብአዴን አባል ነን ባዮች አያውቁ ይሆን?" ሲል በመገረም ከጠየቁ በኋላ ግርምቱን በመቀጠል "ያማራ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በየትኛውም ጊዜ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ጋር ተባብሮ የሀገሩን ክብርና ዳርድንበር እንዲሁም ታሪክ ሲጠብቅ የኖረ እንጂ ፀረ-የትግራይ ሕዝብ ሆኖ አያውቅም። አለ ከተባለም በተጨባጭ ጊዜውንና ቦታውን ለይተው እስከነ ጥፋቱ መጠን ለትግራይ ሕዝብ ሊነግሩት ይገባል. . ." ይላል። *(ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 54 ማክሰኞ ነሐሴ 1 ቀን 2004 ዓ.ም)*

ከብሮም ብርሃነ እውነቱን ነው። ያማራ ሕዝብ የትግራይን ሕዝብ መቼና እንዴት? በነማን ዘመንስ ዘምቶ ዘርፎትና ኢቃጥሎት ይሆን? አፄ ምኒልክ በ1888 ዓ.ም አድዋ ተራሮች እስከነ ባለቤታቸው የዘመቱት ጣሊያንን ለማባረር ሣይሆን የትግራይን ሕዝብ ለመውረርና ለመዝረፍ ከሆነ ወይንም ከጣሊያን ጎን ተሰልፈው ወግተውት ከሆነም በግልፅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይንገሩት። የትግራይ ሕዝብም በግልፅ እስከነ ምክንያቱና ጥፋቱ ይነገረውና አውቆት ወንድሙ የሆነውን ያማራ ሕዝብ በግልፅ ይውቀስበት። ያማራ ሕዝብም እውነት በትግራይ ሕዝብ ላይ አባቶቹ አሁን የሕወሓት ካድሬዎችና ታጣቂዎች ባማራ ሕዝብ ላይ እንደሚፈፅሙበት ያለ ግፍ ፈፅመውበት ከሆነ "ያባት ዕዳ ለልጅ ይተርፋልና" በግልፅ ወንድም የሆነውን የትግራይን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቅበት። ከይቅርታ የበለጠ ደግሞ ያበጠ ቁስልን የሚያፈርጥ የለም። አለበለዚያ በደፈናው ለሥልጣንና ያገርን ሀብት ለመዝረፍ ሲባል ያማራን ሕዝብ በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ በጅምላ በትር ባል ያዘበት ዘመን "ነፍጠኛ!" እያሉ መዝለፍና በሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዲጠላና እንዲፈራ መቀስቀስ የኋላ ኋላ መዘዙ ሳጋር አንድነት አይበጅም። ለትውልድ ጥበብን እንጂ የከፋትን ሥንቅ ቋጥሮ ማቆየት ከፉ የደም በሽታ ይመስለኛል። ነግ በኔ

ነውና ይህ የሕወሓት እኩይ ተግባር ሊገታና ሊቆም ይገባዋል፡፡ በዚህ ሁኔታስ አይጥና ድመት ተሁኖ እንዴት እንደ አንድ ሕዝብ አብሮ ተከባብሮ መኖር ይቻላል? ጠይቁ፡፡ በተረፈ የብአዴንን አመራሮች በተመለከተ በያጋጣሚው እነማን እንደሆኑ የተገለፀ ስለሆነና ሕዝቡም በሚገባ ስለሚያውቃቸው ከዚህ ላይ ስማቸውን እነከሌ እነ ከሌ እያሉ መዘርዘሩ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ባጭሩ ግን አማርኛ ተናጋሪዎች የኤርትራና የትግራይ ልጆች ሆነው የጎንደር ሕዝብ ወይንም ሌላው ያማራ ሕዝብ አቅፎ ደግፎ፣ በጉያው ይዞ ኮትኩቶ ያሣደጋቸው ናቸው፡፡ "የናት ጡት ነካሽ!" ሆነው ዛሬ እየቀለዱበት ያሉት፡፡ ታሪክ ይፍረደው፡፡



ክብሮም ብርሃን

የትግራይና ያማራ ሕዝቦች ከጥንት ጀምረው ኢትዮጵያ እንደ አገር ሥትመሠረት ከዳማት መንግሥት ጀምሮ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ሸዋ፣ ጎንደር የነገሥታቱ በተለያዩ ጊዜያትና ዘመናት መቀመጫዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ ሲኮንም የተጠቀሱት ሕዝቦች ብቻ ሣይሆኑ ሌሎቹም ሕዝቦች አብረው ኑረዋል፡፡ አብረው በመኖራቸውም ተጋብተዋል፤ ተዋልደዋል፤ የባህልና የቋንቋ መዳቀልንም ፈጥረዋል፡፡ በነዚህ ሂደቶችም ያማራና የትግራይ ሕዝቦች ማዕከል ወይንም ያንድነት ርሾ ስለመሆናቸው በየታሪኩ ተጠቅሶ





ይገኛል፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም ባማራ ሕዝብ ላይ የሚያዘንበው የከፋት ፕሮፓጋንዳና የዘር ማፅዳት ዘመቻ ከምን የመነጨ ነው? ይህንን ጥያቄ ያማራ ሕዝብ ብቻ ሣይሆን የትግራይ ሕዝብም ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህንን ሀቅ ጠይቆ እውነቱን ሊጨብጥ ይገባዋል፡፡ ሕወሓት እንደ ሌጣ ፈረስ ሊጋልበን አይገባም፡፡ ከእውነት የበለጠ ቁስልን የሚያሽር ነገር የለምና እያንዳንዱ ዜጋ ከከፋትና ከግል ጥቅመኝነት ተላቆ እውነት የመፈለጊያው ጊዜ አሁን ነው፡፡ በምንም መመዘኛ "በታላቁ መሪያችን ሞት!" እየተባልን ልንደለልና እንደ ሕፃን ልጅ በከረሜላ ልንታለል አይገባንም፡፡

ያማራና የትግራይ ሕዝቦች ከፉ በጎን በጉርብትና እኩል ተካፍለዋል፡፡ ከቋንቋ በስተቀር የሚለያያቸው የለም፡፡ ቋንቋንም ቢሆን ራቅ ያሉት የጎጃም፣ የደቡብ ወሎና የሸዋ አማራዎች ካልሆኑ በስተቀር የጎንደር አማራዎች ትግሬኛንም እኩል ካማርኛ ጋር ይናገሩታል፡፡ ዛሬ ጊዜ አገኘን ተብሎ ተከዜን ተሻግረው መሬት እስከ መከለል የተደረሰውም የጎንደር አማራዎች ትግሬኛ ቋንቋን በመናገራቸው ነው፡፡ ያንዱን ቋንቋ በጉርበትና፣ አብሮ በመኖር ወይንም በሌላ ኢጋጣሚ መናገርም በበጎ መልኩ ሊታይ ሲገባው መሬትንም የሚያስነጥቅ ከሆነ መጥፎ ሥንቅ ነው፡፡ ልብ እንበል፤ ቋንቋ ወሰን ከሆነ ያማሮች አገር ሠፊ ሊሆን ነው፡፡ የኛን ምሳሌ እንተወውና ቋንቋ ያንዲት አገር የደም፣ የሥጋና ያጥንት ወይንም የጎሳ ወሰን ከሆነ እንግሊዝ ቅኝ የገዛቻቸው አገሮች ሁሉ ማለትም እንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያፍሪካ አገሮች የእንግሊዝ አካሎች ሊሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ የቋንቋ ወሰን መዘዙ ብዙ ነው፡፡ልብ እንበል፤ ሕወሓት ተከዜን ተሻግሮ የጎንደሮችን መሬት ወደ ትግራይ መከለሉ ትልቅ የከፋት ሥንቅ ነው ለሁለቱም ሕዝቦች ያስቀመጠው፡፡

ጥንት በማልዱ መሣፍንቱ በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የስበስ ጦርነት ቢያካሂዱም ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ቁርሾና በቀል የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ አሸናፊው አገር ያስተዳድራል፤ ተሸናፊው አቅሙን አውቆ ይገብራል፡፡ ከዚህ ውጭ ለሕዝቦች የሚቆይ የከፋት ሥንቅ አልነበረም፡፡ ጦርነቶቹም ይካሄዱ የነበሩት በገዥ መደቦች መሀከል በሥልጣን ይገባኛል ምክንያቶች እንጂ አንድ ሕዝብ በራሱ አነሳሽነት ሌላውን ሕዝብ የወረረበት ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተከስቶ አይታወቅም፡፡ የገዥ መደቦችን ተከትሎ ግን የዚህ ጎሳ የዚያ ብሔረሰብ ሳይባል አብሮ እየዘመተ መውረሩና ጥፋት ማጥፋቱ እውነት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ፍልሚያ ባህላችንም ነበር•ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ ያማራ ሕዝብ የትግራይን ሕዝብ የቱን የገዥ መደብ ወይንም ንጉሥ ተከትሎ



ኪብሮም ብርሃን

ሄዶ ወይንም በራሱ አነሳሽነት እንደ ዘረፈው እንዳቃጠለው ወይንም እንደ ጨፈጨፈው በታሪክ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ ይህ ሥር የሰደደ ጥላቻና የደም ካንሠር የሆነ የጎሳ በሽታ ከየት መጣ? የሕወሓትን አመራሮች እንዴት ተጣባቸው? ይህንን የጠላትነት በቀልስ ከየት አመጡት? ብሎ አጠንክሮ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

ብዙ አዛውንቶች እንደሚሉትና እንደ ሚስማሙበት ከሆነ ይህ ሥር የሰደደ ጥላቻና ያመረቀዘ ከፋት ምንጮቹ ዐረቦቹና ቅኝ ገዥዎች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የዚህ የጥላቻ ቫይረስ ተሸካሚ ደግሞ ሻዕቢያ መሆኑ አይካድም፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለፀውና እንደሚታወቀውም አብዛኞቹ የሕወሓት አመራሮች ጠ/ሚኒስትሩን ጨምሮ አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ አንዳንዶቹ ደግሞ በከፊል ከሻዕቢያ ጋር የደም አንድነት አላቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር አሠልጥኖ ባምሳሉ የቀረፃቸው ሻዕቢያ ነው፡፡ የዚህን እውነትነት ለማወቅ በሦስት ከፍሎ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

## ያድዋ ድል

እንደሚታወቀው ያድዋ ድል ነጮቹን (ቅኝ ገዥዎችን) ባላንጣ ገዝቶልናል፡፡ ለምን? ቢባል ዓድዋ በቅኝ ግዛት ሥር ይማቅቁ ለነበሩትን ሁሉ ዐይኖቻቸውን የከፈተ ነበር፡፡ በተለይም አፍሪካውያን የራሳቸው ድል አድርገው በመቁጠር ይኮሩባታል፤ ይመኩባታል፡፡ በመሆኑም ካድዋ ድል ማግሥት ጀምሮ በቅኝ ገዥዎች ሥር ይገዙ የነበሩ አገሮች ሁሉ አመፁ፡፡

ባንፃሩ የኢጣሊያ ሽንፈት የእንግሊዝም፣ የፈረንሣይም (የቅኝ ገዥዎች) ሽንፈት ተደርጎ ተወሰደ፡፡ አፍሪካውያን በድሉ እንደኮሩ ሁሉ ቅኝ ገዥዎች ደግሞ በሽንፈቱ አፈሩ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቅኝ ገርዎች የቤት ሥራ እስበሱ እንዲናከስ ሴራ መቀየስ ሆነ፡፡ የዚህ ሰለባ ደግሞ በግንባር ቀደም ከንፉ መመታት ያለበት አማራ ሆነ፡፡ ለዚህም ነው በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ያድዋ የድል ቀን ሲታሰብ ወይንም ሲከበር የምኒልክ ስም የማይጠቀሰው፡፡ ይህ ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ነው፡፡ ዝርዝሩ ሠፊ ነው፡፡ በመጠኑም ቢሆን ባፄ ምኒልክ አጭር ታሪክ ውስጥ ያሠፈርኩት ስለሆነ ከዚህ ላይ በጥልቀት አልገባም፡፡ ለማመልከት የፈለኩት ያድዋ ድልም ላንድነታችንም፣ እስበሳችንም ለመናከስ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረጉን ጠቆም አድርጌ ለማለፍና ያድዋ ዘመቻ አዝማቹ አፄ ምኒልክ በመሆናቸው ብቻ አማራን በቅኝ ገዥዎች ጥርስ ውስጥ ገብቶ እስካሁን እየታኘከ ያለመሆኑን ለማመልከት ነው፡፡





## ክርስትና ሃይማኖት

ሌላው ኢትዮጵያን ሰለባ ያደረጋት "የክርስቲያን ደሴት" የሚለው ደረቅ የቆየ ምስል ነው፡፡ ይህ መፈክር ግን ከሙስሊም ወንድሞቻችን ጋር ተቻችለንና ተፋቅረን፣ አንድ ሆነን ለመኖር እንቅፋት አልፈጠረብንም፡፡ እንዲያውም በሚያስደንቅ ሁኔታ ተጋብተውና ተዋልደው ያንዱን እምነት ሌላው ወዶ ተቀብሎ ወይንም ሚስት ሙስሊም ባል ክርስቲያን ወይንም ደግሞ ባል ሙስሊም ሚስት ክርስቲያን ሆነው የሚኖሩባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች፡፡ ለዚህ ሀቅ ወሎ፣ ሐረርንና ድሬዳዋን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ከልሎች ሃይማኖት አጥሯቸው አያውቅም፡፡

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በዚያን ዘመን "የክርስቲያን ደሴት" ተብላ ብትጠቀስም ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ክርስቲያንና ሙስሊም ልጆቿን አቻችላና አስማምታ የኖረች አገር ስለመሆኗ ለ40 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩት ጆን ሐዘወይ ስፔንሰር ሳይቀረውላታል፡፡ *"ኢትዮጵያ የእስልምናን ወረራ ስትከላከል የቆየች አገር ብትሆንም ሙስሊም ሕዝቧን አቅፋ ለመኖር ችላለች. . ."* ሲሉ አድናቆታቸውን ገልፀዋል፡፡ *(ጥርስ የገባች አገር ገጽ 179)* ምሁሩ *"የእስልምናን ወረራ ስትከላከል የቆየች"* ያሉት የቱርኮችን፣ የግብፆችንና የድርቡሾችን ተደጋጋሚ ወረራዎችን ማለታቸው ነው፡፡

እንግዲህ ለኢትዮጵያ መገዝገዝ አንዱና ዋናው ክርስትና ሃይማኖት ነው ስንል የጥንት ነገሥታት በሚዘምቱበት ዐውደ ውጊያ ሁሉ የሚያፈቅሩትንና ለድል ያበቃኛል የሚሉትን ታቦት ይዘው ይዘምቱ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ብመጀመሪያም የከተት አዋጅ ሲያውጁ "አገርህ ተደፈረች! ሃይማኖትክን የሚያረክስ ጠላት መጣብህ!" በማለት ነበር፡፡ ለምሳሌ አፄ ምኒልክ አድዋ ሲዘምቱ ጊዮርጊስን ይዘው ነበር የዘመቱት ይባላል፡፡ እናም እነ ባልቻ አባ ነፍሶ በጥርኝ ፈረስ ከጠላት ምሽግ ድረስ እየጋለቡ በነፋስ ፍጥነት ከወዲያ ወዲህ እየተዋነኑ ሲያርበደብዱት የፋሽሽት ጦር መመከት ሲሳነው "እኛን ያጠቁን በጥርኝ ፈረስ የሚዋጉት ናቸው፡፡ በተለይ አንዱ ጊዮርጊስ ሣይሆን አይቀርም!" ማለታቸው በስነ ቃል ከጊዜችን ድረስ ዘልቋል፡፡

ዐረቦቹ በተለይም ግብፆች "የክርስቲያን ደሴት" የሚለው አባባል ሲመራቸውና ሲጎፈንናቸው የኖረ ለመሆኑ ተደጋጋሚ ወረራዎችን ያለምንም የመሬት የይገባኛል ጥያቄ ሳይኖራቸው ሙከራ አድርገዋል፡፡ የዚህ ምስጢሩ የሃይማኖት መስፋፋትም ሊባል ይቻላል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን የኦርቶዶክስ

ሃይማኖትን ለመገዝገዝ ነጮቹም ከጥቅማቸው አንፃር ተጨመሩበትና ኢትዮጵያን ለመበታተንና ለማዳከም አንዱን ብሔረሰብ ከሌላው ወይንም አንዱን ወገን ገዥ ሌላውን ወገን የተገዥ ወገን አድርገው በመሣል እስበሱ አስተናንቆ ማፋለምና ወደ ድህነት አረንቋ ውስጥ እንድንዘፈቅ አማራጭ ያልተገኘለት ምርጫ ሆነ:: ይህ ዘዴ ሲመረጥም አርቶዶክስ ሃይማኖትን ከተቻለ ማጥፋት ካልተቻለ በሌሎች የተለያዩ ሃይማኖቶች እንዲዋጥ ማድረግ ነው::

ይህ ቀመር ሲነደፍም የዚህ ሃይማኖት ቀንደኛ አማኝና ተከታይ ተደርጎ የተወሰደው ያማራ ዜጋ ነው:: አርቶዶክስን ማጥፋት ወይንም ማዳከም የሚቻለው በመጀመሪያ የእምነቱ ተከታይ የሆነው አማራ ሲመታ ነው በሚል ይመስላል በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ የመስቀልና የጥምቀት ዋዜማዎች እየተጠበቁ ታርደዋል:: በጅማ፣ ባርካ፣ ባሰቦት፣ የዋልድባ ገዳም ሣይቀር ወደ ስኳር ኢንዱስትሪነት እንዲቀየር የተበየነበት የዚህ ሃይማኖቱን የመገዝገዝ ቀመር ነው:: ይህ ሁሉ ጥፋት ባማኞቹ ላይና በገደማቱ ሲፈፀም የእምነቱ አባቶች ድምፃቸውን ሲያሰሙ አልተሰሙም:: ርግጥ ነው አንዳንድ ቢኖሩም ወይ ተሰደዋል ወይ ተገለዋል:: ዛሬ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሁለት ሲኖዶስ የምትታወቅ ሀገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ ነች::

ሌላው ሴራ ከሙስሊም ወገኖቻችን ጋር ለማዳማትና እስከ መጨረሻው ድረስ ለማቆራረጥ የኢሕአዴግ ሹሞች ሲፈፅሙ ቆይተዋል:: ከቤተክርስቲያን አጠገብ መስጊድ እንዲሠራ ወይንም ካልጠፋ ቦታ ጥምቀተ ባህር የሚከበርባቸው ቦታዎች ለመስጊድ መሥሪያ እየተፈቀዱ ቦታና ጊዜ እየተመረጠ መጠነ ሠፊ ደም ፈሷል:: እነዚህን ሁሉ የሚቆስቁሷቸው የዘመኑ ካድሬዎች ናቸው::

ይህንን እኩይ ተግባር ለመሞገት ወጣቱ ትውልድ ሰንፏል:: ወይንም አገራዊ ደባውን በቅጡ የተገነዘበው አይመስልም:: በምእራባውያን የኳስ ፍቅር ናላው ዞሯል:: በዘፈኑ፣ በዳንኪራው እየማለለ ሳይዋጋ የባእዳን ወይንም የውጭ ምርኮኛ ሆኗል:: ላባቱ ገዳይ እናቱን የሚድር ልጅ እየተወለደ ነው:: ያሣዝናል::

## ዓባይ ሦስተኛው ጠላት የገዛልን

በሦስተኛ ደረጃ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለዚች አገር ጠላት የገዛላት ዓባይ ወንዝ ነው:: ለምን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎች እንደማይነሱ





ተስፋ አደርጋለሁ:: ባጭሩ ግን ዓባይ ለግብፆች ሕይወትና አለኝታ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ተረጋግተው ከሠሩ የጥበብ ባለቤት ለመሆን የሚሣናቸው ነገር አይኖርም በሚል ምንጊዜም እንቅልፍ የማያስወስድ ፍርሃት አላቸው::

ኢትዮጵያውያን የጥበብ ባለቤት ሆነው ዓባይን ከመገደብ ጀምረው እስከ ማትነን ድረስ ቢራመዱ የኛ ሕልውና አከተመ ብለው ግብፃውያን ያምናሉ:: እናም ይህ ከመሆኑ በፊት ኢትዮጵያውያንን እስበሳቸው አስተናንቆ ማመስና ሰላማቸውን ማሣጣት ከተቻለ አይደለም የጥበብ ባለቤት መሆን ሠርተው የእለት እንጀራ ማግኘት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ብለው አመኑ:: ለዚህም ነበር ኤርትራ ከናት አገሯ እንድትገነጠል ሁለንተናዊ ድጋፍ በመሥጠት የእህት ባላንጣ ከጉያችን በመፍጠር እኛኑ በኛው ያዳሙን:: ሕወሓት የዚህ ሴራ ውጤት ነው:: አገር ተዋግቶ አስገንጥሏል፤ የባሕር በር አሣጥቷል፤ እድገታችንን አኮስምኗል፤ ቀሪዎቹን የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦችና ጎሣዎች አንዱን ከሌላው በማናከስ የበቀልን ዘር እየዘራ ይገኛል:: በዚህ ሁኔታ እስበሱ የተናከሰ ሕዝብ አንድ ሆኖ ተግቶ ሠርቶ ከድህነት አረንቋ ይወጣል (ይላቀቃል) ተብሎ አይታሰብም::

በመጀመሪያ መቅደም የነበረበት በሕዝቦች መሀከል ሰላም መፍጠር ነበር:: ሰላም ካለ ፍቅርና የሕዝቦች መተሳሰብ ይኖራል:: መተሳሰብ ካለ ደግሞ ሥራ ይፈጠራል:: ከተሠራ ደግሞ ብልጽግና ይኖራል:: ብልጽግና ካለ ደግሞ ጥበብ ይኖራል::

አፄ ቴዎድሮስ ደብረታቦር አጠገብ ጋፋት ላይ የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ አቋቁመው ነበር:: ከሳቸው ውድቀት በኋላ ግን መከኖ ቀረ:: ቀጣዩ ንጉሥ አፄ ዮሐንስ አርማቸውን ለማንሣት አልፈቀዱም:: ምናልባት ከእንግሊዞች ጋር ልቃቃር እችላለሁ ብለው ሥግተውም ይሆናል:: ወይንም መርሀቸው ሃይማኖት ስለነበር የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪው ጉዳይ አልተከሠተላቸውም ይሆናል:: ወይንም ደግሞ ያፄ ቴዎድሮስ ውጥን በመሆኑ ጠልተውት ይሆናል:: አሁን በዘመናችን እንኳን ደርግ የጋፋትን የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም ቀላል የጦር መሣሪያዎችን (ከላንሽኮብ፣ ማካሮብ ሽጉጥ. . .) ማምረት ጀምሮ ነበር:: ደርግ በቀመሩ መሠረት በወያኔ ባፍጢሙ ሲደፋ ጋፋት ኢንጂነሪንግም አብሮ ተደፋ:: አሜሪካኖች በሕወሓት በጎ ፈቃድ ፈንጂ አምካኝ ጥበበኞቻቸውን ልከው ጓዳ ጎድጓዳችን ሁሉ ፈትሸውና አምክነው ሄደዋል::

ይህ ሁሉ ሲሆን ግንባር ቀደሙና ቀንደኛ ጠላት ተብሎ ተፈርጆ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚዋከበውና የሚመታው አማራ ነው:: ይህ ሲባል ግን በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ፣ በነገሌ ቦረና፣ በሶማሌ ክልል ግጭቶች አልነበሩም፣ ደም አልፈሰሰም ማለት አይደለም:: መጠኑ ይለያይ እንጂ ደም እንደ ጅረት ፈሷል:: ሁሉም ተቋስሏል:: በዚህ ሁኔታ እስበሳችን ተናክሰን አምራቹ ኃይል ወጣቱ ክፍል በምሬት አገሩን እየጣለ እየተሠደደ እንዴት ብለን ነው ከድህነት የምንላቀቀው? እስበሱ በጎሣ ጥላቻ የተናከሠ ሕዝብስ እንዴት ብሎ ነው አገራዊ ራእይ አንግቦ ተባብሮ ሠርቶ እንጀራ በልቶ የሚያድረው? ሌላው ቀርቶ ካንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል ተሂዶ በቀን ሠራተኛነት እንኳን ተቀጥሮ የማይሠራባትን አገር ምን ብሎ መግለጽ ይቻላል?

በመሠረቱ አማራ ራሱን እስካልተከላከለ ድረስ የመከራው ዘመን አያባራለትም:: የሕወሓት ሰዎች ዜጋችን ነው ብለው እንደማይተውትና እንደማይተኙለት ቀጥየ ከማቀርባቸው መረጃዎች መረዳት ይቻላል::





# የሕወሓት ሰዎች ምን እየቀበሩ ነው?

"መጥነው የጎረሱት አያንቅም!" ያበው አባባል:: አበው ይህነኑ አባባል በሌላ አቀራረብም እንዲህ ይገልፁታል "አፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥነዋል!" ከዚህ ቁም ነገር ስንነሳ የሕወሓት ሰዎች የሚናገሩትንና የሚሠሩትን የሚመጥኑ አይደሉም:: አንድም በጀብደኝነት አልያም በበቀልተኝነት እንዳገኙ መቀርደድ ነው:: መንግሥት ሆነው እንኳን የሽፍታ ተግባር ሲፈፀሙ ትንሽ አይሳቀቀጥጣቸውም:: መንግሥት ማለት ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነትና ሚዛናዊ ዳኝነት የሚሠጥበት ተቋም መሆኑን በቅጡ የተገነዘቡት አይመስሉም:: አንድ የመንግሥት አካል በዜጎቹ ላይ በቀለኛ ከሆነ በማን ሊዳኝ ነው? ማንንስ ሊዳኝ ነው? ይህንን ጠይቁ:: ምኒልክን የወቀሰ ፋኖ እሱ ራሱ መልሶ የሚበጫጭቅ አውሬ ሲሆን ምን ትታዘባላችሁ?

## ፍኖተ ገድል ወይንስ ፍኖተ ገደል?

አማራ የዘመኑ ታዳኝ አውሬ ለመሆኑ የተጋዳላይ ብሥራት አማረ ሥራ በቂ ማረጋገጫ ነው:: የመጽሐፉ ርእስ "ፍኖተ ገድል" ሲሆን ፍኖት ማለት መንገድ ማለት ነው:: የገድል መንገድ ለማለት ነው:: ለኔ ግን "የገደል መንገድ ነው" ከማንም ጋር የማያኗኑር፣ የማያቃብር በጥላቻ ተመርዞ ጥላቻን የረጨ ሥራ ነው:: ለማንኛውም ሥራውን እነሆ:-

*"ከቴዎድሮስና ከዮሐንስ ይልቅ የምኒልክ ወደ ሥልጣን መምጣት ኢትዮጵያን አሁንም ድረስ የገጠሟትን ሰፊና ውስብስብ ፖለቲካዊ ማህበራዊና ጎሳዊ ችግሮች ያስከተለ ክስተት ነበር . . ." ይለናል (ብሥራት አማረ ፍኖተ ገድል ገጽ 26)*

ብሥራት አማራ ይቀጥልና አማራን ከደቡብ ሕዝብ ጋር ለማናከስ መርዝ ሲዘራ እንዲህ ይላል *"ሌሎች ሕዝቦችን በተለይ የደቡብ ሕዝቦችን፣ <u>ዝቅተኛ፣ የልሠለጠኑ፣ ሞኛሞኞች፣ የንብረት ባለቤትነትና የመብቶች እኩልነት የማይገባቸው፣ የዱር አራዊት አድርገው ቆጠሯቸው"</u>* (ሥርዝ የራሴ) ይለንና *አያይዞ ". . .በኦርቶዶክስና ባከሱማዊነት ስም <u>በንፁህ ሕዝቦች</u> ላይ. . . ወራዳና ከፉ ተግባር. . . ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋርም* (ከትግሬዎች

*ለማለት ነው) በደቡብ ካደረጉት የማይተናነስ ደም አፋሳሽ ግጭት ደርሷል..." ይለናል:: (እንደ ላይኛው ገጽ 27)*

አፄ ምኒልክ በ1888 ዓ.ም "ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት!" ብለው አድዋ ተራሮች እስከነ ባለቤታቸው ዘልቀው ከኢጣሊያን ወራሪዎች ጋር ከመተናነቃቸው በስተቀር የትግራይን ሕዝብ የወረሩበትን ጊዜ በታሪክ አላውቅም:: ምሁራን አንድ በሉ:: ተጋዳላይ ብሥራት ግን "ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋርም. . . ደም አፋሳሽ ግጭት ደርሷል" ይለናል:: ተጋዳላይ ብሥራት ይቀጥልና:-

*"ለብቻ ለመነጠል የመረጡት ገዥዎች በመጨረሻ ያማራዊነት ፍልስፍና ለጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አጠናክረው ቀጠሉበት:: ብሔር ብሔረሰቦች በግዴታ አማራ ለማድረግ የተከተሉት ጎሣዊ ልዩነት . . . ባንድነትና በመብት እኩልነቶች ላይ ቅራኔ እንዲያመነጭ ምክንያት ሆኗል . . ." ይለንና ምሳሌ ሲያቀርብልን:-*

*"በወንጀል ሥራዎች የተነሳ ያክሱም ሕዝብ ያባረረውና ከ1962-64 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጊዜ ያክሱም ንቡረዕድ ተሹሞ የነበረው የሸዋው ሌርምያስ ከበደ ወልደ/ኢየሱስ ነው" ይለናል:: (እንደላይኛው ገጽ 27)*

ልብ እንበል፤ አበው "መጥነው የጎረሱት አያንቅም!" የሚሉት ያለምክንያት አይደለም:: ተጋዳላይ ብሥራት አንድ የሸዋ አማራ የሆኑ የቤተክህነት ሰው ያውም ኀሰኝነት ምን እንደሆነ ከነሱ በስተቀር ባልታወቀበት ዘመን አክሱምን ረገጧት ብሎ ምን ያህል እንደቆጠቆጠውና ምሳሌ አድርጎ እንዳቀረባቸው አስተውሉ:: "በወንጀል ሥራ የተነሳ ያክሱም ሕዝብ ያባረራቸው" ብሎናል:: የሠሩትን ወንጀል ግን አልገለፀልንም:: ሊገልፅልን ግን ይገባው ነበር:: ደግሞስ የቤተ ክህነት ሰዎች ጎሳና ቋንቋ ከመቸ ወዲህ ነው ወሰን ሆኖ የሚያግዳቸው? በተገኘ ቦታ፣ በተገኘ ጊዜ የክርስቶስን ቃል ይሰብካሉ፤ ያስተምራሉ፤ አድባራትን በቅንነት ያገለግላሉ፤ ያስተዳድራሉ፤ እንደ ብሥራት አማረ ስሌት ከሆነማ ዛሬ ጉድ ፈላ!! እስቲ ከዛሬው ጋር እያነፃፀርን ሕሊናዊ ፍርድ እንስጥ::

የቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና ወይንም የሲኖዶሱ ሕግ በማን ጊዜ ነው የፈረሰው? አንድ ፓትሪያርክ በሕይወት እያለ አባሮ ወይንም መፈንቅለ ፓትሪያሪክ አድርጎ ሥልጣን ላይ የተቀመጡ አባት ብቅ ያሉበት ዘመንስ በማን ጊዜ ነው? በምኒልክ ጊዜ? ወይንስ በቀ.ኃ.ሥ ጊዜ? ዛሬ በኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ





በማይታወቅ ሁኔታ ቤተክህነት ባንድ ጎሳ ሰዎች ብቻ ታጭቃ ያላንዳች መቆርቆር እየታመሰችና እየተመዘበረች ያለችውስ በማን ዘመን ነው? ዛሬ በቤተክህነት ጠ/ጽሕፈት ቤት ዙሪያ የሌሎች እምነት ተከታይ ዜጎችን ፈልጎ ማግኘት ብርቅ እየሆነ ነው:: ሌላው ቀርቶ አባ ጳውሎስ እንዳረፉ ተጠባባቂ ፓትሪያሪክ እንዲሆኑ የተሰየሙት እንኳን ያርሲ ሀገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ናትናዔል ናቸው:: የእምነት መለኪያው ዘር ከሆነ እኒህ አባት ከመጀመሪያውስ ቢሆን አርሲ ዞን ምን ሊያደርጉ ሄዱ? የኦሮሞ ዜጋ ጳጳሰው የዞኑን የእምነት ተከታዮች ማገልገል አይችሉም? ሁሉም ነገር ካባ ጳውሎስ ጎሳ ውጭ እንዳይሆን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ነው? ይህ እውነት ለመሆኑ 6ኛ ፓትሪያሪክ ሆነው የተመረጡት አቡነ ማትያስ የትግራይ ተወላጅ ናቸው:: ሌሎች አባቶች ለሐይማኖታቸው ብቃት የላቸው ይሆን? ጠይቁ::

እንደሚታወቀው ነፍሳቸውን ይማረውና አባ ጳውሎስ የሲኖዶሱን ሕግ አፍርሰው የፓትሪያሪክነቱን ሥልጣን ይዘው ከመንፈሳዊ ሕይወት ይልቅ ለሥጋዊ ቅምጥል ሕይወት ይሳሱና ይጎመጁ እንደነበር ባይናችን ያየነው ሀቅ ነው:: 3ኛው ፓትሪያሪክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጭብጥ ጥሬ እየቆረጠሙ በባዶ እግራቸው የሄዱላትን ቤተክርስቲያን አባ ጳውሎስ ባንፃሩ ጥይት በማይበሳው መኪና ሲንፈላሰሱ አይተናል:: ከዚህም ዘለል ባለ መልኩ ሕዝብ ክርስቲያን ምን ይለኛል ብለው ሳይጨነቁና ሳይሰጉ ዛሬ ሲያልፉ ሊሠራ የሚችለውን ሐውልት በሕይወት እያሉ ቦሌ መድኃኒዓለም ባንዲት ቀበጥ ወይዘሮ አማካኝነት አሠሩ:: ይህንንስ የሕወሓት ሰዎች እንዴት ታዩት ይሆን? የናንተ ሲሆን ቅዱስ የሌላው ሲሆን ርኩስ:: ራስን ከመለኮት በላይ አድርጎ መኖር እንዴት ይቻላል?

በመሠረቱ መነኮስ ማለት ሞተ ማለት ነው:: ሞተ ስንልም በሕይወት አለመኖርን ሣይሆን የዚችን ዓለም ጣፋጭ ሕይወት ንቆና ተጠይፎ ለዚያኛው ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲቃይ መቀበልና ሥጋን ማድከም ማለት ነበር:: አባታችን አባ ጳውሎስ ግን እንዲህ ያሉ አባት አልነበሩም:: በዘመናቸው እምነቱን ተከትሎ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ደም ፈሷል:: እሳቸው በተገኙበት ታቦት እየዞረ መስቀል አደባባይ አጠገብ ከሚገኘው እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ጥር 1 ቀን 1989 ዓ.ም በጥይት የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ የሚረሱ አይደሉም:: ከዚህ ሌላም እጅግ በሚያሣፍርና አንገት በሚያስደፋ መልኩ በዚህ ዘመን የፅላትና የቅርሳቅርስ ሽያጭ የተጧጧፈበት ዘመን ለመሆኑ ያደባባይ ምስጢር ነው:: ባንዳንድ አካባቢዎች ያላንዳች ማጋነን ሕንፃዎቻቸው ተገትረው እንደሆነ እንጂ ፅላቶቻቸው ከመንበራቸው

ውስጥ ስለመኖራቸው በቂ የሆነ ማረጋገጫ የለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ምዝበራና ቅሠጣ (ዘረፋ) እየተፈፀመ ባለባት አገርና ዘመን ተጋዳላይ ብሥራት አማረ በ1962-64 ዓ.ም ለሁለት ዓመት በንቡረዕድነት ማዕረግ አክሱም ፅዮንን ለማገልገል ከመሀል አገር የሄዱትን አዛውንት "ከሸዋ የሄዱ አማራ" በማለት ሲያብጠለጥላቸው ያሣፍራል፡፡ ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት መጥተው ቤተክርስቲያኗን የሠፈሩባትንስ በምን ቋንቋ እንግለፃቸው? እነሱ በየትም ቦታ ተዘዋውረውና ተንደላቀው ኮርተው፣ የበላይ ሆነው እንዲኖሩ እግዚአብሄር በልዩ ትእዛዝ ፈቅዶላቸው ይሆን? ወይንስ አቶ መለስ የወርቅ ዘር እንዳሉት ልዩ ክብር ሊገባቸው? ጠይቁ፡፡



*አማራን ከርሃብ ጋር ያነፃፀረው ብሥራት አማረ*

በመሠረቱ ሐረጉን ሲሰቡት ዛፉ እየተወዛወዘ እንጂ በተለይም ባባ ጳውሎስ ዙሪያ ብዙ ማለት ይቻል ነበር፡፡ ለምሳሌ ዓለማዊ ሕይወት ምን ያህል ይጣፍጣቸው እንደነበር ሌላው ማረጋገጫ ንዋይ ብቻ ሣይሆን ማዕረግም የማይጠቅማቸው ነበሩ፡፡ ይህንን ሀቅ ከጓድ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ማዕረግ ጋር እያነፃፀርን ማየት እንችላለን፡፡ በቅድሚያ የኮሎኔል መንግሥቱን እነሆ፡-

*ጓድ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ የኢሕዴሪ፣ ፕሬዚዳንት፣ ያብዮታዊት ጦር ጠቅላይ አዛዥ፣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የኢሠፓ ዋና ፀሐፊ፡፡ (18 ቃላት)*

*ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ፣ ቀዳማዊ ፓትሪያሪክ፣ ርእሳነ ሊቀጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት፣ የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣ የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም ክብር ፕሬዚዳንት፣ ዓለም ዓቀፍ የሰላም አምባሳደር (34 ቃት)*





እንግዲህ ይኸ ሁሉ የማዕረግ ዲሪቶ ላንድ አባት ምን ይፈይድ ነበር? እንደ እውነቱ ከሆነ ለክብርና ለፀጋ ከሆነ "ብፁእ" ይበቃቸው ነበር፡፡ ከብፁእነት የበለጠም ማዕረግና ክብር ሊኖር አይችልም፡፡ ይህንንስ የሕወሓት ሰዎች እንዴት ታዩት ይሆን? ከሁሉም የሚያሣዝነውና የሚያሣፍረው ደግሞ "የሸዋና የጎንደር አማራ "እያሉ ለመከፋፈል መሞከሩ ነው፡፡ ጎሠኝነት ከኤች.አይቪ የባሰ ክፉ ቫይረስ ነው የምለውም ለዚህ ነው፡፡

ተጋዳላይ ብሥራት አማረ ከንቡረእድ ኤርምያስ ከበደ ወጣ ይልና ደግሞ እንዲህ ይለናል፡-

*"ታላቁ የትግራይ ሕዝባዊ ንቅናቄ ተፀንሶ የተወለደው <u>ብልሹ በሆነው ያማራዊነት ፍልስፍና ተግባር ምክንያት እንደሆነ ርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ . . . ለትግራይ ሕዝብ የትግል ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያዊነት ባማራዊነት ለማጥመቅ የተደረገው ጥረት በቂ ማስረጃ ነው"</u>* (ሠረዝ የራሴ) *(እንደ ላይኛው ገጽ 27)*

ለመሆኑ አማራዊነት የሚባል ፍልስፍናም ነበር እንዴ? የሚገርም ነው፡፡ ነበር ከተባለ ደግሞ ዛሬ የትግሬዊነት ፍልስፍና ሠፍኗል ማለት ነው፡፡ ደግሞስ ምናለበት "የትግራይ ሕዝባዊ ንቅናቄ ተፀንሶ የተወለደው ብልሹ በሆነው አማራዊነት ፍልስፍና ነው" ከማለት ይልቅ "ብልሹ በሆነው ዘውዳዊው ሥርዓት ነው" ቢል ኖሮ ሁሉንም ያሣተፈ መሆን በቻለ ነበር፡፡ የተፈለገው ግን አማራ ላይ ማነጣጠር ነው፡፡ እውነቱም ይኸ ነው፡፡ ታዲያ ሕወሓቶች ያማራ ዘርን ለማፅዳት አልተንቀሳቀሱም ማለት ይቻላል? ጠይቁ፡፡ አማራ ባሪያ ፈንጋይም ሆኖ ቀርቧል፡፡ እነሆ፡-

*". . .የክርስትና ሃይማኖትን ካወቁ ጊዜ ጀምሮ አክሱማውያን ባርነትን የተቃወሙና ሌሎቹንም ያስተማሩ ሕዝቦች መሆናቸው ታሪክ ዘግቦታል፡፡. . . የሸዋ ገዥዎች ግን እስከ 20ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ ሩብ ዓመት ድረስ በባሪያ ንግድ ወንጀል ውስጥ ተዘፍቀዋል፡፡አክሱምንና ሰሎሞናዊ የዘር ሐረግ መናፈቃቸው ሌላው ቅዠትና ስህተት ነበር፡፡ አክሱም ለመሆን መወለድን ወይንም ባህሉን መከተል ወይንም ሁለቱንም መሆን ግድ ይላል" ይለንና አያይዞ "የባሪያ ንግድ የጥቁር አፍሪካውያን ሰብዓዊ ክብር ያዋረደ ታሪክ ነው፡፡ ታላቁ አክሱም ግን ከባሪያ ንግድ ውስጥ ከመሣተፍ መቆጠቧ . . . ክርስቲያን መሆን በባሪያ ንግድ አለመግባት ነው፡፡ የሸዋ ገዥዎች ግን ገቢ ለመሰብሰብ ባሳዘኝ ሁኔታ ባሪያ ነግደው የኢትዮጵያን ንጹሕ እጆች የማቆሸሸ ውጤት አስከትለዋል . . ." (እንደ ላይኛው ገጽ 31-32)*



*አማራን ከርሃብ ጋር ያነፃፀረው ብሥራት አማረ*

አፄ ምኒልክን ደግሞ እየዘረጠጠ እንዲህ ሲል ይዘልፋቸዋል:: *"የሀገር ፍቅር ስሜት የጎደለው ምኒልክ የኢትዮጵያን መሠረታዊ አንድነት ገዝግዞ በማበላሸት ያገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች ራሳቸውን ከሽያጭ እንዳይከላከሉና ማዕከሉን እንዲሸርሽሩ አድርጓል:: የቅኝ ግዛት ሥጋት ሳይኖርበት ለገንዘብና ሥልጣን ግዛቱንና ሕዝቡን ፈርሞ ለውጭ ኃይሎች የሸጠ መሪ ከምኒልክ በስተቀር በታሪክ አይገኝም:: . . ." (እንደ ላይኛው ገጽ 38)*

እውነት አፄ ምኒልክ ለውጭ ኃይሎች መሬት ሸጠዋል? ኢትዮጵያን አንድነት አበላሽተዋልን? እንዴት ነው ነገሩ ጎበዝ? ኧረ በርትታችሁ ጠይቁ:: ያስብን የባሕር በር፣ የጋንቤላ ለም መሬት መቸ ነው እየተቸበቸበ ያለው? እነዚህን አፄ ምኒልክ ናቸው እንዴ የሸጧቸው? አፄ ምኒልክ የውጫሌን ውል አንቀጽ 17ን አልቀበልም ብለው እስከነ ባለቤታቸው አድዋ ተራሮች ዘልቀው ጉርቦ ለጉርቦ ተናንቀው አንፀባራቂ ድል ያጎናፀፉ መሪ ነበሩ:: ይህንን አኩሪ ድል በርግጥ የሕወሓት ሰዎች አይቀበሉም፤ አያምኑም፤ ድሉን ቢያምኑም እንኳን ለራስ አሉላ ብቻ ነው የሚያሸክሟቸው:: እነሆ ብሥራት አማረ እንዲህ ይላል:-

*"ያድዋ ጦርነት የምኒልክን ታሪክ ትልቅ ሰው አስመስሎ አቅርቧል:: ኢትዮጵ <u>ብሔርተኛና ጀግና መሪ በምትፈልግበት ወቅት ያለቦታው</u> ምኒልክ ተገኘ:: ምኒልክ ወደደም ጠላ ያድዋ ጦርነት የማይቀር ታሪካዊ አጋጣሚ ነበር:: ምኒልክ ግዛቷ የተቀናነሰች አንስተኛ ኢትዮጵያን አፄ ብቻ ተብሎ ለመንግሥ እቅድ እንዳለው ጣሊያኖች ደርሰውበት ነበር:: <u>አዲሱ ታዛዣቸው አገሩን በማስከበር ረገድ እንደ ዮሐንስ አገር ወዳድ አለመሆኑን ተገንዝበዋል::</u> (ሥርዝ የራሴ) በምኒልክ <u>ፍርሃትና ስግብግብነት ተፈጥሮ ብቻ</u> አገሪቷን በቅኝ አገዛዛቸው ሥር ለማስገባት ያነሳሳቸው ስሌት ለውድቀትና ለሽንፈት ዳርጓቸዋል:: የራስ አሉላን በሕይወት መኖር ዘንግተዋል:: አሉላ ባይኖር ኖሮ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ትሆን ነበር:: . . ."* ይለናል::

ውድ አንባቢያን ጥላቻምኮ ልክና ገደብ አለው:: እውን አፄ ምኒልክ ፈሪና ስግብግብ ነበሩ? እውነት ያድዋ ድል የተገኘው በራስ አሉላ ብቻ ነው? ምን ዓይነት የበታችነትና የፍርሃት ምንጭ ነው ብሥራት አማረን የተጠናወተው? እውነት እንነጋገር ከተባለ ያድዋ ድል የሁሉም ጀግኖች ቅንብር ውጤት እንጂ የራስ አሉላ ቀርቶ ያፄ ምኒልክ ብቻም አይደለም:: በመጀመሪያ ደረጃ የሕወሓት ሰዎች የዘር ሐረግ እንሳብ ካላሉ በስተቀር በራስ አሉላ ጀግንነት የመመካትም ሆነ የመኩራት የሞራል ብቃት





ሊኖራቸው አይችልም:: የብሥራት አማረ ትረካም የቅጥፈቶች ሁሉ ቁንጮ ነው::

በርግጥ ራስ አሉላ አባ ነጋ ባድዋው ዘመቻ ወቅት ከነበሩት ስመ ጥር ጀግኖች መሀከል አንዱ እንደነበሩ ይህንን ሀቅ የሚክድ ኢትዮጵያዊ የለም:: በራስ አሉላ ጀግንነትም የማይኮራ ኢትዮጵያዊ የለም:: የሚያስገርመው ግን ራስ አሉላ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው!" ያሉትን አንፀባራቂ መርህና መፈክር ወይንም ሕያው ቃል ጥላሸት ቀብተው "እበት ትል ይወልዳል!" እንዲሉ ተጋዳላይ ብሥራትና ድርጅቱ (ሕወሓት) ኤርትራን ተዋግተው አሥገንጥለው በራስ አሉላ ጀግንነት ለመደበቅ መሞከር ሰብቅ ነው:: እንዲያው ለመሆኑ አፄ ዮሐንስንና ራስ አሉላን ለማወደስና ለማሞገስ አፄ ምኒልክ መሰደብና መዋረድ አለባቸው? የትግራይን ሕዝብ "ታላቅና የወርቅ ዘር" ለማለት ያማራ ሕዝብ ማነስና በጨርቅ መመሰልስ አለበት? ኧረ ልናላምጥ የምንችለውን፣ እንጉረስ:: ለማንኛውም ስድቡ ይቀጥላል::

*"የምኒልክንና የሌሎችን የዘር ሐረግ የማጠናው ለዘመናችን ትክክለኛ እሴት ስለማይበት ሳይሆን ታሪክ በምኒልክና በሌሎች የውርስ ይገባኛል ጥያቄዎች የደረሰበትን መዛባት ለማቃናት ነው:: ምኒልክ የኃይለ መለኮት ሣሕለሰላሴ ዲቃላ ልጅ ነበር . . ." (እንደ ላይኛው ገጽ 37)*

ይህ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም የነጋሢ ዘሮች እኛ ነን:: ምኒልክ ዲቃላ ነው:: የነጋሢ ዘር ወይንም የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ብቃይ አይደለም ለማለት ነው:: የዘውዱ ሥርዓትኮ ከቀ.ኃ.ሥ በኋላ ያከተመ መሠለኝ:: አለ እንዴ? አጅሬ ሕወሓትኮ ሥልጣኑን በሥውር በዘውድ ስም ይዞት ይሆናል? ለዚህ ሣይሆን ይቀራል? ምርጫ በመጣ ቁጥር የሚይዘውን የሚጨብጠውን የሚያጣው::

ተጋዳላይ ብሥራት አማረ ያድዋን ድል የትግራይ ሕዝብ ብቻ ድልና ገድል አድርጎ የተረከባትን ደግሞ እነሆ:- *". . .እስከ ዛሬ ምንነቱ ባልታወቀ በሽታ እያንዳንዱን የቀንድ ከብት እንዳለ አለቀ:: ከኢጣሊያ እቅድ መመንጨቱንም የሚጠራጠሩ አሉ:: (በሽታውን ማለቱ ነው) . . .ይህ እቅድ አፍሪካውያንን በበታችነት ከሚቆጥሩ ያውሮፓ ኃያላን አገራት ኢጣሊያንን በመቋቋም ባሳየው ቆራጥ ድፍረት የትግራይን ሕዝብ ለመቅጣት የታቀደ እንደነበር የሚያምኑ በርካታ ናቸው" (እንደላይኛው ገጽ 39-40)*

ልብ እንበል ወገን ብሥራት አማረ ቀደም ሲል "ያድዋ ድል የተገኘው በራስ አሉላ አማካኝነት ነው:: ራስ አሉላ በሕይወት ባይኖሩ ኖሮ ኢትዮጵያ

በኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ሥር ትወድቅ ነበር" ሲል በድፍረት ነግሮናል፡፡ አሁን ደግሞ ከዚያው ሣይወጣ ድሉን ለትግራይ ሕዝብ ብቻ ያሸከምና ለዚህ በቀል መልስ የሚሆን ኢጣሊያ የትግራይን ሕዝብ የብቻ ለመቅጣት ስትል የቀንድ ከብቶችን በመደዳ የሚጨርስ በሽታ በመልቀቅ ተበቀለች ይለናል፡፡

በመሠረቱ ብሥራት አማረ ያልታወቀ በሽታ የሚለው የታወቀና በየታሪኩ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ መቅሰፍትም ለትግራይ ሕዝብ ብቻ የመጣ ሣይሆን መላ ኢትዮጵያን የሸፈነ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን አጠራርም "ጅል ቀን ወይንም ክፉ ቀን" እየተባለ የሚጠራው ነው፡፡ በዚህ ክፉ ቀን ጊዜም አንዲት እናት የሌሎችን ልጆች ስትበላ ሌላዋ እናት ደግሞ የገዛ ልጇን በልታለች፡፡ ከርሃቡ ወይንም ከጠኔው ብርታት የተነሣም ሊበሉ የማይገባቸው እፅዋት' ሥራሥሮችና ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ተበልተዋል፡፡ የርሃቡን አግባብና ክስተት "ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሰ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" በተባለው መጽሐፋቸው ጸሐፊ ትእዛዝ ገ/ሥላሴ እንዲህ ሲሉ ዘግበውታል፡-

*"ክረምቱን በዘመነ ማቴዎስ ላሙ፣ በሬው፣ አልቆ እንግዳ ነገር ስለሆነ ሰውም መቆፈሩን ትቶ በዝና ነበርና በዘመነ ማርቆስ (በቀጣዩ ዓመት ለማለት ነው) ዳር እስከ ዳር ጽኑ ርሃብ ሆነ. . ."* በማለት ዝርዝር ታሪኩን ዘግበውታል (ገጽ 175 -76) ይህንኑ ዋቢ በመጥቀስ እውቁ የታሪክ ተመራማሪ ሪቻርድ ፓንክረስት "The Ethiopian Royal chronicles" በተባለው መጽሐፋቸው በገጽ 172 ላይ በስፋት አስፍረውት ይገኛል።

በዚህ አጋጣሚ ይልቅ አንድ ቁም ነገር ጣል አድርጎ ማለፍ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ይኸውም ስለ ቁርጥ እንጀራ ታሪካዊ አመጣጥ ስንቶቻችን እናውቅ ይሆን? እንጀራን እየቆራረጡ ጠቅልሎ ወይንም ሸምልሎ በወግ በማዕረግ በሠርግም ሆነ በሌላ አጋጣሚ ወይንም በቤት ውስጥም ቢሆን በነፍስ ወከፍ ሳህን ይዞ ለየራስ መመገብ ዛሬ ባገራችን የተለመደና ባህል እየሆነ መጥቷል፡፡ ላያያዝም ሆነ ላቀራረብ ቀልጣፋ በመሆኑ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሣይቀር ተወዳጅ ሆኗል፡፡ ይህንን እንጀራ እየቆራረጡ ጠቅልሎ ለየራስ አንጠልጥሎ መብላት የእድሜ ባለጸጎች አይወዱትም፡፡ "ችጋር ጠሪ ነው" ይሉታል፡፡ ይህንን ሲሉ ከምንም ተነስተው አይደለም፡፡ "ክፉ ቀንን ወይንም ጅል ቀንን" ስለሚያስታውሳቸው ነው፡፡ ታሪካዊ አመጣጡ እንዲህ ነው፡፡

በዚያ ክፉ ርሃብ በገባበት ጊዜ ሕዝቡ ቁራሽ ፍለጋ ወደ ቤተ መንግሥት ወይንም ወደ እንጦጦ ያነዬ የንጉሡ ነገሥቱ መቀመጫ እንጦጦ ስለነበር





ርሃብተኛው ወደዚያው ይጎርፍ ጀመር፡፡ እናም እቴጌ ጣይቱ በመጀመሪያ በነፍስ ወከፍ አንዳንድ እንጀራ ለማዳረስ ሞከሩ፡፡ በኋላ ግን የርሃብተኛው ቁጥር ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ አንዳንድ እንጀራ ላንድ ላንድ ወይንም በነፍስ ወከፍ መስጠቱ ይቀርና ለሕይወት ማቆያ ያህል አንዷን እንጀራ ካራትና ካምስት በመቆራረስ እየጠቀለሉ መስጠት ተጀመረ፡፡ ይህንኑ ሂደት ሪቻርድ ባንክረስት ዘግበውት ይገኛል፡፡ እንግዲህ የቁርጥ እንጀራ ታሪካዊ አመጣጥ ጅል ቀን ወይንም ክፉ ቀን ነበር፡፡

እንግዲህ ስለ ቁርጥ እንጀራ ይህን ያህል ካልን ወደ ተጋዳላይ ብሥራት አማረ ዘለፋ እንመለስና የሚለንን እንመልከት፡፡ ብሥራት አማረ ታላቁን የትግራይ ሕዝብ ምንነቱ ያልታወቀ የቀንድ ከፍት በሽታ ገብቶ የብቻው ነጥሎ ማጥቃቱን ወይንም በርሃቡ የትግራይ ሕዝብ ብቻ መጎዳቱን ከተረከልን በኋላ ይቀጥልና የትግራይ ሕዝብ ጠላቶች ርሃብና በምኒልክ መሪነት አማራዎች ናቸው በማለት እንዲህ ይለናል፡-

*". . .ወቅቱ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ክፉ ዘመን ነበር፡፡ <u>ተፈጥሮም ከጠላት ጋር በማበር ጠላት የተባለው አማራ መሆኑን ልብ እንበል፡፡ ከዳቻቸው</u> . . ."* (ሠረዝ የራሴ) ይለንና ቀጠል አድርጎ *"ምኒልክ ለተከታዮቹ ትውልዶች ያስተላለፈው ሌላው የጥፋት ትእይንት የካሂዲነት ባህሪ ብቻ ሳይሆን ፈሪነትንም ጭምር ነው፡፡" (እንደላይኛው ገጽ 40)*

እንዴት ነው ነገሩ ጎበዝ፤ ልክ እንደ ታላቅነት የፈሪነትም መስፈርቱና ሚዛኑ ግራ የሚያጋባ ሆነ፡፡ አገር ተዋግቶ ያስገነጠለና የባሕር በር የዘጋና ያዘጋ "ታላቅ" አድዋ ተራሮች ዘልቆ ጣሊያንን ውሃ ውሃ አሠኝቶ ያባረረ "ፈሪ!" ኸረ ጠይቁ፡፡ በነገራችን ላይ ይኸ "ታላቅ ታላቅ!" የሚለው ቃል መነሻው ሩቅ ነው፡፡ ካቶ መለስ እልፈት ጋር ብቅ ያለ መስሎኝ ነበር፡፡ እንደ ብሥራት አማረ አተራረክ ከሆነ የሕወሓት ያፍ መፍቻ ቋንቋ ሆኖ "ታላቋ ኤርትራ! ታላቋ ትግራይ!" ከነዚህ ከተጠቀሱት ራቅ ሲባል ደግሞ ዛሬ ፀሐይ የደበዘዘባት ያነዬ ያልጠለቀባት "ታላቋ ብርታኒያ!" ነበረች፡፡ እንግዲህ ሕወሓትና ሻዕቢያ የሷ አርማ ወራሾች መሆናቸው ነው፡፡ ሶማሊያም ባለ አምስት ኮከብ አርማ ከባንዲራዋ ላይ አስቀምጣ "ታላቋ ሶማሊያ" ትል ነበር፡፡ ዛሬ ወደ መንደሮች ወረደች፡፡

ከዚህ ላይ ግን ሊተኮርበትና ሊሠመርበት የሚገባው ቁምነገር እንዴት ነው ከሕወሓት ሰዎች ጋር እንደ ዜጋ አብሮ መኖር የሚቻለው? አንድን ሕዝብ ከሌሎቹ ነጥለው መጥላታቸውና ማሣደዳቸው ሲገርመን ብሥራት

አማረ ከርሃብ ጋር አነፃፅሮ "የትግራይ ጠላቶች ሁለት ናቸው፡፡ ተፈጥሮና (ድርቅ ወይንም በሽታ) ጠላት (በምኒልክ የሚመራ አማራ ነው)" ማለቱ በምን ቃል መግለጽ ይቻላል? እውን ያማራ ሕዝብ ለትግራይ ሕዝብ የርሃብን ያህል የከፋ ጠላት ነው? እውን አማራን ርሃብ ነክቶት አያውቅም? ታሪክ ይፍረድ እንዳንል ታሪክን የሚደፈጥጡ እንጂ ለታሪክ ክብር የሚሰጡ አይደሉም፡፡ ሥግነት ይፍረድ እንዳንል ሥግነትን አያውቁም፡፡ ምን ይሻላል ጎበዝ? እስቲ ጠይቁ፡፡

ብሥራት አማረ *"በትግራይ የሁለቱ ወያኔዎች አብዮቶች (ቀዳማይና ያሁኑ ወያኔ ለማለት ነው) መነሳት ምክንያት ምኒልክ አስቀድሞ ለሠራው ከህደት ቀጥተኛ መልስና ውጤት ነው"* ካለን በኋላ አያይዞ አንድ የትግራይ አዛውንት ምናልባትም ከመጽሐፉ የፊት ሽፋን ኋላ ቀር ጠመንጃ አንግተው፣ ዝናራቸውን ታጥቀው ካጠገባቸው የመገናኛ ሬዲዮ ይዞ ለቆመው ወጣት ተጋዳላይ እጃቸውን በርቀት በመዘርጋት ባመልካች ጣታቸው አሻግረው "ያውና ያማራዎች አገር" በሚል በሚመስል መከረው ሲያስናብቷቸው እንዲህ አሏቸው ይለናል፡-

*"ኢትዮጵያ የናንተ ናት፡፡ አሁን የሚያቆማችሁ ኃይል የለም፡፡ ልጆቻችን ከነሱ ይበልጥ ጠቢብና አሳቢ እንደሆናችሁ የንጉሥ ምኒልክ ሰዎች አሁን ይማራሉ፡፡ እናንተን ለማሸነፍም ሆነ ለማስቆም የሞራል ብቃት የላቸውም፡፡ ትግራይ አንደዬም ተሸንፎ አያውቅም* (ሠረዝ የራሴ) . . . !" *(እንደላይኛው ገጽ 41)*

ይኸ ከባድ ፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ እውነት የትግራይ ሕዝብ አንደየም ተሸንፎ አያውቅም? ሲሸነፍ የኖረው ታዲያ የትኛው ሕዝብ ነው? የትግራይ ሕዝብ አንድም ጊዜ ካልተሸነፈ አፄ ዮሐንስ መተማ ላይ ድል የሆኑት ማንን ይዘው ዘምተው ነው? በዚህ ሥልጡን ዘመንስ አንዱን ብሔር ጀግና ሌላውን ፈሪና ተሸናፊ አድርጎ የዘር መርዝ መርጨት ምን ዓይነት የፍርሃት ምንጭ ነው? ለመሆኑ ለነብሥራት አማረ አማራ ቅዠት የሆናቸው ለምንድን ነው? እንዲህ ዓይነት መመፃደቅስ ለምን አስፈለገ? ባንድ ወቅት የጎበዝ ወይንም ኃያል የሆነ በሌላ ጊዜ ሊኮስስ ይችላል፡፡ የበረቱ ይደከማሉ፣ የደከሙ ደግሞ ይበረታሉ፡፡ ዛሬ በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች "ሚች አውሬ ገዳዩን ያስመሰግናል" እንዲሉ የትግራይ ልጆች ጎብዘው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገ ደግሞ ሊኮስሱ ይችላሉ፡፡ ደግሞምኮ ፍልሚያው የስበስ በመሆኑ ይህን ያህል የሚያኩራራ አይመስለኝም፡፡ "የላም አሸናፊ መሆንም" ያሳፍራል፡፡ ደግነቱ ሀፍረትን አያውቁም፡፡






በመሠረቱ የብሥራት አማረን መጽሐፍ ከዚህ ባለፈ ማየት ሕመም መሥረቅ ነው፡፡ የዜግነት ርሾንም ጨርሰን ልናሟጥጥ እንችላለን፡፡ እስቲ ደግሞ ቀጥለን የሱ ቢጤዎች የሚሉንን እንያቸው፡፡ ብሥራት አማረ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ በድል አድራጊነት ሲገባ የሰላምና መረጋጋት የፀጥታና አሥተዳደር አስተባባሪ ሆኖ ማገልገሉን ይገልጽና ትኩስ እንጀራ በቅጡ ሳይበላ ወይንም የድሉን ፍሬ ሳያጣጥም በ1984 ዓ.ም የመንግሥት ሥራ ለቆ በስደት ወደ አሜሪካን አገር መሄዱን ሲነግረን ለምንና በምን ምክንያት እንደተሰደደ ግን አልነገረንም፡፡ ለምን ስደትን መረጠ? ከነማንስ ጋር ተጋጭቶ ይሆን? ምናልባት በሰላምና መረጋጋት ስም ስንቶቹን ቀንበጦች በልቷቸው ይሆን? ልጆቻችሁ፣ ባሎቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ እንደ ወጡ የቀሩባችሁ ጠይቁ፡፡ በተረፈ ከተጋዳላይ ብሥራት አማረ ወደ ተስፋዬ ገብረአብ ስንሸጋገር ደግሞ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

ተስፋዬ ገብረአብ ኤርትራዊ ነው፡፡ ግን ደግሞ ተወልዶ ያደገው ደብረዘይት ያዳን ጤፍ እየበላ ነው፡፡ "የናት ጡት ነካሽ" እንዲሉ ወይንም የዘር ልጓም ስቦት እሱም የድርሻውን እንዲህ ይለናል፡-

*"ነፍጠኞች አቡቢንቲ የተባለ ሽቶ አንድ ብር ይሸጡልንና እነሱ ግን ሦስት እንቁላሎችን ባምሳንቲም ይገዛሉ፡፡ ወተትና እንጀራ መሸጥ በኦሮሞ ነውር ነው፡፡ እነሱ ግን አንድ እንጀራ መሸጥ ጀምረዋል፡፡ ይኸ ነው ሥልጣኔ፣ ቁንዲፍቱ መጥመቅ የኦሮሞ አይደለም፣ የሰው ሚስት መወሸም የኦሮሞ ባህል አይደለም፡፡ ነፍጠኞች ባህላችንን አቆሸሹት፣ መሬታችንን ነጠቁን፡፡ . . . ምኒልክ የተባለው ስግብግብ ይህን ሀብታም መሬት ሲያይ ጎመጀ፡፡. . ." (የቡርቃ ዝምታ ገጽ 93)*

የምኒልክ ጥላ ሞት ወይንም አፅም ወይንም የሙት መንፈስ ከትንሽ እስከ ትልቅ ለምን እንደሚያሸብራቸው አይገባኝም፡፡ የሚገርም ነው፡፡ ነፍጠኛውስ ቁንዲፍቱ ማውጣት አስተማራቸው፡፡ ዛሬ ኢሕአዴግ ቢራ ጠመቃ ይሆን ያሠለጠናቸው? ኧረ የሰው ሚስት መወሸምም በሌላውም ነውር ነው፡፡ ያማራም ባህል አይደለም፡፡ እንዲያውም ሥርዓተ ቁርባን አለ፡፡ ከቴ ለምን ይሆን አማራና ኦሮሞን ለማስተራረድ የሕወሓት ካድሬዎች ተግተው የሚሠሩት? እስቲ ጠይቁ፡፡

በመሠረቱ ተስፋዬ ገብረአብ እንኳን ላማራዎችና ለራሱ ወገኖች የሚታመን አይደለም፡፡ ከሃዲ ነው፡፡ ስለምኒልክና ስለነፍጠኝነት ብዙ ብሏል፡፡ ዛሬም በስደት ሆኖ እየጻፈ ነው፡፡ በሽታ ነውና ስላማራ መቸም ይጽፋል፡፡ እስቲ ደግሞ ትልልቆቹ ተጋዳላዮች ስላማራ ህዝብ ምን ይላሉ? ቀጥለን እንመልከት፡፡



*የህግ ባለሙያው አቶ ሙሉጌታ በሪሁን*

ወገን የጀኔራል ሣሞራ ንግግር አያማችሁም? ልብ አንበል ጀኔራል ሣሞራ የኢትዮጵያ የመከለከያ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ተብለው የተቀመጡ ናቸው:: ግን ደግሞ ከ85 ብሔር ብሔረሰቦች መሀከል አንዱን (አማራን) መርጠው ወይንም ነጥለው "አማራን እንዳያንሠራራ አድርገን አጥፍተነዋል!" በማለት ባዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰበ ሕዝብ ያደረጉት ንግግር አስደንጋጭና አሳሳቢ ነው:: እንቅልፍ የሚያስተኛም አይደለም:: የሕወሓት ሰዎች ምን እየሠሩና ምን እየቀበሩ እንዳሉ ደግማችሁ ደጋግማችሁ ጠይቁ:: አንዳንድ ጊዜ ልብ ብላችሁ አጢናችሁ ከሆነ የንፁሐን ደም እየተከተለ የሕሊና ሰላም የሚነሳቸው ይመስላሉ::

አማራ በዚህ ዘመን ጫካ ገብቶ ጥይት ተኩሶ አንድ ተጋዳላይ ሳይገልባቸው ይህን ያህል በመንፈሱ ለምን እንደሚሸበሩ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው:: ይህንንም ጠይቁ::

ባማራ ሕዝብ አንድ የጠነከረ ባህል አለ:: "ለልጅ ከፉ ነገር አይነገርም" ይባላል:: ይህ መልካም ነገር ነው:: ከፉ ሥራ ቢሠራ እንኳን በጊዜው ይወቃቀሱበታል እንጂ ካለፈ በኋላ አይነሳም:: በጣም ነውር ነው:: ቁርሾና በቀሉ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍ ጥንቃቄ ይደረጋል:: ከልጆች ፊት አይነሳም:: "እሱን ነገር እርሱት፤ አታንሱት፤ በቃኮ አለፈ" እየተባለ ይደበቃል:: ወይንም እንደሞተ ይቆጠራል:: አሁን ግን አበጥሮ መነጋገሩ የግድ እየሆነ መጥቷል:: ከእንግዲህ በደረቅ ፕሮፓጋንዳ እየተቋሰሉ አብሮ





መኖር ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ቁስሎቻችንና እባጮቻችን ሊፈርጡና ሊሽሩ የሚችሉት እውነቱን አውቀን መወቃቀስ ስንችል ብቻ ነው:: አለበዚያ እንደብሥራት አማረ የፈጠራ ታሪክ እየጻፍን አንድን ሕዝብ ከርሃብ ጋር እያነፃፀርን ጥላሸት የምንቀባ ከሆነ ሌላ ከፉ ብጉንጅ እያሳበጥን መሆናችንን ልናውቅ ይገባናል:: የሕወሓት ሰዎች በየጉያችን እባጭ እያስታቀፉን መሆናቸውን እያንዳንዱ ዜጋ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ሌላው የሕወሓት ተጋዳላይ ያስታቀፈንን እባጭ (ብጉንጅ) ደግሞ እነሆ:-

## እናት ሲመታ እግር መቆም አይችልም!

የሕወሓት ሰዎች ወደፊት እንደምናየው ያማራ ወጣቶችን ለመብታቸው ሲሟገቱ፣ ሌላው ቀርቶ የሚፈፀምባቸውን ግፍ ለመናገር እንኳን እንዳይችሉ "ፊት የደረሰን አዝመራ ወፍ ይበላዋል" እንዲሉ እናት እናታቸውን በመቀጥቀጥ ሌሎች በእግራቸው ቆመው እንዳይሄዱ ፖሊዮ እንደያዘው ሽምድምድ ወይንም ልፍስፍስ ትውልድን ማፍራት ሆኗል:: የፖለቲካ ጫወታውንም ልብ ብሎ ላጤነ ሰው እንደ ዱላ ቅብብሎሽ ጨዋታ ዓይነት ነው:: ይህንን ያልተገነዘብነውና ያልተረዳነው የነሱን ትርፍራፊ የምንለቃቅመው ብቻ ነን:: ለማንኛውም አንዱ ተጋዳላይ ከዚሁ አዲስ አበባ አብነት ሠፈር የድርሻውን ካዛውንቶቹ ተጋዳላዮች ተቀብሎ ጥላቻውን በሚገባ ገልጿል::

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ሐሳባቸውን እንድናወጣላቸው ግለሰቦች ይጽፉልናል:: የዚህ ተጋዳላይ ደብዳቤዎችም ከጄ የገቡት በዚህ ወቅት ነበር:: ለማንኛውም የመጀመሪያው ደብዳቤ እንዲህ ይላል:-

"ወቅቱ የወያኔ ሠራዊት የደርግን ሠራዊት እየጠረረገ ወደ አዲስ አበባ ቀርቧል:: በቅድሚያ ግን ትግሬና ወያኔ ያንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ስለሆኑ ትግሬ ስል ወያኔ፣ ወያኔ ስልም ትግሬ ማለቴ እንደሆነ ይታወቅልኝ" ሲል አስቀድሞ ይነግረናል:: ለኔ ግን ወያኔዎችና ትግሬዎች የተለያዩ አድርጌ ነው የምወስዳቸው:: በርግጥ ወያኔዎች የትግራይ ሕዝብ ልጆች መሆናቸው ይታወቃል:: የትግራይን ሕዝብ በመደዳ ግን"ትግሬ ማለት ወያኔ፤ ወያኔ ማለት ትግሬ" ብሎ መበየን ትክክል አይመስለኝም:: አንድ ሕዝብ በጅምላ በምንም መመዘኛ በፋኖ ስም አይፈረጅም:: ለማንኛውም አማራን የኮነነበትን ጽሑፉን እነሆ:-



የህግ ባለሙያው አቶ ሙሉጌታ በሪሁን

"<አማራና ረቂቅ ተንኮሎቹ፤> በሚል ርእስ በጋዜጣችሁ ባታወጡትም ባለፈው ደብዳቤዬ ስላማራ እኩይ ማንነትና ስለ ሕወሓት የመጨረሻ ግብ ጽፌላችሁ ነበር፡፡ ለነገሩ አመለካከታችሁን የሚንድ ጽሑፍ እንዴት ልታወጡ ትችላላችሁ?" ሲል ዝግጅት ክፍሉንም ወርፎታል፡፡ የሆነ ሆኖ "አማራና ረቂቅ ተንኮሎቹ" የሚለውን እንይለት፡-

"1ኛ. <ወጋ ነቀል> ዐማራ በነገር ጠቅ አድርጎ ለማፅናናት ይሞክራል፡፡ ወጋ ነቀል በየትም ብሔር የሌለ ያማራ እኩይ መታወቂያ ነው፡፡

2ኛ. <አሽሙረኛ> ዐማራ በቀጥታ ከመናገር ይልቅ አስመስሎ መዝለፍ ወይንም መሰደብ ይቀናዋል፡፡

3ኛ. <እየሳቀ ሰውን ይገላል> ዐማራ ጥላቻውን በውስጡ ቀብሮ ውጫዊውን ገጽታውን እንደፈንዲሻ ያፈካል፡፡ ትግሬ ግን ያማራ ተቃራኒ ነው፡፡ ንዴቱን፣ ጥላቻውን፣ ባጠቃላይ የውስጥ ማንነቱን በፊቱ ላይ ይነበባል፡፡ የሚያሣዝነው ግን ሰው የሚወደው እየሣቀ የሚጎዳውን ነው. . ." ይለናል፡፡ ሌሎቹን ብሔረሰቦችም ትግሬን (ግልፁን) ጠልታችሁ (ድብቁን) ወይንም እየሳቀ የሚገላችሁን አማራን ትወዳላችሁ ሲልም ወቅሷል፡፡

ሌላው የዚህ ተጋዳላይ ጽሑፍ <የሕወሓት የመጨረሻ ግብ!> በሚል ርእስ "ትግሬ በሁሉም ብሔረሰቦች እጅግ በጣም የተጠላ ብሔር ነው፡፡ ትግሬን የሚወድ አንድም ብሔረሰብ የለም፡፡ የትግሬ ሕዝብ የሚጠላው በትግሬነቱ ብቻ ነው፡፡ ትግሬ ሆኖ ጥሩ ከመሆን የሌላ ብሔር ተወላጅ ሆኖ ከፉ መሆን ያስወድዳል፡፡ አንድ ሕዝብ በማንነቱ የሚጠላ ከሆነ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር እንዴት አብሮ መኖር ይችላል?" በማለት ይጠይቅና "ሕወሓት ይህንን ስለሚያውቅ የመጨረሻ ግቡ ትግራይን ገንጥሎ መኖር ነው፡፡ የሕወሓትን ሐሳብ እደግፋለሁ፡፡ በትግሬነቴ የምጠላ ከሆነ ተገንጥዬ መኖርን መቶ በመቶ እመርጣለሁ፡፡" የጥቅሱ መጨረሻ፡፡

ይህ ተጋዳላይ ከራሱም ጋር የተጣላ ይመስለኛል፡፡ አንድ ሰው በግል ምግባሩ ሊጠላ ይችላል፡፡ አንድ ሕዝብ ግን በጅምላ ሲጠላ አይቼም ሆነ ሰምቼ አላውቅም፡፡ "ከፉ ሰዎችን የገዛ ጥላቻው እየተከተለ ያሣድዳቸዋል" የሚባለው እንደ ሕወሓት አባላት ያሉትን ነው፡፡ ለመሆኑ የትግራይን ሕዝብ በጅምላ ወይንም በመደዳ ሌላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ስለመጥላቱ የመለኪያ መሥፈርቱ ምንድን ነው? ይህ ተጋዳላይ የራሱ ፍርሃትና ጭንቀት ወይንም እሱ በሌሎች ሕዝቦች ላይ ያለውን ጥላቻ የፈጠረበት የፍርሃት ድፍቀት





እንጂ የትግራይን ሕዝብ በመደዳ የሚጠላ አንድም ዜጋ የለም፡፡ በርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ሕዝብ ጭምር ከሌሎች ወንድሞቹ ሊነጥለው የሚታገለውን ሕወሓትን አይወድም፡፡ ይህ ተጋዳላይም ከትግራይ ሕዝብ እንደ ሕወሓት ለመሸንጥ ስለሚፈልግ "ወያኔ ስል ትግሬ ትግሬ ስልም ወያኔ ማለቴ ነው" ሲል ገና ከመግቢያው ላይ ሊያስተዋውቀን ሞክሯል፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፡፡

## "ሆዱ ጩቤ አፉ ቅቤ!"

". . .ባንዳንድ አካባቢዎች ‹እናንተ የዚህ ብሔረሰብ አባል ናችሁ (አማራዎችን ለማለት ነው) ይህንን አካባቢ ለቃችሁ ውጡ› እየተባሉ ነው" ተብሎ ገና ከማለዳው ለጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

". . .እኛ ዋንኛውን ያማራ ሕዝብ በወሬ አይደለም፣ በሩቅም አይደለም የምናውቀው፤ አርሶ አደር ነው፡፡ ያማራ አርሶ አደር እኛ በተግባር ነው የምናውቀው፡፡ ከኛ ጎን ተሰልፎ ሲዋጋ፣ ስንቅ ሲሠንቅልን ነው የምናውቀው፡፡ ጎጀውን እናውቃታለን፡፡ . . . ምን ዓይነት እንጀራ እንዳለው እኛ እናውቃለን፡፡ ከማንም በተሻለ ሁኔታ አድልኦ የለውም፡፡ ስለዚህ ያንን ሕዝብ እንደ ሕዝብ ጠላት የሚወስድ ካለ ያ ዘረኛ ነው!"

ጠ/ሚንስትሩ ይህንን የተናገሩት በ1983 ዓ.ም ሥልጣን ላይ እንደወጡ ነበር፡፡ ይህ ወቅት ደግሞ አነግ ያማራ ዜጎችን "ከክልሌ ውጡ" እያለ ያምስ የነበረበት ወቅት ነበር፡፡ በመሆኑም የጠ/ሚንስትሩ ንግግር መልካምና ካንድ መሪ የሚጠበቅ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ወደ ውስጥ ስንገባና ከዚያ በኋላ እስካሁንም ድረስ ባማራ ሕዝብ ላይ የተወሰዱትንና በመወሰድ ላይ ያሉትን ርምጃዎች ስናጤን የጠ/ሚንስትሩ ንግግር "ሆዱ ጩቤ አፉ ቅቤ!" እንደሚባለው ዓይነት ናቸው፡፡

እውነት ነው፤ ያማራ ሕዝብ ከደርግ ወታደሮች እየደበቀ እያበላና እያጠጣ፣ የሚሄዱበትን ሥርጣስርጥና የቅርቅፍት መንገዶች እያመላከተ አዲስ አበባ እስከሚደርሱ ድረስ አሳልፏቸው ነበር፡፡ እነ አጅሬ ግን "አፉ ቅቤ ሆዱ ጩቤዎች ናቸውና" መልሰው መኗሪያ አሣጥተው ያሳድዱት ጀመር፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ ሀቅ አስቀምጬ ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡ እንዲህ ነው፡-

በቀድሞው አጠራር ጎንደር ክ/ሀገር ቆላማ አካባቢ የወያኔ ታጣቂዎች ወይንም ፋኖች ውሃ ይጠማቸውና ካንድ መንደር ውስጥ ገብተው ውሃ እንዲሠጧቸው ይለምናሉ:: ይሰጧቸዋል:: ተጋዳላዮቹ ከጠጡ በኋላ ሣንቲም አውጥተው የውሃውን ዋጋ እንክፈላችሁ ይላሉ::

"እንዴ! ጥሩ ውሃኮ ነው የሠጠናችሁት፤ ጠላ አይደለምኮ" ይላሉ በመገረም ሴቶቹ::

"ጥሩ ውሃ ቢሆንም፤ ወንዝ ወርዳችሁ አይደል የምትቀዱት? የጉልበታችሁን ዋጋ መክፈል አለብን:: አለበለዚያማ እንደ ደርግ ወታደሮች ዘራፊዎች መሆናችን ነው!" በማለት ይገለገላሉ::

"ቢሆንም እኛ ለጥሩ ውሃ ሣንቲም አንቀበልም" በማለት ሴቶቹ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተጋዳላዮቹ መራርቀው "አፉ ቅቤ ሆዱ ጩቤ" ፕሮፓጋንዳቸውንም ነዝተው ሄደዋል:: ካንጀት ቢሆን ኖሮ ያ ሁሉ ትህትናና ለወገን አሣቢነት አዲስ አበባ ሲገቡ በኖ ባልጠፋ ነበር:: "ጅብ እስቲነከስ ያነከስ ነውና!" አዲስ አበባ ገብተው ሲደላደሉ ግን ያማራን ዜጋ መኗሪያ አሣጥተው ባላሳደዱት ነበር::

እንግዲህ እስካሁን ለማስቃኘት የሞከርኩት የጎሰኝነት ሥርዓት ምን ያህል ጨካኝና አድሏዊ መሆኑን ነው:: ጎሰኝነት የኔ ከሚላቸው ጎሣዎች በስተቀር በዚች አገር ላይ ሌሎቹን እንዲኖሩ አይፈቅድም:: አቅም ካለው ማጥፋት ነው:: አቅም ካጣና የጊዜው ሁኔታ የማይፈቅድለት ከሆነ ደግሞ የሱ የበታች ሆነው ተሸቆጥቁጠው፣ ሰብአዊ ክብራቸው ተገፎ በጢሰኛ ወግ ዝቅ ሲልም በእንስሳ ወግ መኖር ነው:: ይህንን ሀቅ ባማራ ሕዝብ ላይ የሚወሰደው ርምጃ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል:: የኦሮሞው ዜጋችንም ከዛፍ ዛፍ እንደሚዘል ጉሬዛ በገዛ ቀየው ካብራኩ የወጡ ጀሌዎች ሲያዘልሉት እያስተዋልን ነው::

"በብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃና ዳንኪራ" ስም ወይንም ጥቁር መጋረጃ ጎሰኝነት ተከልሎ አገር እያጠፋ መሆኑን ዜጎች ልብ ልንል ይገባናል:: እስከ መቸስ አንዱ ጎሳ የሌላው ጎሳ ጠላት ተብሎ እስበሳችን እንደ ዶሮ አውራዎች እየተተካተክን እንኖራለን? ዐላየሁም፣ አልሠማሁም፣ አልናገርም ከምንልበት ጊዜ ላይ አይደለንም ያለነው:: ይች አገር አማራጮቿ ሁሉ በጎሳ እሾህ ታጥሮባት ወደ ገደል አፋፍ እየቀረበች ነው:: ምሁራን አንድ ሊሉ ይገባቸዋል::





የምሁራን ዝምታ ማብቃት አለበት:: የምሁራን አድርባይነትና ጥቅመኝነት እጅግ አድርጎ ያሣፍራል:: ምሁራን ታላላቅ ሰዎች ናቸው:: ተፈርተው መከበር አለባቸው:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ሞራላዊ ብቃት ኖሯቸው በተግባር ሲያሣዩ ነው:: ማንንም ሣይፈሩ ለሰዎች ወይንም ለዜጎች ስቃይ ድምፃቸውን ማሰማት አለባቸው:: በምንም መመዘኛ ምሁራን የጎሳ ጥልቆ ሊያጠልቁ አይገባቸውም:: ኢትዮጵያዊ ካባ ነው መጎናፀፍ ያለባቸው:: ለማንኛውም ቢያንስ ለብሔራዊ መግባባት ምሁራን ድምፃቸውን ማሰማት የሚገባቸው ጊዜው አሁን ነው::

<><><>

# የሽብር ራእይ!

የኢሕአዴግ መንግሥት አንዱ ከፋቱ ዜጎችን በሽብር ራእይ ዘፍቆ አሸማቆና አስጨንቆ መግዛት ነው:: ለመሆኑ ሽብር ምንድን ነው?

ሽብር የከፋ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ምጥ ማለት ነው:: አሸባሪዎች ደግሞ ህፃናት የሚማሩበትን ት/ቤት በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ፣ አይሮፕላን በመጥለፍ መንገደኞችን አግተው ፖለቲካዊ ጥቅምን ለማስከበር ሲሉ እንዲፈፀምላቸው የሚፈልጉትን ጥያቄ በማቅረብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይደራደራሉ:: ለጠየቁት ጥያቄ በቂ የሆነ መልስ ካላገኙ አሠቃቂ የሆነ ርምጃ እንደሚወስዱ ይዝታሉ:: በዚህ ወቅት በታጋቾቹና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ጭንቀትና ምጥ በቃላት ለመግለጽ ይከብዳል::

እንግዲህ ከዚህ መሠረታዊ ሀቅ ስንነሳ እውነት ባገራችን ይህንን ዓይነት ሽብር የሚፈፅሙ ሽብርተኞች አሉ ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ እንቆቅልሽ ነው የሚሆንብን::

በርግጥ ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ በተፈጠረው የመንግሥት አስተዳደር ክፍተት በመጠቀም ግለሰቦች አይሮፕላን በመጥለፍ ወደ ውጭ አገር ለመኮብለል እንደ ፋሽን ተዘውትሮ ነበር:: ጋምቤላ፣ ባሕርዳር፣ ድሬደዋ፣ ከዚሁ አዲስ አበባ ተሞክሯል:: እነዚህ ጠላፊዎችም አገራቸውን ለኢሕአዴጋውያን ጥለው ለመሰደድ ከማሰብ በስተቀር አንድም የፖለቲካ ጥቅም ለማስከበር የሚል ጥያቄ በወቅቱ ለመንግሥት ስለማቅረባቸው መረጃ የለም:: አብዛኞቹም በቁጥጥር ሥር ውለው ቃላቸውን ሠጥተው እሥር ተፈርዶባቸው የእሥር ጊዜያቸውን ጨርሰው ወጥተው የመንግሥት ተቀጣሪም የሆኑ አሉ:: ለምሳሌ ያምበዋ ወጣት ሙኒት ተጠቃሽ ናት:: ሙኒት ኡጋንዳ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ተመድባ በመሥራት ላይ ነች::

ሌላው በዘመነ ደርግ "ከኔ ወዲያ አብዮተኛ ላሣር ነው!" በሚል በኢሕአፓና በመንግሥት መካከል በተፈጠረ ሥልጣን ለኔ ይገባኛል ግብግብ ምክንያት በነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር ከወዲህም ሆነ ከወዲያ ያንዲት እናት ልጆች በሚያሣዝን ሁኔታ ተራርደዋል:: ይህ የታሪክ ጠባሣም ዘግናኝ ከመሆኑ በስተቀር የፀረ-ሽብር ሕግ አልወጣለትም ነበር:: ለሥልጣን ቅርምት ወንድማማቾች የተጋደሉበት በመሆኑ በሁለቱም በኩል እናቶች ከል ለብሰዋል:: የሚያሣዝነው ይልቅ እናቶች ዛሬም ቢሆን ከላቸውን በነጭ ሸማ





አለመቀየራቸው ነው:: በተረፈ ዛሬ ኢሕአዴግ እንደሚጮኸው የውጭ ጫና ወይንም ያከራሪዎች እጅ አልነበረበትም:: ይህ ከሆነ ታዲያ የዛሬው የኢሕአዴግ ሥጋት ከምን የመጣ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው::

እንደሚታወቀው ኢሕአዴግ ያሜሪካን ሣተላይት (ተወርዋሪ ጦር) በመሆን በጎረቤት አገሮች ላይ በሰላም አስከባሪነት ስም የሚያደርገው ጣልቃገብነት በራሱ እንዲሸበርና ሰላም እንዲያጣ አድርጎታል:: የራሱ ጥላ ባስበረገገው ቁጥር የራሱን ተግባር ነው አንዳንድ ጊዜ ገልብጦ የሚያነብልን::

በርግጥ ባንድ ወቅት ልክ እንደ አይሮፕላን ጠለፋው በኦነግ እየተሳበበ አዲስ አበባና ድሬደዋ በትላልቅ ሆቴሎች ላይ ጊዜ ጠብቀው የሚፈነዱ ቦምቦች እየተጠመዱ በመፈንዳታቸው ዜጎች መሞታቸውና መቁሰላቸው እውነት ነው:: ለምሳሌ ፒያሣ ትግራይ ሆቴል የፈነዳው ፈንጂ በመዝናናት ላይ የነበሩትን ንፁሐን ዜጎችንና የሆቴሉን አስተናጋጆች ጨምሮ በርካታዎች የሞትና የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል:: ይህ ሁሉ ሆኖም ኢሕአዴግ በወቅቱ በኦነግ ከማሳበብ በሥተቀር አክራሪዎች ወይንም አልቃኢዳ አለዚያም ሽብርተኞች የሚል መግለጫም ሆነ የፀረ-ሽብር ሕግ አላወጣም ነበር:: እውነታው ይህ ከሆነ ታዲያ ያሁኑ የኢሕአዴግ ሥጋትና ፍርሃት ከምን የመጣ ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል::

ዋናውና የኢሕአዴግ ተጨባጩ ሥጋት እያደገ የመጣውን የሕዝቡን የሙብት ጥያቄ ለመመለስና ለማስተናገድ ከብዶታል:: በተለይም ከ97 ዓ.ም ወዲህ የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ካቅሙ ውጭ ሆኖበታል:: በመሆኑም ሌላ ተጨማሪ የማፈኛ ሕግ እንደሚያስፈልገው አምኗል:: ይህንንም ለመጫን መልካም አጋጣሚን ወይንም "የዴሞክራትነቱን" ጭምብል የማይገፍ መሆን እንደሚገባው ተገንዝቧል:: ይኸም ተሣክቶለታል::

መቸም ኢሕአዴግ የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝልኛል ካለና ለሥልጣን ማቆያ ጊዜ የሚያገኝ ከሆነ የሌሎችን መጥፎ ማነቆ ሕግም ሆነ ሌላውን ነገር ከመኮረጅ ወደ ኋላ አይልም:: እናም ሽብርተኝነት በኢትዮጵያ እንዳለና በምሥራቅ አፍሪካ አደጋ እንደሚሆን አስቀድሞ ከማንም በፊት መጮህ የጀመረው ያሜሪካን መንታ ፎቆች በሽብርተኞች ከተደረመሱ በኋላና ዓለም አቀፍ ገፅታ ሲሰጣቸው ነበር:: ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የፀረ-ሽብር ሕግ አውጥቶ ሥራ ላይ አዋለ:: በተለይም ጦሩን ሞቃዲሾ ድረስ ካዘለቀ በኋላ እንቅልፍ ሊተኛ አልቻለም:: ስለሙብታቸው የሚሟገቱትን ሁሉ "ሽብርተኞች" እያለ እስር ቤት ማጎርን እስካሁንም እንደተያያዘው ነው::

## የፀረ-ሽብር ሕጉ

የፀረ-ሽብር ሕጉ ገና ከመግቢያው ላይ ዓላማውን ሲያስተዋውቅ እንዲህ ይላል፡-

*"በሥራ ላይ ያሉት የሀገሪቱ ሕጎች በበቂ ሁኔታ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ጠንካራ የሕግ አቅም መፍጠር በማስፈለጉ . . ."* ይላል፡፡ *(አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ.ም)*

እንግዲህ የሕጉ ዓላማ ያገርን ደህንነት ከከፉ አጥቂዎች ወይንም አሸባሪዎች ለመጠበቅ ወይንም ለመከላከል ሣይሆን የዜጎች ሽምቀቆ መሆኑን ነው የምንረዳው፡፡ ያ ባይሆንማ ኖሮ ነባሩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ከበቂ በላይ በቂ ነበር፡፡ ሽብር በሌለበት አገር ሽብር ያለ በማስመሰል ኢሕአዴግ ለራሱ ተሸብሮ ዜጎችን በማሸበር ሥልጣን ላይ ለመቆየት የማገቻ ሕግ አውጥቶ ነፃ ሐሳብ ለማራመድ የሚሞክሩትን ሁሉ በሽብርተኝነት እያነቀ ወደ እስር ቤት መወርወርን የትንፋሽ ማግኛ ስልት አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡

ባስፈለገው ጊዜና ለሥልጣኔ ያሠጉኛል የሚላቸውን በሕግ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን በደረቁ በመወንጀል ወይንም የፕሮፓጋንዳ ዶፍ በማውረድ ዜጎች ወደነሱ እንዳይጠጉና አባል እንዳይሆኑ የማስፈራሪያ አጥር ሲያጥር ሕጉ በክፍል2 እንዲህ ይላል፡-

*"በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ስለመሣተፍ" በሚለው ርእስ ሥር ፩ ማንኛውም ሰው በሽብርተኛ ድርጅት ወይንም የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈፀም ሰው የመለመለ ወይንም አባል የሆነ ወይንም ሥልጠና የወሰደ ወይንም በድርጅቱ በማንኛቸውም መልክ የተሳተፈ እንደሆነ እንደየ ተሳትፎ ደረጃው ከ5-10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል"* ይላል፡፡ ይህ እንግዲህ ትልቅ ማሸማቀቂያና የፍርሃት ድባብን የሚፈጥር ነው፡፡

ኢሕአዴግ ግለሰቦችን ለማነቅና ለማጥፋት ዒላማ አድርጎ ሲነሳም እነሱን በቁጥጥር ሥር ከማድረጉ በፊት ለመረጃ ይሆኑኛል የሚላቸውን ሰዎች አስቀድሞ ያዘጋጃል፡፡ ባስፈለገ ጊዜም ከታዳኙ ጋር አብሮ በቁጥጥር ሥር ያውላቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በሱ ላይ እንዲመሠክሩ በርካታ ማባበያዎችን ያቀርብላቸዋል፡፡ ፈቃደኛ ካልሆኑ ከሰውዬው ጋር ተባባሪዎች ናችሁ ተብለው እድሜ ልክ እስራት እንደሚጠብቃቸው ከዛቻ ጋር ይነገራቸዋል፡፡ በሱ ላይ በመመስከራቸውም ምንም ነገር እንደማይደርስባቸው ልዩ ጥበቃና





እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ሁሉ ቃል ይገባላቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የተጠየቁትን ለመፈፀም ይፈቅዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ግን ቀድመው የተዘጋጁ ስለሚሆኑ የሚሰጣቸውን መመሪያ ከማጥናት ውጭ ምንም ዓይነት ችግር አይፈጥሩም፡፡ ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ማንነታቸው ሁሉ እንዳይታወቅ የፀረ-ሽብር ሕጉ እንዲጠብቃቸው ሆኖ ተቀርጿል፡፡ ክፍል7 እንዲህ ይላል፡-

*"ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች"* በሚለው ሥር አንቀጽ 32 *"ለምስክሮች ጥበቃ ስለማድረግ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፍ/ቤት ማንኛውም የሽብርተኝነትን ጉዳይ በሚያይበት ጊዜ በራሱ አነሳሽነት ወይንም ባቃቢ ሕግ ወይንም በምስክሩ ጠያቂነት የምስክሩን ማንነትና አድራሻ በሚስጥር ለመጠበቅ አስፈላጊ ርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል. . ."* ይለንና የሚወስዳቸውንም ርምጃዎች እንደሚከተለው ያስቀምጣቸዋል፡-

*ሀ/ ከሱ የሚሰማበትን ቦታ መወሰን (መደበቅ ሊሆን ይችላል) በቀንፍ ውስጥ ያለው ሐሳብ የኔ ነው፡፡*

*ለ/ የምስክሮች ስሞችና አድራሻዎች በፍ/ቤት ትእዛዞች፣ ውሳኔዎችና መዝገቦች ላይ እንዳይገለፁ*

*ሐ/ የምስክሮች ማንነትና አድራሻ እንዳይገለጽ ትእዛዞችን መስጠት"* ይላል፡፡

እንግዲህ የፀረ-ሽብር ሕጉ ለሚዘጋጁ ምስክሮች እስከዚህ ድረስ ዘልቆ እንክብካቤ እንደሚያደርግ ተቀርጾ ተቀምጧል፡፡ የተፈረደበትን ሰው ለማንበርከክና ከጫማ ሥር ለመጣል ደግሞ የፀረ-ሽብር ሕጉ በክፍል7 ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

*"አንቀጽ 33 የፍርድ ሂደትን ስለመርዳት" በሚለው "ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተን ወንጀል በመፈፀሙ ባድራጎቱ የተፀፀተ እንደሆነና ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም በዝርዝር ለማስረዳት የተባበረ እንደሆነ ወይንም ወንጀሉን በመፈፀሙ ከሱ ጋር የተሳተፉ ሰዎችን ያጋለጠ እንደሆነ ባቃቤ ሕግ ጥያቄ መነሻነት ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ሊያቀልለት ይችላል"* ይላል፡፡ ይህንን አንቀጽ በተመለከተ ነፍሳቸውን ይማረውና ጠ/ሚንስትር መለስ ፓርላማ ላይ ባንድ ወቅት አንስተው "ወንጀል መፈፀማቸውን አምነው ከተፀፁቱና ይቅርታ ከጠየቁኮ ምህረትም ይደረግላቸዋል" በማለት ተናግረው ነበር፡፡

የዚህ አንቀጽ ዓላማ ሁለት ሥለት ያለው ነው፡፡ አንደኛው ስለት አንበርክኮ ከጫማ ሥር ከጣሉ ብኋላ ዳግም እንዳይለምደው አንገቱን ደፍቶ

እንዲኖር ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ሥልት ደግሞ እድሜ ልክ ፍርድ ጭኖ ሁለት ሦስት ዓመታት አሥሮ መልሶ ይቅርታ አድርጎ በምሕረት በመልቀቅ ለወገን ሩህሩህና ተጨናቂ ስለሚያስመስል በተለይ የውጭ ዜጎችን ለማታለል ይጠቅማል። ኢሕአዴግ ይህንን ሥልት አዘውትሮ ተጠቅሞበታል። ዛሬም እየተጠቀመበት ነው። የዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የቅንጅት መሪዎችና በኋላ ደግሞ ብርቱካን ሚደቅሳ ነች። ከዚህ ውጭ ኢሕአዴግ ለዜጎች የሚራራና የሚጨነቅ አንጀት የለውም።

እንግዲህ የፀረ-ሽብር ሕጉን ከፍ ብለን እንዳየነው ያገርንና የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ተብሎ የወጣ ሣይሆን የኢሕአዴግን ደህንነትና ከሥልጣን ላይ ተጣብቆ እንዲቆይ በጥንቃቄ ተሰልቶ የወጣ ሕግ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ደርግ ሕግን ይፈራል። ፈርቶም ያከብራል። ሕግ የያዘውን ነገር ባጠገቡ አይደርስም፤ ወይንም በፍ/ቤቶች ጉዳይ ላይ በድፍረት ጣልቃ አይገባም። ወይንም እንዲህና እንዲያ ይደረግ ብሎ ጫና አያደርግም። ሊያጠፋቸው፣ ሊረሽናቸው የሚፈልጋቸውን ግለሰቦች የሕግ ሽፋን ሳይሰጥ ወይንም ከሕግ ፊት ሳያቀርብ "የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ..." እያለ በመሸለል ይረሽናቸዋል። ባንፃሩ ኢሕአዴግ ሕግን ይንቃል፤ ንቆም በሕግ ሲቀልድ ይስተዋላል። አንዲት ነገር ከሕግ ውጭ አይሠራም እንዲባል በሕግ ሽፋን ዜጎችን ያጉላላል፤ ያንገላታል፤ በትንሺ ጥፋት ሁሉ የፖለቲካና የሽብር ጥላሸት በመቀባት እድሜ ልክ፣ ዝቅ ሲልም 20 ዓመትና 18 ዓመት ያሸክማል።

በዘመነ ኢሕአዴግ ፍ/ቤቶች ከኢሕአዴጋውያን ነፃ ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር አያስችልም። አንዳንድ ጊዜም የፍርዱ ሂደት በባለሥልጣናት ቀድሞ የሚያልቅበት አጋጣሚም እንዳለ ዜጎች በምሬት ሲገልፁ ዓመታትን አስቆጥረዋል። በመሆኑም በነዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ከሁሉም እየከፋና እየጎፈነነ የመጣው የፍትህ ድርቀት እየበረታ መምጣቱ ነው።

## የፀረ-ሽብር ሕጉ ለምን አስፈለገ?

> *"ሰላማዊ ትግል ውጤት እያመጣ መሆኑ የሚታወቀው በአምባገነኖች እስር ቤቶች ሰላማዊ ታጋዮች መታጎር ሲጀምሩ ነው!!" ማኅተማ ጋንዲ።*





## የድኩላና የነብር ኑሮ ለምን?

እንደሚታወቀው ሕወሓት ሥልጣን ላይ የወጣው መጠነ ሠፊ ደም አፍስሶና ያገር ንብረትን አውድሞ እንጂ በሕዝብ ይሁንታ በምርጫ ሥልጣን ላይ የተቀመጠ በመሆኑ አይደለም። በጉልበትና በማምታታት ሥልጣን የጨበጠ ፓርቲ ደግሞ የሰላም እንቅልፍ አይተኛም፤ ዜጎችንም አያስተኛም። እሱ በበረገገ ቁጥር ዜጎችንም እያስበረገገ በበረት ውስጥ መንጋውን እንደሚያምስ ከፉ ኮርማ ሕዝብን እያመሰ ለመብታቸው የሚሟገቱትን ንቁ ወጣቶች ወንጀል እየፈበረከ ያግታል፤ የበረገጉት ደግሞ አገር ጥለው እንዲሰደዱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያመቻቻል። ቀሪዎቹ በፍርሃት ተሸማቀው የድኩላና የነብር ኑሮ እየኖሩ ኖርን ይላሉ። ከነዚህ ጠንከር ያሉቱ ደግሞ ምክንያት ተፈልጎ ወይንም በዚያው መከረኛ ሽብርተኝነት ተሳቦ ወደ እስር ቤት ይወረወራሉ።

ሕወሓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈፀመ ያለው ግፍ እንቅልፍ አያስተኛውም። ሊተኛም አይችልም። ፈንጅ ላይ የተቀመጠ ድርጅት ነው። ሕዝብን በጎሳ ከፋፍሎ ትውልድን አገራዊ ራእይ አሣጥቶ የኢትዮጵያን መሠረት አናግቷል። ኤርትራን ተዋግቶ አሥገንጥሏል፤ ያሰብን የባሕር በር አዘግቷል፣ በዚህ ከፋና እኩይ ተግባሩ ከሕዝብ ጋር ሊያስማማው የሚችል አንዳችም በጎ ሥንቅ የለውም።

ታዋቂው ምሁር ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ኢሕአዴግ የሚያወጣቸው ሕጎች ለዜጎች ማጥቂያነትና ሕዝቦች በባርነት እንዲማቀቁ ሆነው መቀረጻቸውን እንዲህ ሲሉ ይተቻሉ፦

*"ሕግ የዜጎች ከለላ፣ የዜጎች አለኝታ በመሆን ፈንታ በተጣመመ መንገድ እየተተረጎመ የዜጎች ማጥቂያ መሣሪያ እየሆነ፣ በዚህ ሥልት ንፁሐን ዜጎች ሲወነጀሉ፣ ሲታሠሩ፣ አገር ጥለው ሲሰደዱ፣ እውነት ዜጎችን ነፃ የማታወጣበት እየሆነች ስትሄድ ኢያዩ ዝም ማለት የመንግሥት ባሪያ መሆን ነው"* ሲሉ ምሁሩ ነቅፈዋል። *(ፍኖተ ነፃነት ቅፅ 2 ቁጥር 37 ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም)*

በመሠረቱ መንግሥት ሕግ ሲቀርጽም ሆነ ሲያወጣ ዜጎቹን የከፋ አደጋ እንዳይገጥማቸው የመከላከያና የመጠበቂያ ሕግ ያወጣል እንጂ ገና ለገና ለሥልጣኔ ያሠጉኛል፣ ይቀናቀኑኛል ብሎ የፍርሃት ሕግ አያወጣም። መሰሎት እንጂ ሕጎች ሁሉ የወንጀሎች ምንጮች ናቸው። አፈናው እየከፋና እየጠበቀ በሄደ ቁጥር ካፋናው ሽመላቀቅ የመውጫ ቀዳዳን መፈለግ የግድ

ይሆናል፡፡ ነፃነትን በመሥጠት ወይንም በመልቀቅ እንጂ የማፈኛ ሕግ በማውጣት በጭራሽ ሕዝብን መግዛት አይቻልም፡፡ በተለይም ስለመብታቸው የሚሟገቱትን በዚሁ የማፈኛ ሕግ ወንጀል እየፈበረኩ የእድሜ ልክ እሥራት መጫን ይሰቀጥጣል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን አንዱዓለም አራጌ፣ ጋዜጠኛ እስከንድር ነጋ፣ ናትናኤል መኮንን <ሸብርተኞች> ተብለው ሲያዙ በተቀናበረና በተጠና ስልት የተያዙ ለመሆናቸው ሁለት ማስረጃዎችን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

አንደኛው እንደተያዙ "ታላቁ መሪያችን" በተወካዮች ም/ቤት ባደረጉት ንግግር ርግጠኛ ሆነው በማስረጃ እንደተያዙ ነበር የተናገሩት፡፡ ይሁን እንጂ ዘግይቶም ቢሆን የፍርድ ሂደቱ ሲጀመር አቃቤ ሕግ በተደጋጋሚ የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀ ምስክርና ማስረጃ ፍለጋ ነበር የገባው፡፡




*አንዱዓለም አራጌ ከባለቤቱና ከሁለት ህፃናት ልጆቹ ጋር የዕድሜ ልክ እሥራት ከመሸከሙ በፊት*





ሁለተኛው ማስረጃ ሦስቱም ሲያዙ በያሉበት በተመሣሣይ ሰዓት በዘመቻ ነበር፡፡ እነዚህን የሰላም ታጋዮች በጭፍኑ ሸብርተኞች ናቸው ብለን ፍርድ ከመሥጠታችን በፊት ወይንም ንፁሆች ናቸው ብለን አስቀድመን ከመቆርቆር ትንሽ ስለ ሽብርተኞች ምንነት ወይንም በገሀዱ ዓለም ስላላቸው ሕይወት ማወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

እንደሚታወቀው ሽብርተኞች የራሳቸው የሆነ ኑሮ የላቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ የት እንደሚኖሩ እንኳን በቅጡ አይታወቁም፡፡ አንዳንድ ጊዜም በውኑ ዓለም ስለመኖራቸው የምንጠራጠር ጥቂቶች ዓይደለንም፡፡ ከሚወስዷቸው ዘግናኝና አሸማቃቂ የጭካኔ ርምጃዎች አንፃር እነሱነታቸውን በሰብዓዊ ሚዛን አስቀምጦ በቃላት ለመግለፅ እጅግ ከባድ ነው፡፡ እነሱን አድኖ ለመያዝና ማንነታቸውን ለይቶ ለማወቅ የሚጠይቀው የገንዘብ መጠንና የሰው ኃይል በራሱ ያንዲትን አገር ኢኮኖሚ የሚፈታተንና የሚያደቅ ነው፡፡ አሜሪካን ኦሳማ ቢንላድንን አድና ለመያዝ ወይንም ለማጥፋት ምን ያህል ጊዜ እንደ ደከመች ዓለም ያወቀው ሀቅ ነው፡፡



*የ18 ዓመት ፈርደኛ ናትናዔል መኮንን*



አንዱዓለም አራጌ ከባለቤቱና ከሁለት ህፃናት ልጆቹ ጋር
የዕድሜ ልክ እሥራት ከመሸከሙ በፊት



የ18 ዓመት ፍርደኛ ናትናኤል መኮንን

ከዚህ እውነታ ስንነሳ እውነት እነ አንዱዓለም አራጌ ሽብርተኞች ነበሩ? ኑሯቸውስ ከላይ እንደተገለፁት ያሉ ናቸው? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ሦስቱም ባለትዳሮችና የልጆች አባቶች ናቸው:: ታዲያ ሦስቱም ባለትዳሮችና የልጆች አባቶች ከሆኑ በሽብርተኝነት ተግባር ላይ ለምን ተሠማሩ? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው::

የኢሕአዴግ የጎሣ ሥርዓት አፋኝ ከመሆኑ የተነሣ እንቅልፍ አያስተኛም:: ሰዎች ሆነን እንደ ሰዎች የምናስብ ከሆነ እንዴት ብለን ነው የራሳችንን ምቾት በመምረጥ ብቻ ተደላድለን መቀመጥ የምንችለው? የነዚህ የሰላም ታጋዮች ችግርም ወይንም በሽብርተኝነት ያስወነጀላቸው የነሱ ኑሮ ጎሎባቸው ያንን ለማሟላት ሣይሆን የዜጎች ስቃይና ሰቆቃ አርፈው የግል ኑሯቸውን በምቾት እንዲኖሩ አላስቻላቸውም:: በተለይም የዚች አገር የወደፊት እጣ ፈንታ በእጅጉ አስጨንቋቸዋል:: የሥርዓቱ አፋኝነት የጉረሮ አጥንት ሆኖባቸዋል:: እናም የሥርዓቱን በታኝነትና አፋኝነት አጥብቀው ተቃወሙ:: መቃወም ብቻም አይደል ለውጥም መምጣት እንዳለበት አመኑ:: ይኼ ነው እንግዲህ በሽብርተኝነት ያስወነጀላቸው::

አንድን አፋኝ ሥርዓት መቃወምና የፍትሕ ሥርዓት እንዲሰፍን መታገል በሽብርተኝነት የሚያስወነጅል ከሆነ እያንዳንዱ የዚች አገር ዜጋ የሞት ያህል አይቀሬውን "ሽብር" በጀርባው አዝሎ እንደሚዞር ማወቅ አለበት:: ባጭሩ የነአንዱዓለምና የነ እስክንድር ወንጀል አርፈው እየተረገጡ ለመገዛት አለመፍቀዳቸው ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ ከታላላቅ ሕንፃዎች ሥር ወይንም ሕዝብ በሚዝናናባቸው ትላልቅ ሆቴሎች ፈንጂ ሲያጠምዱ ወይንም በሌ አይሮፕላን ለመጥለፍ ሲሉ እጅ ከፍንጅ አልተያዙም::

በመሠረቱ የሥርዓቱን አፋኝነትና ዴሞክራሲ አልባነት አውቆም ይሁን ሣያውቅ ማስታወቂያ ሚንስቴር "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና የደህንነት፣ ፖሊሲና ስትራቴጅ" ብሎ ባሳተመው መጽሐፉ የሚከተለውን ቁምነገር አስፍሯል:-

*"የዴሞክራሲ ሥርዓት ባገራችን እውን ካልሆነ በብሔርና በእምነት ተነጣጥለን፣ በመብት መረገጥ ተቃቅረን፣ መበጣበጣችንና ሰላም መጥፋቱና ልማት ቀርቶ ድህነት መስፋፋቱ ብሎም ለእልቂትና ለብተና መዳረጋችን አይቀርም. . .ልማትና መልካም አሥተዳደርን የማስፈን ጉዳይ ብቻ ሣይሆን እልቂትና ብተናንም የማስቀረት፣ ብሔራዊ ህልውናችንን የማረጋገጥ ጉዳይም ጭምር ነው . . ."* ይለናል:: *(ገጽ 2-3)*





ማስታወቂያ ሚንስቴር ሕሊናውን ቆጥቁጦት ወይንም አይቀሬውን የከፋት ቀውስ አስቀድሞ ተገንዝቦ ይህንን ሀቅ ሣይደብቅና ሣያድበሰብስ ማስቀመጡ ሊያስመሰግነው ይገባል:: ሌላም ማስረጃ መጨመር ተገቢ ነው::

እንደሚታወቀው ጠ/ሚንስትር መለስ <የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው፤ የፈጠሯትም አፄ ምኒልክ ናቸው> ብለው ነው የሚያምኑት:: ይሁን እንጂ በሌላ አጋጣሚ ከሳቸው አንደበት ይወጣል ተብሎ ሊታመን በማይችል መልኩ ሲናገሩ ደግሞ ግርምትን መፍጠሩ አይቀርም:: ካንገታቸው ነው ካንጀታቸው? ለሚለው ጥያቄ ዛሬ በሕይወት ስለሌሉ መልስ ማግኘት አንችልም:: ለማንኛውም እሳቸው የተናገሩትን እነሆ:-

*"የጠቅላይ ሚንስትር ሥጋት ምን ሊሆን ይችላል?"* ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ *"ሁልጊዜም ከእንቅልፌ የሚያባንነኝ ሥጋት አለ:: ይች ታላቅ አገር፣ ይቺ ካንድ ሺ ዓመታት በፊት ታላቅ የነበረች አገር አስከፊ አዘቅት ውስጥ ገብታ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቿ የተራቡባትና የሞቱባት አገር ምናልባትም በመፈረካከስ ላይ ትሆን? የሚል ፍርሃት ይቀሰቅሰኛል::" (መለስ ከልጅነት እስከ እውቀት ገጽ 128)*

ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ ሣይቀሩ ሀቁን ሣይደብቁ እየተናገሩ <ምናልባትም በመፈረካከስ ላይ ትሆን?> በማለት እየጠየቁ ታዲያ የነአንዱዓለም የሽብርተኝነት ወንጀል ከየት መጣ? እንዴትስ ተፈበረከ? ወገን ጠይቁ::

ማስታወቂያ ሚንስቴር ወዳሣተመው መጽሐፍ ስመልሳችሁ ደግሞ የሚከተለውን ሐቅ ታገኛላችሁ:- ". . .*በጎረቤት አገራት* (ዐረቦቹ ለማለት ነው) *በግርድና መኖር እንደፀጋ በሚወሰድባት አገር የሚኖር ዜጋ ካላፈረ፣ ካልተሸማቀቀ፣ ውርደቱ ወገቡን ካልቆረጠው፣ ያገር ፍቅሩ የቱ ላይ እንደሆነ አስቸጋሪ ነው?. . .ያሁኑ ውርደታችን መሠረታዊ ምንጩ ድህነትና ኋላቀርነት ነው:: የዴሞክራሲና የመልካም አሥተዳደር እጦት ነው . . ."* (እንደላይኛው ገጽ 7-8)

እንግዲህ አሁን አገሪቱ ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ ማስታወቂያ ሚንስቴር ያሣተመው መጽሐፍ አልደበቀም:: በተለይም የመራባችንና የመዋረዳችን ዋንኛ ምንጩ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እጦት መሆኑን በሚገባ ገልፆታል:: በርግጥም የዐረቦች ገረድ ከመሆን ለዚች አገር ወጣቶች የከፋ ውርደት ሊኖር አይችልም::

ኢሕአዴግ ባንድ በኩል የዴሞክራሲ አፈናና የመልካም አሥተዳደር እጦት መኖሩን ያምናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ የዴሞክራሲ አፈናንና የመልካም አሥተዳደርን እጦት በመቃወም ለውጥ እንዲመጣ የሚታገሉትን የሰላም ታጋዮች በሽብርተኝነት ስም እየወነጀለ እድሜ ልክ በመፍረድ እስር ቤት ይከታል፡፡ ይህ ነገር እንዴት ነው? ብለን ይህንኑ ጥያቄ ይዘን ራሱን ኢሕአዴግን ብንጠይቀው ያለጥርጥር የሚሠጠን መልስ፡-

"አዎን፤ ዴሞክራሲያችን ገና ጨቅላ ነው፤ አላደገም፤ በዚህ ምክንያትም የመልካም አሥተዳደር እጦት አለ፡፡ በተለይም ከላይ ወደታች ሲወርድ ያፈፃፀም ችግር አለ፡፡ ይሁን እንጂ ዴሞክራሲን እየመጠንኩ ትንሽ ትንሽ የማጎርሳችሁ እኔ እንጅ እናንተ እየጠቀለላችሁ ልትጎርሱ አትችሉም፡፡ ለውጥ የሚመጣውም በኔ እንጂ በሌላ አካል ሊሆን አይችልም፡፡ እኔው በኔ ‹በመተካካት› ዴሞክራሲንም ሆነ መልካም አሥተዳደርን በረጅም ጊዜ ሂደት እንደማሰፍን አትጠራጠሩ፡፡ ከኔ ውጭ የሚደርግ የትግል ሥልት ግን ሕገወጥ ብቻ ሣይሆን ሽብርተኝነትም ነው" ብሎ እንደሚመልስ መጠራጠር አያሻም፡፡

እነ አንዱዓለም አራጌ ደግሞ <በምንም መመዘኛ ባፉኙ ኃይል ለውጥ ሊመጣ አይችልም> ባዮች ናቸው፡፡ <መተካካት> የሚባለውም <ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም> እንደሚባለው ዓይነት ነው ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ልዩነታቸውም ከዚህ ላይ ነው፡፡

## መልካም አሥተዳደር እንዴት?

ስለመልካም አሥተዳደር ታላቁ ምሁር ዶ/ር ሐዲስ ዓለማየሁ *<ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አሥተዳደር ያስፈልጋታል?>* በተባለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል፡- *"መንግሥት የሕዝብ እንጂ ሕዝብ የመንግሥት ሊሆን አይችልም"* (ገጽ 13) በሌላ አነጋገር "መንግሥት የሕዝብ አገልጋይ እንጂ ሕዝብ አገልጋይ ወይንም ሎሌ ሊሆን አይችልም" ማለታቸው ነው፡፡ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ግን ከዚህ ሀቅና መርህ በእጅጉ የራቁ ናቸው፡፡ የሕዝብ ሎሌ የመንግሥት ጌታ፤ ያውም የታገተ ወይንም የተጠረነፈ ሕዝብ፡፡

እንግዲህ እነ አንዱዓለም አራጌ ከላይ እንደ ተመለከትነው ኢሕአዴግ ራሱ ሊደብቀው ያልቻለውን ከፋፋይ ሥርዓት መልከ እንዲይዝ ታገሉ እንጂ ያረቡ ዓለም የለውጥ ወላፈን እንኳን ሺው እንዲል አልተነፈሱም ነበር፡፡ ለምን ቢባል ያገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አይፈቅድምና፡፡





የኢሕአዴግ እውነተኛ ሥጋትና ፍርሃት ግን ያረቡ ዓለም የለውጥ ማዕበል ወደ አገራችን እንዳይመጣ በፖለቲካው መሥክ ንቁ ተሣታፊ የሆኑትን ወጣት ታጋዮች አስቀድሞ ታፔላ በመለጠፍ ማኮላሸትና ሌሎች ተሸማቀው አርፈው እንዲቀመጡ ለማድረግ ነው፡፡ እውነቱ ይኸ ነው፡፡

የሚያሣዝነውና የሚሰቀጥጠው ደግሞ አንዱዓለም አራጌ ጧት ልጁን ት/ቤት (ሙዋዕለ ሕፃናት) አድርሶ ማታ ሲመለስ ለውጡን ለማየት ፎቶ ለመታሰቢያ ከሕፃን ልጁ ጋር ተነስቶ ነበር፡፡ አባት እንደወጣ ሲቀር ሕፃኑ ማታ ት/ቤት ውሎ ሲመለስ አባቱን ሲያጣው ምን ሊሰማው እንደሚችል መገመቱ ከባድ ነው፡፡ ጧት ማታም እናቱን "አባቴስ?" እያለ ሲጠይቅ እናት የምትሰጠው መልስ ሲጨንቃት ሕሊናዋ ምን ያህል ሊቆስል እንደሚችል እናቶች ካልሆኑ በስተቀር ይህንን ሰቀቀን ማንም ሊረዳው አይችልም፡፡ እንግዲህ እንዲህ ያለው የሰላም ታጋይ ወይንም ለውጥ ፈላጊ ነበር እድሜ ልክ ተሸከሞ ከርቸሌ የተከረቸመው፡፡

አንዱዓለም አራጌ እድሜ ልክ ሊፈረድበት "ጥፋተኛ" ተብሎ የመፈረጃ የፍርድ የማቅለያ ሐሣብ እንዲያቀርብ ፍ/ቤት በጠየቀው ጊዜ፡-

*". . .እኔ በተፈጠርኩበት በዚህ ዘመን ለራሴ፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት እንደሚገባን (እንደሚያስፈልገን) በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ፡፡ ይህንን በማድረጌ በማንም ላይ በከፋት አልተነሣሁም፤ ሕግም ጥሼ አላውቅም፡፡ በድሃዋ አገሬ ጥቅም ላይም አልተነሣሁም፡፡ ፈጣሪየንም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያሣዝን፣ ሕሊናዬን የሚቆጠቁጥ አንዳች ነገር ፈፅሜለሁ ብዬ አላምንም፡፡ ፈፅሞ ሰላም ይሰማኛል፡፡ እኔን ከዚህ ያቆመኝ የነፃነት ናፍቆት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችና ፍትሕ ለምኜ ስነፈግ ይኸ የመጀመሪያዬ አይደለም፡፡ ከሣሾቼ እንድጠጣው የፈለጉትን ጽዋ በፀጋ ከመጠጣት ውጪ ባልፈፀምኩት ወንጀል የማቅለያ ሐሣብ የመጠየቅ አማራጭን ሕሊናዬ ስላልተወልኝ አዝናለሁ"* ነበር ያለው፡፡

ናትናኤል መኮንን በበኩሉ ሲያዝ ከነአንዱዓለም ጋር በተመሣሣይ ቀንና ሰዓት ነበር፡፡ መንግሥት አለ ብሎ ሥራ ውሎ በ79 ቁጥር አውቶቢስ ተሣፍሮ ወደ ቤቱ ሲመጣ መገናኛ ላይ ድልድዩን እንደ ተሻገረ በታጣቂ ኃይሎች ተከቦ ነው የተያዘው፡፡ ይህ በራሱ የከፋ ሽብር ነበር፡፡ ናትናዔል የተያዘው ግን አውቶቢሱን በቦምብ ለማጋየት ቦምብ ይዞ አልነበረም፡፡ የምሳ

ሳህኑን በፌስታል አንጠልጥሎ ነበር፡፡ እሱም እንደ አንዱዓለም ጥፋተኛ ነህ ተብሎ የመፋረጃ ሐሳብ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ እንዲህ ነበር ያለው፡-

*“ወንድሙን ወንድሙ እየገደለ ሐውልት የሚያቆምበት ዘመን እንዲያበቃ ያቅሜን አስተዋፅኦ ለማድረግ ሰላማዊ ትግል አድርጌያለሁ፡፡ ይህንን በማድረጌ አልቆጭበትም!”*



*የ18 ዓመት ፍርደኛ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ*

እውቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሲያዝም በተመሣሣይ ሰዓትና ቀን ነበር፡፡ ህፃን ልጁን (ናፍቆትን) ከት/ቤት አውጥቶ በግል መኪናው ይዞ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከመንገድ ተኮቦ ነው የተያዘው፡፡ ህፃኑ ናፍቆት አባቱን ከነጣቂዎች ለማስለቀቅ በትንኝ አቅሙ በካልቾና በጡጫ ተፋልሟል፡፡ የፀጥታ ኃይሎቹ





እግዜር ይስጣቸው፤ ናፍቆትን ሽብርተኛ ብለው ካባቱ ጋር ቀላቅለው ወደ እስር ቤት አልወሰዱትም፡፡ እናቱን ጠርተው ነው ያስረከቧት፡፡ በዚህ ተግባራቸው ሊመሠገኑ ይገባቸዋል፡፡ ይች አገር ጨርሳ ወደ አረመኔነት አለመሸጋገሯ ተመስጌን የሚያሰኝ ነው፡፡ አጅሬ ኢጋዚ ቢሆን ኖሮ ግን የህፃን ናፍቆት አጥንት ስብርባሪ እንኳን አይገኝም ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ህፃኑ ናፍቆትን እናቱ ሠርከዓለም ፋሲል የተገላገለችው (የወለደችው) በ97ዓ.ም ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ነበር፡፡ እንግዲህ የዚች አገር የፖለቲካ ከፋትና ዝቅጠት እስከዚህ ድረስ የወረደ ነው፡፡

ውድ ወገኖቼ፤ እንግዲህ በህፃን ናፍቆት አእምሮ ውስጥ ምን ተፀንሶ የሚያድግ ይመስላችኋል? አንዳንድ ጊዜ በግሌ ሣስብ እነዚህ “የሕዝብ ብሶት ወለደን” የሚሉ የሕወሓት ተጋዳላዮች ወላጆቻቸው ምን ዓይነት የጭካኔ መርዝ እየጋቱ አሣደጓቸው? ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ እናንተም ጠይቁ፡፡ ለማንኛውም እስክንድር ነጋም የመፋረጃ ሐሳብ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ የሰጠው መልስ እነሆ፡-

*“ሀገሪቱ ውስጥ ሕጋዊና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር መምጣት እንዳለበት እንደ ጋዜጠኛነቴና እንደ ዜግነቴ ስለማምን ልጽፍ የሚገባኝን ጽፌለሁ፡፡ ይህንን በማድረጌ ሕሊናዬን የሚቆጠቁጠኝ ነገር የለም!”*

እንግዲህ ይህንን ሁሉ ያፈና መዋቅር የዘረጉና በኋላም ዜጎችን በዘመቻ እየተለቀሙ እስር ቤት እንዲታጎሩ የመሩ “ታላቁ መሪያችን” ነበሩ፡፡ ይባስ ተብሎ ዛሬ በሙት መንፈሳቸው እንግዛችሁ ስንባል ደግሞ እጅግ አድርጎ የሚቆጠቁጥ ነው፡፡



*የ18 ዓመት ፍርደኛ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ*

# ሽብር ፍለጋ ሞቃዲሾ ድረስ?

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ጎልታ ከምትታወቅባቸው ቁምነገሮች መሀከል አንዱና ዋናው የራሷን ሰንዝር መሬት አሣልፋ የማትሠጥ፣ የሌሎችንም ቅንጣት የማትፈልግ መሆኗ ነው፡፡ ሁልጊዜም በተከላካይነት እንጂ አንድም ጊዜ አቅም አለኝ ብላ ባጥቂነት ወሰን አልፋ ወይንም ደንበር ጥሳ ጎረቤት አገራትን ወራ ወይንም ተንኩሣ አታውቅም፡፡ ይህ የተከበረ የሦስት ሺ ዘመን ታሪኳ በዚህ ትውልድ ግን በጦር ጠማኙ ኢሕአዴግ እጅ ላይ በመውደቋ ምክንያት መልካም ገፅታዋ እንደ በረዶ ከምር ቀልጦ ወይንም ተንዶ ወሰን ጥሳ ጎረቤት አገር ሶማሊያን ወረረች፡፡

ኢሕአዴግ <ባሸባሪነት> ስም የገዛ ዜጎቹን የሚያምሰው አንሶ ደንበር ተሻግሮ ሶማሊያን በመውረር ያሜሪካንን ደም ሲበቀል ለኢትዮጵያ ደግሞ የዘለዓለም ደም በመትከል ጠላት ገዝቶላታል፡፡ ምንም ዓይነት የደንበር የይገባኛል ጥያቄ ሣይኖረን ወይንም እንደ 69 ዓ.ም 700 ኪሎ ሜትር ዘልቃ ሣትወረን አቶ መለስ ሠራዊታችን ሞቃዲሾ ድረስ ዘልቆ (በሕግ አስከባሪነት ስም) እንዲገባ ትእዛዝ የሠጡበት ምክንያት ለምንድን ነው? ካንድ “ዴሞክራት መሪ ነኝ” ከሚል የሚጠበቅስ ነበር ወይ? እነዚህን ጥያቄዎች ይዘን ስንቶቹስ ሞቱ? ስንቶቹስ ቆሰሉ? ስንቶችስ አሸዋ በልቷቸው ቀሩ? በውጤቱስ ኢትዮጵያ ምን አተረፈች? መልስ ሰጭ አካል ባታገኙም ጠይቁ፡፡

ርግጥ ነው ሶማሊያና ሱዳን ለኢትዮጵያ መልካም የሚባሉ ጎረቤቶች አይደሉም፡፡ መቸም ይሁን መቸ ጥሩ ጎረቤቶችም የሚሆኑ አይደሉም፡፡ ሱዳን የደንበር ጥያቄ ባይኖራትም ከግብፅ ጋር በማበር በዚሁ መከረኛ ዓባይ ወንዝ ምክንያት ልክ እንደዚህ ቀደሟ መገዝገዟን አታቆምም፡፡ ከዚህ ቀደም ለኤርትራ ገንጣዮችና ለሕወሓት አስገንጣዮች ሁለንተናዊ ድጋፍ በመስጠትና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንደ ዋና መሠረት በመሆን የጁን እስካገኘችበት እለት ድረስ የልቧን ሠርታለች፡፡ ወደ ፊትም ለኛ በጎ ነገር ታስባለች ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ትልቁ ቁምነገር ባጠመደችው ወጥመድ ወይንም በዘረጋችው አሽከላ መሸምቀቋ ነው፡፡ ኤርትራን ከኢትዮጵያ አስገንጥላ እኛን አሣዘነችን፡፡ እሷም ልታጣ የማትችለውን ለም አገርና የነዳጅ ክምችት ያለበትን ደቡብ ሱዳንን አጣች፡፡ <አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩ፤ በቆፈሩት ጉድጓድ ሣይገቡም አይቀሩ!> የሚባለው እንዲህ ያለው ነገር ነው፡፡ አንድ አገር ከዋናው አካል ሲገመስ ምን ያህል እንደሚያሣዝንና





እንደሚያም ሱዳን ቀመሰችው፡፡ በቆፈረችው ጉድጓድ ያለ አፈር መላሽ ገባችበት፡፡ ወደ ሶማሊያ ስንመለስ ደግሞ ሁኔታው ሌላ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሶማሊያ ከኢትዮጵያ የመሬት ጥያቄ አለኝ በሚል በተደጋጋሚ ስትተነኩስ መኖሯ ይታወቃል፡፡ በተለይም በ69 ዓ.ም እኛ በለውጥ ማዕበል እየተናጥን በነበርንበት ወቅት አጋጣሚውን ተጠቅማ ጊዜው አሁን ነው በሚል ድሬዳዋ ድረስ ዘልቃ ወራናለች፡፡ ዜያድባሬ በሕልም ግመል እየጋለበ ኢትዮጵያን ብቻ ሣይሆን ሶማሊያንም በጎሣ አናክሶ በመጨረሻ አፈራርሶ እሱም ሣያምርበት ካገሩ ተባሮ የትም ወድቆ ቀረ፡፡

ሶማሊያ ልክ እኛ በ69 ዓ.ም ውጥረት ላይ በነበርንበት ወቅት አመች ጊዜ ጠብቃ በእብሪት እንደ ወረረችን ሁሉ እኛም ዛሬ እሷ መንግሥት አልባ ሆና በጦር አበጋዞቿ እየታመሠች ባለችበት ወቅት ገና ለገና <የተለያዩ የእስልምና አክራሪዎች ወይንም አሸባሪዎች ምሽግ ልትሆን ትችላለች> በሚል ሥጋት በልዕለ ኃያሏ አሜሪካ አደፋፋሪነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ሞቃዲሾ ድረሽ ዘልቆ መግባቱ ጀግንነት ሣይሆን አንገት የሚያስደፋ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ ጣልቃ መግባት ካለባትም እንደተለመደው በጨዋ ደረጃ ለማንም ሳትወግን እንደ ጥንቱ ኩብሯን ጠብቃ በጎረቤት አገር ወግ ሸማግሌ ወይንም አደራዳሪ ሆና ነበር መቅረብ የነበረባት፤ ክብሯን ዝቅ አድርጋ ለኮሎኔል አብዱላሂ ዮሱፍ ወግና ፍልሚያ ውስጥ መግባቷ ግን አሣፋሪ ነበር፡፡ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሞቃዲሾ ድረስ የዘመተበት ምክንያት ምንድን ነው? እውን ሽብርተኞችን ፍለጋ ነው? ብለን ስንጠይቅ የሚከተለውን መልስ እናገኛለን፡-

<አልቃዒዳ ወይንም ሽብርተኝነት> በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ማለትም በመንግሥት አልባዋ አገር ሶማሊያ እንቁላሉን እየጣለ ነው፤ ሣይፈለፈል ከዚያው ላይ ወይንም ባለበት ገምቶ እንዲቀር አሜሪካ ሰላም አስከብራለሁ በሚል የኢትዮጵያ ሠራዊት ከመግባቱ በፊት ቀድማ ገብታ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የሶማሊያ ፋኖዎች ያሜሪካንን ወታደሮች ገለው በሞቃዲሾ ጎዳናዎች ለመቀጣጫነት ሬሣቸውን በመጎተት ዘግናኝና አሣፋሪ የዘላን ተግባር ፈፀሙ፡፡ ይህ ድርጊትም ያሜሪካንን ባለሥልጣናት በእጅጉ አስቆጣቸው፡፡ አርፈው እንዲቀመጡም አላስቻላቸውም፡፡ የምር እነዚያን ፋኖዎች ለመቅጣት ታጥቀው ተነሱ፡፡ ይህንን የበቀል ቀመር ሲቀምሩም በነጭ ወታደር ሊቋቋሟቸው እንደማይችሉ ቀድመው አውቀዋል፡፡ በመሆኑም “እሾህን በሾህ” እንዲሉ ወይንም “ጥቁርን በጥቁር” ከዚያው ጎረቤታሞችን

አስበሳቸው ማስተናነቅ እንደሚቻል ስልት ቀየሱ፡፡ ለዚህ ስልትም ኢትዮጵያ ተመረጠች፡፡

ያ ወቅት ደግሞ ኢሕአዴግ በቅንጅት የተሸነፈበት ወቅት ስለነበር <ድምፃችን ይከበር> ባሉ ወጣቶች ላይ በወሠደው አሸማቃቂ የግድያ ርምጃ በዓለም ዙሪያ ውግዘትና ጩኸት የበዛበት በመሆኑ አይከፍሉ መሥዋእትነት ከፍሎ ወይንም አሜሪካ የጠየቀችውን ባውንታ ተቀብሎ ያንን አሥፈሪ ጊዜ ከሷ ሥር ተሸጉጦ ማለፍ ነበረበት፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ተፈላላጊዎች ጊዜ አገናኘቻቸውና ባሜሪካ ያፍሪካ ጉዳይ ኃላፊዋ በጄንዳይ ፍሬዘር በኩል በሚስጢር አለቀ፡፡ ከዚህ በኋላ አሜሪካ የቅንጅትን ጉዳይ ቀዝቃዛ ውሃ ቸለሰችበት፡፡ አንዲት ነገር ሣትተነፍስ <ውሾን ያነሳ ውሾ> ብላ ጭጭ እንዳለች ቀረች፡፡



ያውሮፓ ኅብረትን ወክለው የታዛቢዎች ሰብሳቢ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሚዝ

ያውሮፓ ኅብረትን ወክለው የታዛቢዎች ሰብሳቢ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሚዝ (በኢትዮጵያውያን አጠራር ሐና ጎበዜ) ጩኸት ውሃ በልቶት ቀረ፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር ጠ/ሚንስትር መለስ ለወት ያህል ፓርላማ አቅርበው ጦሩ አሸባሪዎችን የትም ይሁን የትም፣ ከገቡበት ገብቶ መዋጋት እንዳለበት ም/ቤቱን አሣምነው ሶማሊያ እንዲገባ ያስወሰኑት፣ ሀቁ ይኸ ነው፡፡





ከዚህ ውጭ ግን አሸባሪዎች ሶማሊያ ውስጥ ኖሩም አልኖሩ እሷ በራሷ ለኢትዮጵያ መቸም የማትተኛ አሸባሪ ነች፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ ኢሕአዴግ የሚጓዝበት ስህተትን በስህተት የማረም አባዜ ነው፡፡

ሶማሊያ የሠራዊታችን ዘው ብሎ መግባት ከቤንዚን ላይ ክብሪት እንደመጫር የሚቆጠር ነው፡፡ በሷ ምክንያት በተዘዋዋሪም ቢሆን ያረቡን ዓለም ጥርስ እንደሚያስነክሱብን መወቅ አለበት፡፡ ምንም ይሁን ሳትተነኩሰን በራሷ ችግር ተጠምዳ ባለችበት ወቅት ሽብርና ሽብርተኞችን ፍለጋ ሞቃዲሾ ድረስ መሄድ አልነበረብንም፡፡ የዚህ ሁሉ ስህተት ድምር ውጤት "የታላቁ መሪያችን" መሆኑ ደግሞ በግልፅ ሊታወቅ ይገባዋል፡፡ ወደፊት ወይ በኛ እድሜ ወይ ዘግይቶ ትውልድ እዳ ከፋይ እንደሚሆን ቅንጣት የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ እስከዚያው ግን እግዚአብሔር ተሸብረው ከሚያሸብሩና በሙት መንፈስ እንግዛችሁ ከሚሉ ይጠብቀን!!

<><><>



*የውሮፓ ኅብረትን ወክለው የታዛቢዎች ሰብሳቢ የነበሩት ወ/ሮ አና ጎሚዝ*

# ክፍል ሦስት

*አልሆን ብሎ ነገሩ ሲጠጥር*
*ሳቡት ካበውን የላላው ይወጠር!*

## አንቀጽ 39 እንደ ዋሥትና

አንድ ሰው ቤት ለመሥራት ሲያስብ መሠረቱ የሚያርፍበትን አፈሩን በሙያተኞች ማስመርመር አለበት:: የሚነቃ፣ የሚናድና የሚንሸራተት መሆን አለመሆኑን በጥንቃቄ ማወቅ አለበት:: መሠረቱ በጥሩ ሁኔታ የተጣለና ተዋቅሮ የተሠራ ቤት ላደጋ የተጋለጠ አይሆንም:: መሠረቱ በጥሩ ሁኔታ ያልተጣለና በሚገባ ተዋቅሮ ያልተሠራ ቤት ከሆነ ግን በትንሽ ነገር መፍረሱና መደረማመሱ ምንም ጥርጥር የለውም:: እንደዚሁም ሁሉ ለነገ እንዲተርፍ ሆኖ በሥርዓት ያልተዋቀረና መሠረቱን ያልጣለ መንግሥት ከሆነ መፍረሱና መደረማመሱ አይቀሬ ነው:: ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ይህንኑ ሀቅ አመላካች በመሆኑ አሥፈሪ ነው:: ጎሣን መሠረት አድርጎ በቋንቋ መሥፈርትነት የተዋቀረ በመሆኑ ለዘለቄታ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም::

የዘውዱ ሥርዓትም ሆነ የደርግ ኮሙኒስታዊ ሥርዓት የሕዝቦችን ጥቅምና መብት ሊጠብቁና ሊያስከብሩ ባለመቻላቸው ሊወድቁ ችለዋል:: ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም <አብዮታዊ ዴሞክራሲ> በሚል ፍልስፍና ቀፍድዶ በመያዝ ሕዝብ ፀጥ ብሎ ሲገዛ የሰላም አባት መስሎ በሸንበቆ ከዘራ ሊገዛ ሕዝብ <መብቴን> ብሎ ሲጠይቅ በጥይት እየቆላና ባሸባሪነት ስም እየወነጀለና እድሜ ልክ እየፈረደ ሊገዛ ከቶ አይቻለውምና እየገነባው ያለው ሥርዓት በድቡሽት ላይ የተሠራ ለመሆኑ እንኳን ሕዝቡ ኢሕአዴግ ራሱ ደህና አድርጎ ያውቀዋል::

ኢትዮጵያ ቢያንስ ከ85 በላይ የሚሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ጎሳዎችና ነገዶች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያሏት አገር ናት:: እነዚህ ብሔር





ብሔረሰቦች፣ ጎሳዎችና ነገዶች ካራት የነገድ ሥሮች የተገኙ ናቸው:: እነሱም:-

1.ሴም 2. ኩሽ 3. ዖሞዎ 4. ናይሎቲክ ናቸው:: በመሠረቱ የዚህ ጽሑፍ ዓላማና ተልዕኮ ስለኢትዮጵያውያን ነገዶችና ጎሳዎች ምንነት ተንትኖ ለማስረዳት አይደለም:: ትልቁ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከነዚህ አራት የነገድ ሥሮች የተገኙ መሆናቸውንና የደም ትሥሥር ያላቸው መሆኑን ጠቁሞ ለማለፍና ተገንጥለውም ለየብቻቸው ሊኖሩ እንደማይችሉ አእምሮ ላላቸው ግንዛቤን ፈጥሮ ለማለፍ ነው::

እንግዲህ ከነዚህ አራት የዘር ግንዶች የተገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ጎሳዎች ከረጅም ጊዜ ጀምረው ባንድ የመንግሥት ጥላ ሥርና ባንድ መልከዓምድር አብረው በመኖራቸው የደጋው ወደ ቆላው በመውረድ፣ የቆላው ወደ ደጋው በመውጣት በጦርነት፣ በንግድ በደጅ ጥናት፣ የጌታ በማደር፣ በፍልሰት፣ በስደት፣ ከቀያቸው በመራቅ አንዱ ከሌላው በመጋባትና በመዋለድ የደም ውህደትን ፈጥረዋል:: በመሆኑም ዛሬ ንፁህ ኦሮሞ ነኝ፣ ንፁህ ትግሬ ነኝ፣ ንፁህ አማራ ነኝ፣ ንፁህ የዚህ ጎሳ ወይንም የዚያ ነገድ አባል ነኝ የሚሉ ካሉ እነሱ የዋሆች ናቸው፤ ወይንም እንደ ሕወሓት አባላት በዘር በሽታ የተለከፉ ናቸው:: ለደም ውህደታችን ትልቁ ማስረጃችን ደግሞ የጠይም ውቦች መሆናችን ነው::

ጠይምነት እንዴት? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የዓለም ሕዝቦች የዘር ግንዶች ሦስት ናቸው ተብሎ ይታመናል:: እነሱም:-

1. *ነጭ - ያውሮፓ ሕዝቦች አባት*
2. *ብጫ (ቀይ) - የኤዥያና የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝቦች አባት*
3. *ጥቁር - ያፍሪካ ሕዝቦች አባት ናቸው ተብሎ ይነገራል:: ይህ ሲባልም ቀለማቸውን (መልካቸውን) መሠረት ተደርጎ እንጂ በሰው ዘርነታቸው የተለያዩ አንዱ ከሌላው ትስስር የላቸውም ማለት አይደለም::*

እንግዲህ ጠይምነት እንዴት ለሚለው ጥያቄ መልሱ ኢትዮጵያኖች ከጥቁርና ከነጭ ይበልጠውንም ካጎራባች ሀገራት ካረቦቹና ከሕንዶቹ በቀይ ባሕርና በዔደን የባሕር ሠላጤ በንግድም፣ በፍልሠትም፣ በስደትም ወደ አፍሪካ ምድር ሽገር እያሉ ከኗሪው ጥቁር ሕዝብ ጋር በመጋባትና በመዋለድ ውብና ማራኪ የሆኑ የጠይም ፍልቅልቅ ሕዝቦችን ፈጠሩ:: ያልጠቆሩ፣ ያልነጡ፣ ወይንም ብጫ ያልሆኑ፤ በመጠንም ያልረዘሙ፣ ያላጠሩ ልከኛ ቁመት ያላቸው ተገኙ::

ይህ ጠይምነትም ባጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘ መልክ አይደለም፡፡ የረጅም ጊዜ አዝጋሚ የታሪክ ጉዞን ያስቆጠረ ነው፡፡ ይህ ሂደት ዛሬም ቢሆን አልተቋረጠም፤ እንደ ቀጠለ ነው፡፡ ለዚህም ነው የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝቦች <አፍሮ አሻርያን> እየተባሉ የሚጠሩት፡፡

ታዲያ ዛሬ ዓለም እንደ ሙዳይ እየጠበበች በመጣችበት ወቅት <የዚህ ጎሳ፣ የዚያ ብሔረሰብ> እየተባባልን ቡድን ፈጥረን በጥላቻ የጎሪጥ መተያየታችንና መፋጠጣችን ለምን ይበጅ ይሆን? ዘመኑ ዘመነ ቴክኖሎጂ በሆነበት ወቅት እኛ ወደ ኋላ መቅረታችን ሊቆጨን ሲገባ፣ ጠላታችንም ኋላ ቀርነታችን ሆኖ ሳለ እሱን አንድ ሆነን ታግለን ማሸነፍ ስንችል አንዱ ጎሳ የሌላው ጎሳ ጠላትና ደመኛ እንደሆነ አድርገን በሕዝቦች መሀከል የጥላቻ መርዝ እየረጨን በጨለማ ውስጥ እንደሚከንፉ የሌሊት ወፎች መሆናችን አሣሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ቢበቃን በተገባ ነበር፡፡ ግን የሚበቃንና የሚጠቅመን አልሆነም፡፡ ጎዡዎቻችን ገና ሰላም አልናፈቀቻቸውም፡፡

ገና ከማለዳው ያንድ መንደር ልጆች በወጣትነት ስሜት ቂምና በቀልን ቋጥረው በመሠባሰብ የመግቢያ በሩን እንጂ የመውጫ በሩን በቅጡ ሣያስተውሉ ያረጀ ያፈጀ ኮሚኒስቶች አላምጠው የተፉትን <የብሔር ጭቆና> በሚል <እስከ መገንጠል> የሚያደርስ መርህ ነድፈው መንቀሳቀሳቸው ሕወሓቶች ትልቅ ጥፋት ነበር የሠሩት፡፡ ሕወሓቶች የትግራይን ክልል ከሌላው የኢትዮጵያ አካል ገንጥለው እንደ ሀገር ለማቆም የጥላቻ ሥንቅ ሰንቀው በረሃ መግባታቸው ዛሬም ድረስ ያለቀቃቸው ትልቅ የዘር በሽታ ነው የተጠናወታቸው፡፡ በምንስ መመዘኛ ነው "የትግራይ ነፃ አውጭ" ተብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ መሆን የሚቻለው? ጠይቁ፡፡

21 ዓመታት በመንግሥትነት ተጉዘው እንኳን ከጎሣ አምላኪነት አለመላቀቃቸው በራሱ ክፉ የዘር ህመም እንደተጣባቸው በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡

የሕወሓት አባላት ገና ከመነሻቸው <የብሔር ብሔረሰቦች ጭቆና> ይዘው በረሃ ሲገቡ መፍትሔው <እስከ መገንጠል ድረስ> እውን ማድረግ ነው ብለው አምነዋል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና ሠጥተዋል፡፡ ኢሕአዴግ <እስከ መገንጠል ድረስ> መብት የሚሠጠውን አንቀጽ 39ኝን ሲያፀድቅ አንድ አዛውንት ሙስሊም ከመደሰታቸው የተነሣ እየዘለሉ ባዳራሹ ውስጥ ሲቧርቁ የራሳቸው ቆብ (ኩፍያ) ወልቆ ነበር፡፡ ዛሬ እኒያ አዛውንት ሙስሊም ምን ያህል እንደ ተሣካላቸውና ምን እንዳገኙ





አናውቅም፡፡ ምናልባትም ሳያልፍላቸው አልፈው ይሆናል፡፡ ለሕዝቡ ግን ጠብ ያለለት ነገር የለም፡፡ ኢሕአዴግ <እስከ መገንጠል> መብት የሚሰጠውን አንቀጽ 39ኝን ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና ሲሠጥ አምኖበትና የዘለቄታ መፍትሄ ይሆናል ብሎ አስቦ ሣይሆን ሕዝቦች በጥርጣሬና በጥላቻ እስበሳቸው የጎሪጥ እየተያዩ ሲፋጠጡ የሥልጣን ዕድሜው እንደሚረዝም በማመኑ ነው፡፡ በመሆኑም ዛሬ አንቀጽ 39ኝን ለሥልጣኑ ማቆያ እንደ ዋሥትና እየተጠቀመበት ነው፡፡ <እኔ ካልገዛኋችሁ ኢትዮጵያ ትፈራርሳለች> እያለም ያስፈራራል፡፡ የሥልጣን ተቀናቃኞቹ እንኳን እሱ በቀደደው መስኖ እየፈሰሱ፣ አንድ ሆነው ስለአገር ማሰብ ተስኗቸው ግን ደግሞ እሱን <ጎሠኛ> እያሉ ሲያወግዙ ትንሽ እንኳን ሀፍረት አይሠማቸውም፡፡

በመሠረቱ እንደ ኢትዮጵያ ያለችን የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ለመምራትና ለማሥተዳደር ጥበብንና ብልሃትን ይጠይቃል፡፡ የመጀመሪያው ምንም አይነት ጎሣዊ አድልኦ ሣያደርጉ በእኩልነት መምራት ሲቻል ነው፡፡ የሕወሓት <ልሂቃን> ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ መርህ አይዋጥላቸውም፤ አያውቁትም፡፡ በመሆኑም አንዱ ብሔር የሌላው ብሔር ጠላት እንደሆነ በመቀስቀስና በማራገብ <እስከ መገንጠል> የሚል መርህ በመቅረጽ ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና በመሥጠት የገዛ ዜጎቹን አቧድኖ ለማፋለም የሚያፋጥጥ መንግሥት በዓለም ላይ አለ ከተባለ የኢሕአዴግ መንግሥት የመጀመሪያ ነው፡ በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ ይካሄዱ የነበሩት ደም አፋሳሽ የእሰበሰ ጦርነቶች <ገብር አልገብርም> በሚል እንጂ <እገነጠላለሁ አትገነጠልም> በሚል አልነበረም፡፡

ሕወሓት በኋላ ባምሳሉ የፈለፈላቸውን ኃላፊነት የመሸከም አቅምና ችሎታ የሌላቸውን ከጎኑ በማሰለፍ ኢትዮጵያውያንን በጎሳ ለማስተናነቅ ሲነሣ ቀደምት ነገሥታት የሠሯቸውን መልካም ተግባራት አሻራቸውን ከታሪክ ማኅደራት ለመፋቅ እንዲያመቸው ስንት በጎ ነገሮች እያሉ ለማሣመንና ተቀባይነት እንዲያገኝ ክፉ ክፉ ነገሮችን እየነቀሰ በማውጣት ባብዛኛውም እንደ ብሥራት አማራ የፈጠራ ድርሳናትን በቅጥፈት በማጨቅ አንዳንድ ጊዜም ዶክሜንተሪ ፊልሞች ሣይቀር በማቅረብ አንዱን ብሔር ገዥና ረጋጭ ሌላውን ብሔር ተገዥና ተረጋጭ በማስመሰል መስበክና በሕዝቦች ሕሊና ውስጥ ጥላቻና ከፋትን ማስረፅ ነው፡፡ የዚህ እኩይ ተግባር ሰለባ የሆኑት ቀደም ሲል እንዳየነው በብሥራት አማረ ሣይቀር የተንበሳቆሉት የመጀመሪያው አፄ ምኒልክ ናቸው፡፡ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ቢሆኑ የሕይወት ዋጋ ቢከፍሉም የጎሳ በሽታ ቁውና አፅማቸው ከመወቀስ

አላመለጠም፡፡ ዘመኑ ርቆ ሌላ ዘመን ውስጥ ያለን ብንሆንም አፄ ቴዎድሮስም ከመወቀስና ከመዘለፍ ይባስ ተብለውም በሚያስገርም ሁኔታ ባሪያ ፈንጋይም ነበሩ ተብለዋል፡፡ ይህንን ሀቅ ለመረዳት በቅንጭብጫቢም ቢሆን ነገሥታቱ የነበሩበትን ዘመንና የተጓዙበትን አስቸጋሪና የፈተና ወቅት እንዴት እንዳለፉትና እንዴት እንደተጋፈጡት ለመዳሰስ ይሞክራል፡፡ እግረመንገዳችንም የዘመናችን የቅጥፈት ሥንክሳር ማጋለጥ የግድ እየሆነ መጥቷል፡፡

◇◇◇





# አፄ ቴዎድሮስ



*አፄ ቴዎድሮስ*

እንደሚታወቀው አፄ ቴዎድሮስ በተነሱበት ወቅት የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ የተለየ መልክና ቅርፅ ነበረው፡፡ ባገር ውስጥ ማዕከላዊ መንግሥት ተዳክሞ በጎጥ መሣፍንት ኢትዮጵያ እየታመሠች ነበር፡፡ አንዱ ራስ ወይንም ደጃዝማች ሌላውን ራስ ወይንም ደጃዝማች <ገብር አልገብርም> በሚል በየቀኑ ፍልሚያ የሚገጥሙበት ወቅት ነበር፡፡ በዚያ ዘመን ገበሬው አርሶ ማምራት፣ ወልዶ መሣም፣ አሣድጎ መዳር፣ ነጋዴው ነግዶ ማትረፍ የሚቻልበት አልነበረም፡፡ ከሠቆቃውና ከምሬቱ ብዛት የተነሣ ኢትዮጵያኖች ሰው ሆነው የተፈጠሩበትን እለት ይረግሙ ነበር ይባላል፡፡

በውጭ የነበረው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን፣ ኤሽያን፣ ላቲን አሜሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ እየተቀራመቱ

# አፄ ቴዎድሮስ



*አፄ ቴዎድሮስ*

የነበሩበት ወቅት ነበር። ኢትዮጵያ ግን ነፃና ሉዓላዊት ሀገር የነበረች ቢሆንም ከቅኝ ገዥዎች በከፋ መልኩ በመሣፍንት እየታመሰች ነበር።

እንግዲህ ካሣ (አፄ ቴዎድሮስ) በዚህ ውጥንቅጡ በወጣበት ወቅት ነበር የሕዝብ እንባና ሰቆቃ አምጦ የወለዳቸው። በመሆኑም በዚያን ዘመን የገነኑ የጎጥ መሣፍንትን እስከነ ሥርዓታቸው መንግሎ ለመጣል ቴዎድሮስ ጨከን ያለ ርምጃ ከመውሰድ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። የሆነውም ይኸው ነበር። ይሁን እንጂ የዘመነ መሣፍንትን አስከፊነት በቅጡ ያልተረዱ ወገኖች አፄ ቴዎድሮስን ከልክ ያለፉ ጨካኝና አረመኔ አድርገው ይሥሏቸዋል። ሀቁ ግን አፄ ቴዎድሮስ ሩኅሩኅም፣ አዛኝም፣ ምህረትን የሚያውቁ እንደነበሩ የሣቸው እሥረኛ የነበረው ዶ/ር ሄኔሪ ብላንክ ሣይቀር መሥክሮላቸዋል። ባንድ ወቅት አንዲት ምንትዋብ የምትባል ሴት:-

*"ሥጋም እንዳያምረኝ ቋንጣ ሰቅያለሁ*
*ሲሻኝ ከወንድሜ ካባቴ አበላለሁ።*
*ሺ ፈረስ ከኋላው ሺ ፈረስ ከፊቱ*
*ይህን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ!*
*ይህንን ሲሰማ ያጎራል ላመሉ*
*ማናትም ቢላችሁ ምንትዋብ ናት በሉ!"* በማለት መሣደቧ ለቴዎድሮስ ይነገራቸውና ተይዛ ትቀርባለች። መኳንንቱ ገሚሱ <ንጉሣችን ተሣድባለችና መሠቀል አለባት> ሲል ቀሪው ደግሞ <የለም ሴት ነችና ባይሆን ዳግመኛ እንዳይለምዳት አርባ ጅራፍ ተገርፋ ትለቀቅ> በማለት የየራሱን ፍርድ ይሠጣል። ቴዎድሮስ የመኳንንቱን አስተያየት ካዳመጡ በኋላ ወደ ሴትዮዋ መለስ ብለው:-

"እቴ፤ እንዲያው ምን በድየሽ ነው የምትሰድቢኝ?" በማለት ሲጠይቋት:-

"አባ ታጠቅ፤ ከዚህ የበለጠ ምን ሊበድሉኝ ኖሯል? ወንድሜን፣ አባቴን ገለውብኛል" ስትል መለሰችላቸው። በዚህ ጊዜ ስሜታቸው ይነካና አንገታቸውን ደፍተው ለትንሽ ጊዜ ተከዘው ከቆዩ በኋላ ቀና በማለት ወደ መኳንንቱ አትኩረው እየተመለከቱ:-

"ታዲያ ይህንን የመሰለ በደል ፈጽሜባት እኔን እንድታሞግስ ትፈልጉ ኖሯል?" በማለት ከወቀሷቸው በኋላ ዘጌ ማደሪያ ጉልት እንደ ሰጧት ዶ/ር ሄነሪ ብላንክ ጽፏል። ይሁን እንጂ ሴትዮዋ በሰጧት ጉልት አልተጠቀመችበትም። እስከ እልፈተ ሕይወታቸው ድረስ በሄዱበት እየሄደች ግብረ በላ ሆና ደስ ሲላት ስታሞግሳቸው ሲከፋት ደግሞ ስትሰድባቸው





ኖራለች። ይህ እንግዲህ ምህረትንና ይቅርባይነትን የሚያውቁ ለመሆናቸው ማረጋገጫ ነው።

ሌላው ደግሞ አፄ ቴዎድሮስ እንደማናቸውም ሰው የሚያዝኑና የሚጨነቁ መሆናቸውን የገለፁበት አጋጣሚ የሚወዷት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች በሞት ሲለዩዋቸው:-

*"እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሣትሄድ*
*እቴጌ ተዋበች ሚስት ናት ገረድ?*
*እጅግ ሥራ አዋቂ ትናትና ሞተች*
*መድኃኒቱን ምሣ ታበላኝ ነበረች!"* ሲሉ ስቅስቅ ብለው ማልቀሳቸው ትዕይነገርላቸዋል።*(አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት ገጽ 185)*

እንዲሁም ብላንክ ግሥተኛነታቸውን ሲገልፅ እንዲህ ብሏል "አፄ ቴዎድሮስ በራሳቸው ጉዳይ መታገሥ ይችላሉ። ባገር ጉዳይ ላይ ግን ፈጽሞ ትእግሥት የላቸውም" ሲል አግራሞቱን በተመሣሣይ መጽሐፍ ገልፆል።

አፄ ቴዎድሮስ ሌላው ታላቅነታቸውን ያስመሠከሩበትና ላገራቸው ቀናዒ እንደነበሩ የገለፁበት አጋጣሚ ደግሞ ሣያወላውሉ በራሳቸው ላይ የወሰዱት ቆራጥ ርምጃ ነበር። ንጉሥ ነገሥቱ የሚመኩበትና የሚተማመኑበት የጦር መሪያቸው ፊታውራሪ ገብርዬ ከሮበርት ናፒዬር ጦር ጋር ተፋልሞ መሰዋቱንና በርካታ ታማኝ ወታደሮቻቸውም መሞታቸውን ሲነግሯቸው እጅግ አድርገው አዝነው፤ አግተዋቸው የነበሩትን ወይንም ለፍልሚያው ምክንያት የሆኑትን ያውሮፓ እስረኞችን ፈተው ከለቀቋቸው በኋላ ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው በሁለት እጆቻቸው ራሳቸውን ደግፈው አቀርቅረው ማዘን ሲጀምሩ ራስ እንግዳ:-

"ለምን ያዝናሉ? እነዚህን ነጮች እንመልሳቸውና ገለን ወይንም ተዋግተን እንሙት!" ሲሏቸው ተቆጥተው:-

"አንተ ጅል ባለፈው ሁለት ቀናት ውስጥ የፈጀሁት ሰው አይበቃኝም? እነዚህን ነጮች ገድዬ አበሻን በደም እንዳጥባት ነው የምትፈልገው?" ብለው እንደመለሱላቸው ብላንክ በመጽሐፉ በገጽ 30-31 አብራርቶ ጽፏል። በመጨረሻዋ ሰዓት ይህንን ማለታቸው በራሱ ለወገንና ለሀገር ምን ያህል እንደሚጨነቁና ኃላፊነት እንደሚሠማቸው በቂ የሆነ ማረጋገጫ ነበር።

አፄ ቴዎድሮስ ይህንን ሁሉ አድርገው በመጨረሻ መሸነፋቸውን ሲያውቁ አንድ ያበሻ ንጉሥ በነጭ ወታደር መማረክን ከሞት በላይ ሞት ስለሆነባቸውና በተለይም ለትውልድና ለታሪክ እንዲህ ዓይነት አሣፋሪ ታሪክ ላለማስቀመጥ ሲሉ በራሳቸው ላይ የወሰዱት ቆራጥ ርምጃ ዝንተ ዓለም የትውልድ መኩሪያ ሆነው ይኖራሉ:: ይህኑ ርምጃ አወሳሰዳቸውን ብላንክ አድንቆ ጽፏል:: አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያም <አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት> በተባለው መጽሐፋቸው ብላንክን ዋቢ ጠቅሰው በገጽ 402 ላይ አስፍረዋል:: በወቅቱም የሚከተለው ስንኝ ተቋጥሮላቸዋል:-

*"ገደልን እንዳይሉ ሙተው አገኟቸው*
*ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው*
*ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?*
*በመቅደላ በኩል ጩኸት በረከተ*
*የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ::*
*የሸዋን መኳንንት ሲንቁ ሲንቁ*
*የትግሬን መኳንንት ሲንቁ ሲንቁ*
*ወንድ ያለፉስዎ ገለውም አያውቁ!"*

እንግዲህ አጼ ቴዎድሮስ አገርን ለማማከልና ከሁሉም በላይ ይችን አገር የጦር መሣሪያ የኢንዱስትሪ ባለቤት ለማድረግ ላይ ታች ሲባክኑ ከነጮች ጋር በገቡት አታካራ ሕይወታቸውን አሣልፈው እያሉ ይህንን ችግራቸውን በቅጡ ያልተገነዘቡ <ቤት ዘግተው አቃጠሉ፤ በገደል ላይ ጣሉ፤ ወዘተ. . .> በማለት እጅግ በራቀ ዘመን ተራምደው ተራ ዘለፋ ሲዘልፏቸው መስማት ሕሊናን ይሰቀጥጣል::

አሁን ባለንበት ዘመን እንኳን ነፍሳቸውን ይማረውና ታዋቂው የታሪክ ምሁር ደጃዝማች ዶ/ር ዘውዴ ገ/ሥላሴ በሃይማኖት ዓለሙ አቀነባባሪነት አፅማቸውን ጥላሸት ለመቀባት ሲባል ብቻ ላንድ ምሽት በተዘጋጀ የቴሌቪዥን መድረክ ተራ ሽፍታና ባሪያ ፈንጋይ እንደነበሩ እያንበሳቆሉ ሲገልፅዋቸው ሕሊናው ያልቆሰለ ንጹሕ ዜጋ አልነበረም::

ለመሆኑ ምሁሩ አፄ ቴዎድሮስን በዚህ የጎሣ ሥርዓት ባሪያ ፈንጋይ ተራ ወንበዴ አድርገው ለምን አቀረቧቸው? ዓላማውስ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በወቅቱ መነሣታቸው አልቀረም:: ዓላማውና ተልዕኮው ይህንኑ መከረኛ አማራ ለማሸማቀቅና በሳቸው ታሪክ እንዳይኮራና አርማቸውን ወራሽ ትውልድ እንዳይፈጠር ቅስሙን ሠብሮ አንገቱን ደፍቶ እየቆዘመ የሚገዛ ዜጋ ለማፍራት ነው:: ይህ ዓይነቱ ትንኮሣ ግን ለዛሬ አንድነታችን





ብቻ ሣይሆን ለነገም ጉዟችን ጭምር የከፋትን ሥንቅ የሚያስቋጥር ነው:: ባጭሩ የደጃዝማቹ ንግግር ለማንም፣ ለምንም አይጠቅምም:: እንዲህ ዓይነቱ ተራ ዘለፋም ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው አዛውንት ምሁር አንደበት በመሠንዘሩ የጎሠኝነትን ዝቅጠትና መጥፎነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነበር::

እንደ እውነቱ ከሆነ በየታሪኩ ተጠቅሶ የምናገኘው ቴዎድሮስ የባሪያ ንግድን ወይንም ሽያጭን አጥብቀው ይቃወሙ እንደነበር ነው:: ደጃዝማች ዘውዴ ግን ገልብጠው ነገሩን::

እነ አቶ መለስስ 7 ሆነው ኋላቀር ጠመንጃ ይዘው አይደል እንዴ ከደደቢት ተነስተው ለመንግሥትነት የበቁት? ምንድን ነው አዲስ ነገር የሆነው? ሕወሓት የሠራው ከሆነ እንደታምር ሊነገር የሌሎች ሲሆን ግን በማፈሪያነት ሊጠቀስ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ጠይቁ::

ወቃሾቹና አውጋዦቹ እሳቸው ፈፀሙት ከተባለው ድርጊት እጅግ ርቀው ሰብዓዊ ርኅራኄ የሰፈነባቸው ቢሆኑ ኖሮ ሊወቅሷቸውና ሊያወግዟቸው ተገቢ በሆነ ነበር:: ዓላማው ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት ታሪካቸውን ጥላሸት ለመቀባትና ወራሽ ለማሣጣት በመሆኑ በጣም ያሣዝናል።

አሁን ባለንበት የሥልጣኔ ደረጃ ላይ ደርሰን እንኳን ሻዕቢያ በ1980 ዓ.ም በምዕራብ ኢትዮጵያ አነግን ከፊት በማስቀደም አሶሳ ላይ በሠፋሪ ወገኖቻችን ላይ የፈፀመው አሠቃቂ እልቂት ለሕሊና እጅግ አድርጎ የሚሰቀጥጥ ነው:: ስብሰባ ብሎ ጠርቶ ካንድ አዳራሽ ውስጥ በማጎር በውጭ በመቆለፍ አቃጥሏቸዋል:: የሕወሓት የትግል ጓድ ወይንም አጋር እስከዚህ ድረስ የከፋ አረመኔ ነው:: ሻዕቢያ በሰብዓዊ ሚዛን የማይቀመጥ መሆኑን በአይደር ት/ቤት ህፃናት ላይ ያደረሰውን የቦምብ ድብደባ አይተናል:: ታዲያ ይህን የመሰለ ወንጀል በዚህ ሥልጡን ዘመን እየተፈፀመ አፄ ቴዎድሮስን የመውቀስና የመኮነን ምን የሞራል ብቃት ይኖረናል? ይህም ሆኖ ግን አፄ ቴዎድሮስ ጥፋት አላጠፉም ብለን በጭፍን አንከራከርም:: በርካታ ስህተቶችን መሥራታቸው እውነት ነው:: ይሁን እንጂ አንዲት ኢትዮጵያን ለማማከል ሲሉ ይዘውት ከተነሱት ራእይ ጋር ከዘመኑ ርቀትና ኋላ ቀርነት አንፃር በማመዛዘን ልንገነዘብላቸው ይገባናል:: ከዚህ አልፈን ሥንጥር እየፈለግን ታሪካቸውን ጥላሸት መቀባቱ ግን ለዚህ ትውልድ ፋይዳ

የለውም:: አለው ከተባለም የበቀልን ሥንቅ ማስቋጠር ነው:: ይህ ደግሞ አይጠቅመንም::

<><><>





# አፄ ዮሐንስ 4ኛ



አፄ ዮሐንስ 4ኛ

በዝብዝ ካሣ (በዝብዝ የፈረሣቸው ስም ነው) እንደዚያን ዘመን ወጣቶችና ጎልማሶች ከትውልድ ቀያቸው (ከተምቤን) ወደ ጎንደር በመሄድ ያፄ ቴዎድሮስ ጭፍራ (ወታደር) ሆኑ:: ቴዎድሮስ ለወታደሮቻቸውና ለመኳንንቶቻቸው ማዕረግና ሹመት ሲሰጡ ለካሣም የባላምባራስነት ማዕረግ ሰጥተዋቸው ነበር:: ካሣ ምርጫ ግን በዚህ ማዕረግ ባለመርካታቸው አኩርፈው በመከዳት ወደ ተምቤን ተመለሱ::

ካሣ ምርጫ ተምቤን ውስጥ ትንሽ ከቆዩ በኋላ ራሳቸውን በራሳቸው ደጃዝማች ካሣ ብለው ማዕረግ በመሥጠት ወይንም በመሾም መንቀሳቀስ ጀመሩ:: ይሁን እንጂ የጄኔራል ሮበርት ናፒየር ሖር ወደ ኢትዮጵያ እስከ

# አፄ ዮሐንስ 4ኛ



አፄ ዮሐንስ 4ኛ

ዘ ካሣ (በዝብዝ የረረሣቹው ስም ነው) እንደዘየን

መጣበት ጊዜ ድረስ ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ውስጥ ለውስጥ ከማሴር ያለፈ የትግራይን ሕዝብ ግብር እንዳይገብር አሣምፀው ለጦርነት የተሰለፉበት ጊዜ የለም፡፡ ቴዎድሮስም ለካሣ ሸፍትነት ክብደት ሠጥተው ወደ ትግራይ ጦር አላዘመቱባቸውም፡፡ በሌሎች ከባድ ካባድ ችግሮች ተጠምደው ስለነበር የካሣ ሸፍትነት ይህንን ያህል ክብደት እንዳልሰጡት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## "ምን ብጠላው በወንድሜ ላይ ደም አልይበት!"

እንደሚታወቀው አፄ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዘመናዊ ሥልጣኔ በነበራቸው ጉጉትና ቀናዒነት የተነሣ ከእንግሊዝ ጋር በገቡት የከፋ ውዝግብ ምክንያት እንግሊዝ ቴዎድሮስ በመያዣነት አግተው የያዟቸውን ዜጎቻቸውን ለማስለቀቅ በጄኔራል ናፒየር የሚመራ ጦር በ1860 ዓ.ም መጥቶ ዘይለ ወደብ መሥፈሩ ተረጋገጠ፡፡ ይኸኔ ከትግራይ መኳንንት መሀከል በግንባር ቀደምትነት ከጄነራል ናፒየር ጋር ተላልከው ለመንገድ መሪነት፣ ለሥንቅና ለመረጃ አቅርቦት የተገኙትና ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑት ካሣ ምርጫ ነበሩ፡፡ በመሆኑም የጄኔራል ናፒየር ጦር ከዘይላ ወደብ ተነስቶ በሠናፌ፣ ባጋሜ፣ በዋርላ ደላንታ አድርጎ መቅደላ አምባ እስከሚደርስ ድረስ በመንገድ አንዳችም እንቅፋት አልገጠመውም ነበር፡፡ የዚህ ምክንያቱ ያገር ተወላጅ መንገድ መሪና መረጃ አቀባይ በማግኘቱ ነበር፡፡

አፄ ቴዎድሮስ በዚያች በመጨረሻዋ ፈታኝ ወቅት ሰው ሲፈልጉ ሰው ማጣታቸውና የገዛ ወገናቸው ጠላትን መንገድ እየመራና የሥንቅ አቅርቦት እያቀረበ ማየት ካሣዘኙ ታሪካቸው መሀከል እጅግ የከፋው ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ብዙ ጎልታ ከምትታወቅባቸው በጎ ምግባራት መሀከል አንዱና ዋናው በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የከፋ ደም መፋሰስ ቢደርስም እንኳን መኳንንቱ የውጭ ጠላት ሲመጣ በጭራሽ ቀዳዳ አይከፍቱም ነበር፡፡ "ምን ብጠላው በወንድሜ ላይ ደም አልይበት!" በማለት አንድ ሆነው ወራሪውን ጠላት ረግጠው ያስወጡ ነበር፡፡ ይህንን የቆየና የዳበረ ወግ ካሣ ምርጫ የጄኔራል ናፒየርን ጦር ሥንቅ በማቀበልና መንገድ በመምራት ሠበሩት፡፡ አላፊውን ቴዎድሮስን መጥላትና የማያልፈውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ክብር ማዋረድና ያገርን አንጡራ ሀብት ማዘረፍ ታሪክ ይቅር የማይለው ወራዳ ተግባር ነበር ካሣ ምርጫ የፈፀሙት፡፡ ምንም ያህል የሥልጣን ጉጉት ቢኖርባቸውም የጠላትን ጦር መንገድ ሊመሩ ባልተገባቸው ነበር፡፡ ግን ተገባቸውና እየመሩ መቅደላ አምባ አደረሱት፡፡





እንደ እውነቱ ከሆነ ታሪከም እንደሚጠቁመን ካሣ ምርጫ የናፒየርን ጦር በደጋው አገር እየመሩ መቅደላ ባያደርሱት ኖሮ ሊመጣ አስቦ የነበረው ታቹን ባፋር በረሃ ነበር፡፡ በዚያ በኩል ቢመጣ ኖሮ ወታደሮቹ ውሃ ጥሙንና የበረሃውን ነዲድ ችለው ወደ ደጋው አገር የመዝለቃቸው ሁኔታ አጠራጣሪ ነበር፡፡ በረሃውን ይወጡታል ቢባል እንኳን በረሃብና በውሃ ጥም፣ እንዲሁም በበረሃ ነዲድ በጣም የተጎዱ ስለሚሆኑ የጦርነቱ ሁኔታ ሌላ መልክ ሊኖረው በቻለ ነበር፡፡

ለጠላት በር መከፈትንና ስለ መንገድ መምራት ስናወሳ ሊላም ሣንጠቅሰው የማናልፈው ቁስል አለ፡፡ ያ ቁስልም የማይጨው ጦርነት ከመፈንዳቱ ቀደም ብሎ የቀደማዊ ኃይለሥላሴ አማች (የልዕልት ዘነበወርቅ ባል) የምሥራቅ ትግራይ ገዥ የነበረው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ አገሩንና ንጉሠ ነገሥቱን በዚያች ፈታኝ ቀውጢ ወቅት ከድቶ ኤርትራ በመግባት ልክ ካሣ ምርጫ የናፒየርን ጦር እየመሩ መቅደላ እንዳደረሱት ሁሉ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣም ኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ በምትፈልግበት ወቅት የኢጣሊያንን ጦር እየመራ መጣ፡፡

ጄኔራል ናፒየር አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን በራሳቸው አጥፍተው የጦርነቱ ፍፃሜ ከሆነ በኋላ የዘረፈውን ዘርፎ የሚያወድመውን አውድሞ ለጉዞ ከመንቀሣቀሱ በፊት ለካሣ ምርጫ ለዋሉለት ውለታና ላበረከቱት ሁለንተናዊ አገልግሎት 12 ዘመናዊ መድፎች፣ 900 ሲናድር ጠመንጃዎች፣ ቁጥራቸው በትክክል ያልታወቁ ሽጉጦችና ከውትድርና ሙያ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ በርካታ ቁሳቁሶችን (እንደ ባይሮክለር መነፅር የመሳሰሉትን) በገፍ ካሥታጠቃቸው በኋላ እነዚህን ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የሚያስተምሩና ጦራቸውንም ዘመናዊ ውትድርናን የሚያሠለጥኑላቸው ሁለት የእንግሊዝ ወታደሮችን (ኪርክሃምና ሉዊ የተባሉ) ካሥቀረላቸው በኋላ በመጨረሻ እንዳመጣጡ ወደ ሀገሩ ሲመለስም በክብር አጅበው አሸኛኘት አድርገውለታል፡፡

ጄኔራል ናፒየር ጓዙን ጠቅልሎ ካገር እንደወጣ በዚያን ወቅት በሠራዊት ብዛትም ሆነ ባደረጃጀት ከነበሩት መኳንንት መሀከል የላስታው ዋግ ሹም ጎበዜ የተሻሉ ስለነበሩ ጊዜ ሳይሰጡ ተሻምተው ወዲያውኑ <አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ንጉሠ ነገሥት ዘ-ኢትዮጵያ> ተብለው ነገሡ፡፡

ካሣ ምርጫ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ጄኔራል ናፒየር አሰታጥቋቸው ቢሄድም የዋግ ሹም ጎበዜን ያህል ሰው ስላልነበራቸው ያፄ ተክለ ጊዮርጊስን

ንጉሠ ነገሥትነት ተቀብለው ራሳቸውን ሲያደራጁ ቆይተው በመጨረሻ እወጣዋለሁ ባሉበት ወቅት <አልገብርም> በማለት ማመፃቸውን በይፋ አስታወቁ። በዚህ ወቅት አፄ ተክለ ጊዮርጊስ <አትችለኝም። ሠራዊቴ እንደዚህ ጤፍ ብዙ ነው> ብለው አንድ አቅማዳ ጤፍ ባህያ አስጭነው ላኩባቸው። በዝብዝ ካሣ በበኩላቸው <ሠራዊትዎ እንደ ላኩት ጤፍ ብዙ ቢሆንም በታጠቁት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ እቆላለዎታለሁ!> በማለት ጤፉን ቆልተው መልሰው ላኩላቸው።

በዚህ ሁኔታ የዛቻና የማስፈራራት መልዕክት ከተለዋወጡ በኋላ ሁለቱም ሊለዝቡ ባለመቻላቸው አፄ ተክለጊዮርጊስ ከላስታ ተነስተው ወደ ትግራይ በመዝመት ዓድዋ አሰም ወንዝ አጠገብ ፍልሚያ ገጠሙ። እውነትም ካሣ ጤፉን ቆልተው እንደላኩት ሁሉ ያፄ ተክለጊዮርጊስን ሠራዊት ናፒየር ባሥታጠቃቸው ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ቆልተው ንጉሠ ነገሥቱም በፍልሚያው ላይ ተገደሉ። በዚሁ የጦርነቱ ፍፃሜ ሆነ። በነገራችን ላይ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሚስት የካሣ ምርጫ እህት ስለነበሩ አልቃሽ፡-

*"ጉዳዩ ወንድምሽ፣*
*የሞተው ባልሽ*
*ሐዘንሽ ቅጥ አጣ እኔ ምን ልበልሽ!"* ብሏቸዋል

# ካሣ ምርጫ አፄ ከሆኑ በኋላ የወሰዷቸው ርምጃዎች

ካሣ ምርጫ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ከገደሉ በኋላ <አፄ ዮሐንስ 4ኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ!> ተብለው ነገሡ። በዚህ ወቅት ደግሞ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ <አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ> ተብለው ነገሡ። ሁለት አፄዎች ባንድ ጊዜ ላንዲት አገር የሚቻልም፣ የሚታሰብም፣ የሚሆንም አይደለምና አንዱ ባጥቂነት መውጣት ስለነበረበት ለጦርነት ተሰላለፉ።

አፄ ዮሐንስ <ምታ ነጋሪት፣ ከተት ሠራዊት> ብለው ምኒልክን ለመውጋት ከትግራይ ተንቀሳቅሰው ወሎ ምድር ገቡ። ይሁን እንጂ የዚያን ዘመን የሃይማኖት አባቶች እንደዛሬዎቹ ጭልጥ ያሉ ጥቅም አሳዳጆችና በጎሣ የተመረዙ አልነበሩምና ለሃይማኖታቸው፣ ለእምነታቸው የበረቱ፣ የተከበሩ፣ የተፈሩና አንቱ የተባሉ ስለነበሩ ተደማጭነት ነበራቸው። በመሆኑም ሁለቱ





ወንድማማቾች ሥልጣን ለኔ ይገባኛል ምክንያት ደም በከንቱ መፋሰስ እንደ ማይገባቸው ግራ ቀኙን በያሉበት ከወቀሱና ከተቆጡ በኋላ ቀጠሮ ተይዞ ምኒልክ ወደ ወሎ እንዲጓዙ ተደርጎ ወሎ ውስጥ <ሊጨ ወይንም ሊቻ> ከተባለች ቦታ ሁለቱ አፄዎች ለዚሁ ተግባር ተብሎ ከተዘጋጀ ድንኳን ውስጥ ከታላላቅ የሃይማኖት አባቶች ጋር ገብተው ከብዙ ቆይታ በኋላ እንደገና ከድንኳኗ በመውጣት የርቁ ሁኔታ በምን ዓይነት መንገድ ይቋጭ ይሆን እያለ በጉጉት ለሚጠብቃቸው ሕዝብ ባዋጅ መልክ የሚከተለውን አስነገሩ፡-

"አፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" ሲባሉ ምኒልክ ደግሞ አንድ ደረጃ ዝቅ ብለው "ንጉሠ ሸዋ" መባላቸውን በተነገረና በተገለፀ ጊዜ ሕዝቡ ታላቅ ደስታና እልልታ አቅልጦ እንደነበር የእድሜ ባለጸጎች ይተርካሉ። ከዚህ ውጭ ሁለቱ መሪዎች በሌሎች ጉዳዮች ላይ ምን እንደተነጋገሩ የሚታወቅ ነገር የለም።

እንግዲህ ከፍ ብሎ እንደ ተመለከትነው እስበስ በሥልጣን ንጥቂያ ምክንያት የሚያፋጥጥ ዘመን ሲከሠት የሃይማኖት አባቶች የማስታረቅ፣ የማቻቻልና የመምከር፣ የመገሠፅ ተግባር ያከናውኑ ነበር። የሞራል ብቃትም ነበራቸው። "ሰዎች የሆኑ ሁሉ ሌሎችን እንደራሳቸው እንዲወዱና እንዲያከብሩ" የሐዋርያነት ተግባር ይፈፅሙ ነበር። በዚህ ዘመን ግን ይህ መልካም ሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባር ተገልብጦ "ሰዎች የሆናችሁ ሁሉ እንደ አውሬ እስበሳችሁ ተናከሱ!" በሚል ቃል የተተካ መስሏል። ዛሬ የሃይማኖት አባቶች እንኳንስ የተጣሉን ሊያስታርቁ ይቅርና እነሱ ራሳቸው ጠብ አቀጣጣይ ቤንዚን ሆነዋል። ሣይሞቱ የሞቱትና ዛሬ ሲሞቱ የሚያሠሩትን ሐውልት በቁማቸው ያስቆሙ እለት ነበር።

የዘመኑ ካህናትና ዳቆናት ኢሕአዴግ በሚያዘጋጃቸው የድጋፍ ሰልፎች ላይ በመገኘት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ከበሮ እየደለቁ፣ ከፊት ከፊት ሰልፉን የሚመሩ ናቸው። እንደነዚህ ያሉትን የሃይማኖት ሰዎች ጆን ሐዘወይ ስፔንሰር በመታዘብ እንዲህ ይሏቸዋል፡-

*". . .የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በርካታ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሚገኙባት ምትክ የማይገኝላቸውን ድርሳናትና ንዋየ ቅዱሳት ከመጠበቅ በስተቀር ማኅበራዊ ችግሮችን አልተገነዘቡም። ማይማንና ስስታም ካህናት ጊዜው እንዳልተለወጠ ሁሉ የተካበተ ሀብቷን ሙጭጭ ብለው ይዘዋል። ቤተክርስቲያኒቱ ከኢጣሊያን ፋሽሽቶች አገዛዝ ጋር እንዳደረገችው ሁሉ*

*ከኮሚኒስት ደርግ ጋርም ልክክ አለች!!"* በማለት ተችተዋቸዋል፡፡ *(ጥርስ የገባች አገር ገጽ 175)*

ስፔንሰር እንዳሉት እነዚህ የቤተክህነት አባቶች ከፋሽሽት ኢጣሊያና ከኮሙኒስት ደርግ ጋር ልክክ እንዳሉት ሁሉ ዛሬ ደግሞ በኢሕአዴግ <አብዮታዊ ዴሞክራሲ> ፀበል ተጠምቀው የካድሬ ተግባር ሲፈፅሙ ማየት ለእምነቱ ተከታዮች አንገት የሚያስደፋ ሆኗል፡፡ የሆነ ሆኖ ይህን በዚህ እናቁምና ወደ አፄ ዮሐንስና ወደ ንጉሥ ምኒልክ እንመለስ፤

አፄ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒልክ ሊቾ ላይ ከታረቁ በኋላ የበለጠ እንዲተማመኑ በማሰብና በደም በሥጋ ለመተሣሠር ሲሉ የ12 ዓመቱን አርአያ ዮሐንስንና 7 ዓመት ከ6 ወራት የሆናትን ህፃን ዘውዲቱ ምኒልክን አጋብተው ሞት እስከለያያቸው ድረስ በጋብቻ በመተሣሰር መተማመንን ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል፡፡ የዚህ ዘመን ባለሥልጣትና ወያኔዎች ግን እንኳንስ በጋብቻ ሊያስተሣሥሩ ይቅርና በጉርብትና እየተጠራሩ ቡና አብሮ መጠጣትም እየቀረ ነው፡፡ በመሰረቱ የሕወሓት ሰዎች ቆም ብለው ማሰብና መፀፀት እስካልቻሉ ድረስ ውጤቱ አሣዛኝ ነው የሚሆነው፡፡ አንዱ የሌላውን ቁስል በስንጥር እንጨት የሚመነቁር ከሆነ ያንድነት ርሿችን ጭራሹኑ መሟጠጡ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ውጤት የሚደሰቱ ካሉ ደግሞ ጊዜው ላይርቅ ይችላል፡፡

## ስህተት አንድ
## በወሎ ሙስሊሞች ላይ የወሰዱት ርምጃ

አፄ ቴዎድሮስ አገራቸውን ወደ አንድ ማዕከላዊ መንግሥት ለማጠቃለል ሲፈልጉ የጦር መሣሪያ እንደሚያስፈልጋቸው አምነዋል፡፡ በመሆኑም የእደ ጥበብ ሙያተኞችን ማሰባሰብና ተገቢውን ክብር መስጠት ነበረባቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ቴዎድሮስ ለሃይማኖት ከማመን ባለፈ የሚጨነቁ ንጉሥ አልነበሩም፡፡ ባንፃሩ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ደግሞ ለእደ ጥበብ ሙያተኞችና ለዘርፉ ግድ አልነበራቸውም፡፡ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ግን ቀናዒ ከመሆናቸው የተነሳ ሃይማኖትን መርሃቸው አደረጉ፡፡ በመሆኑም ለኢትዮጵያ አንድነት አንዱና ዋናው እንቅፋት የሃይማኖት ልዩነት ነው በሚል ወደ ጥፋት የሚያመራና የተሳሳተ መርህ ይዘው ተነሱ፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ በዘመናቸው ከወሰዷቸው ስልት አልባ የተሳሳቱ ርምጃዎች መሀከል አንዱ በወሎ ሙስሊሞች ላይ የወሰዱት ርምጃ ነበር፡፡





አፄ ዮሐንስ ወሎ (ቦሩ ሜዳ ላይ) በ1870 ዓ.ም ንጉሥ ምኒልክና ራስ አዳል (ኋላ ንጉሥ ተክለኃይማኖት) በተገኙበት በተካሄደ ሃይማኖታዊ ጉባዔ ላይ የወሎ ሙስሊሞች ክርስቲያን እንዲሆኑ አዋጅ አወጁ፡፡ ግንባር ቀደም አርአያ ለመሆንም አፄ ዮሐንስ ይማም መሐመድ ዓሊን ክርስትና አንስተው የራስነት ማዕረግ በመሥጠት በክርስትና ስማቸው <ራስ ሚካኤል> ተባሉ፡፡ በኋላ ንጉሥ ሚካኤል የተባሉት የልጅ ኢያሱ አባት ናቸው፡፡ ንጉሥ ምኒልክ ደግሞ የወ/ሮ መስተዋትን ልጅ ይማም ዓመዴ ዓሊን በፈረስ ስማቸው <ይማም አባ ዋጠውን> ክርስትና አንስተው በክርስትና ስማቸው <ደጃዝማች ኃይለማርያም> ተባሉ፡፡

ባዋጁ ውስጥ <ትንባሆ ሲያጨሱ፣ ሱረት ሲምጉ፣ የተገኙ አፍንጫቸው እንዲፎነን (እንዲቆረጥ)፣ የታች ከንፈራቸውና ምላሳቸው እንዲቆረጥ የሚል> በመካተቱ ይኸው ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የፈቀዱ በፈቃዳቸው ወደ አቅራቢያቸው ቤተክርስቲያን እየሄዱ ክርስትና ተነሱ፤ ያልፈቀዱ ደግሞ በጭቃ ሹምና በፈረሰኛ እየተገደዱ ተነሱ፡፡ ክርስቲያን መሆን ሕሊናቸው ያልተቀበለላቸው ደግሞ አገር ጥለው ወደ ሱዳን ተሰደዱ፡፡ የኋላ ኋላ ለድርቡሾች መንገድ መሪ ሆነው በመምጣት የጦርነቱ ቀጥታ ተካፋይ በመሆን በቀላቸውን ሲወጡ እናስተውላለን፡፡ ይህም ይዘገያል እንጂ ሰው የሥራውን-ወይንም የጁን እንደማያጣ በቂ የሆነ ማረጋገጫ ነበር፡፡

ክርስትና ተነሱ ተብለው በተገደዱ ጊዜ አንድ ሙስሊም የሚከተለውን ስንኝ ቋጥሯል፡-

*"ታናሽ ታላቅ በላን አርካ አደባባይ*
*አለልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ?"* ሲል ምሬቱን ገልፆዋል፡፡

ወደ ሱዳን መሰደድ ያልሆነላቸው ሙስሊሞች ደግሞ ወደ ሸዋ እየመጡ ለምኒልክ የጌታ በማደር የምኒልክን ጎራ አጠናከሩት፡፡ በተለይም የወረዒሉ ሙስሊሞች ከመንዝ ጋር ኩታ ገጠሞች በመሆናቸው እምነታቸውን እንደያዙ ወደ መንዝ በመሻገር የምኒልክን ስምና ዝና ከርቀት አገኑት፡፡ ባንፃሩ አጼ ዮሐንስ ቋሚ የሆነውን "አገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው!" የሚለውን መርህ በመፃረራቸው የሕዝብን ፍቅርና አክብሮት በማጣት ኃይላቸው እየሳሳ ሲመጣ እናስተውላለን፡፡

# ስህተት ሁለት
# በቤጌምድር ሕዝብ ላይ የፈፀሙት ነውረኛ ተግባር

ያጼ ዮሐንስ ሁለተኛው ስህተት በቤጌምድር ሕዝብ ዘንድ ዛሬም ድረስ የሚያስወቅሳቸው በፍርደ ገምድልነታቸው ነበር፡፡ የትግራይን ሠራዊት አግተልትለው በማምጣት ከሰኔ እስከ ህዳር ወር መጨረሻ ድረስ ለ6 ወራት ደብረታቦር በመቀመጥ ሠራዊታቸውን በድፍን ቤጌምድር በተሠሪነት በማሠማራት ተዘፍዝፎ ሲያምስ ይከርማል፡፡ በልማዱ አንድ ሕዝብ ሠራዊት በተሠሪነት በየቤቱ እንዲሸከም የሚበየንበት ባንድ ደጃዝማች ወይንም ፊታውራሪ አማካኝነት ወይንም በራሱ አነሳሽነት አልገብርም ብሎ ያመፀ እንደሆነ ነበር፡፡ ይህም ቢሆን መሸነፉን አውቆ ምሕረት ከጠየቀና ከገበረ የተመራበት ተሠሪ ሠራዊት ይነሳለታል እንጂ ለረጅም ጊዜ እንዲሸከም አይበየንበትም፡፡ አፄ ዮሐንስ ግን በተፃራሪው በሰላም ቀጠና ወይንም በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የችጋር ወቅቶች እየተጠበቁ ለረጅም ወራት ሠራዊታቸውን በያመቱ የቤጌምድር ሕዝብ እንዲቀልብ ማድረጋቸው ስህተት ብቻ ሳይሆን ጭካኔም ነበር፡፡

በዚያን ጊዜ የቤጌምድር ሕዝብ ባፄ ዮሐንስ ሠራዊት ከመዋረዱ የተነሣ ዘመነ መሣፍንትን እንደገና የናፈቀበት ጊዜ እንደነበርም በእድሜ አንጋፋዎች ይተርካሉ፡፡ ልክ ዛሬ አንዳንዶች አፋኙ የደርግ ሥርዓት በስንት ጣዕሙ እንደሙሉት ዓይነት ማለት ነው፡፡

መቸም ቢሆን አንበጣና ሠራዊት የሠፈረበት ሕዝብ በሁለንተናዊ መልኩ መቅኖ የለውም፡፡ የቤጌምድር ሕዝብም በዚያን ጊዜ መቅኖ አጣ፡፡ ሥራ ውሎ ሲመጣ ሚስቱን ተገዳ ከወታደር ጋር ተኝታ ያገኛታል፡፡ ይህ ለወንድ ልጅ የከፋ ውርደት ነበር፡፡ አንዳንዶች ሥራ ትተው ሚስቶቻቸውን እየጠበቁ ከቤት መዋል ጀመሩ፡፡ ይህም ለገበሬው የከፋ ስቃይ ነበር፡፡ "ባገርና በሚስት የለም ዋዛ!" ያሉ እየገደሉ ዱር ቤቴ አሉ፡፡ ይህ ደግሞ የከፋ ጥፋትን በሕዝብ ላይ አስከተለ፡፡ አንድ ወይንም ሁለት ግለሰቦች በሚፈፅሙት ጥፋት የንጉሥ ነገሥቱ ሠራዊት ያችን መንደር ያወድማታል፡፡ ወንድ ልጅ የተባለ ሁሉ የፊጥኝ እየታሠረ አርባ ጅራፍ ይገረፋል፡፡ ሕዝቡ ተዋረደ፤ ተናቀ፡፡ ከያቅጣጫው የቁጭት ድምፆች መሠማት ጀመሩ፡፡ በዚህ ምክንያትም እስቴ ወረዳ አቶ ካሣ ገብረየስ በተባሉ ቀንደኛ አዛውንት መሪነት ሰባት ጎልማሶች በሕዝብ ተወክለው ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ለማሰማት ወደ ደብረታቦር ሄዱ፡፡





እነ አቶ ካሣ ገብረየስ ካፄ ዮሐንስ አደባባይ እንደ ደረሱ "አቤት አቤት!" ሲሉ አቤቱታቸውን አቀረቡ፡፡ በዚህ ጊዜ ሊጋባዎች (የንጉሡ አጋፋሪዎች) ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት አቀረቧቸው፡፡ አፄ ዮሐንስም፡- "ምን ሆናችሁ ነው?" ሲሉ ጠየቋቸው፡፡

"ጃንሆይ፤ ሠራዊትዎን ተሠሪነቱን ተቀብለን፣ አክብረን፣ ጥሩ እያበላንና ጥሩ እያጠጣን፣ ምንም ሣናጓድል ሚስቶቻችን ተነጠቅን! ይህንን ይፍረዱን!" ሲሉ አመለከቱ፡፡

ከዚህ በኋላ አደባባይ የተሰበሰበው መኳንንት ይተችበት ጀመር፡፡ ግማሾች "እነዚህ ባላገሮች የሠራዊቱን ስም አጉድፈዋልና መቀጣት አለባቸው" ሲሉ ሌሎች ደግሞ "የለም ሠራዊት በሚሠፍርባቸው አካባቢዎች ሁሉ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ይከሰታሉ፡፡ ይህ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ድሮም ቢሆን በግድ እንጂ ባላገርና ወታደር አይስማሙም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ባላገሮች ቢያጠፉም ሕዝብ የላካቸው ስለሆኑ በወቀሣ ሲለቀቁ ይታየናል" በማለት ሰፊ ክርክር ከተካሄደ በኋላ በመጨረሻ የንጉሠ ነገሥቱ ውሳኔ በጉጉት ይጠበቅ ነበርና የሚከተለውን ወሰኑ፡-

"አካፍሉት እንጂ፤ ምፅሪ ከትግራይ ጭኖ አልመጣ!" ሲሉ አሣዛኝና ነውረኛ ውሳኔ በመወሰን የነ አቶ ካሣን ልብ አደሙት፡፡

ከዚህ በኋላ በድፍን ቤጌምድር ወንድ ልጅ የተባለ ሁሉ ካፄ ዮሐንስ ሠራዊት እየሸሸ የቻለ ሚስቱን እየያዘ ያልቻለ ሚስቱን እየጣለ ተሰደደ፡፡ መኳንንት ቀመሶች ደግሞ ወደ ሸዋ እየሄዱ የምኒልክን የወደ ፊት ተስፋ አለመለሙት፡፡ ለምሳሌ ከታላላቅ መኳንንት መሀከል ራስ ወሌ ብጡል( የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ወንድም) እስከነልጃቸው (ደጃዝማች ጉግሣ ወሌ) በኋላ ራስ ተብለው የቤጌምድር ገዥ የነበሩት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው እንግዲህ ጣይቱና ምኒልክ ከመጋባታቸው በፊት ገና ከማለዳው ነበር፡፡ ምኒልክና ጣይቱ ከተጋቡ በኋላ ደግሞ የቤጌምድርና የየጁ መኳንንት በሙሉ ማለት ይቻላል አገራቸውንና ግዛታቸውን ላፄ ዮሐንስ ሠራዊት እየለቀቁ ወደ ሸዋ በመምጣት ምኒልክን ምኒልክ አሰኟቸው፡፡ ለምሳሌ አከስታችን ብለው ከመጡት መሀከል ወንድማማቾቹ ደጃዝማች አድማሱ ብሩና ደጃዝማች ዓያሌው ብሩ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሌጣቸውን መጥተው ባንድ ጊዜ ለሁለቱም የደጃዝማችነት ማዕረግ ያጎናፀፏቸው ምኒልክ ነበሩ፡፡

ከነዚህ ቀጥሎ ወደ ሸዋ የመጡት ከጉና እስከ በሽሎ ገዥ የነበሩት ያዋርላው ተወላጅ ደጃዝማች ይማም ተፈሪ ነበሩ፡፡ ካፄ ዮሐንስ ጋር

በመቀያየማቸው ምክንያት ግዛታቸውን ለቀው 11 መኳንንትንና 25 ጭፍሮቻቸውን ይዘው ነበር ሸዋ የገቡት:: ካሥራ አንዱ መኳንንት መሀከል አንዱ የኔ ቅድመ አያት ፊታውራሪ ወርቅነህ ይመር ነበሩ:: ያነዬ ግራዝማች ነበር ማዕረጋቸው:: ምኒልክ ነበሩ የፊታውራሪነት ማዕረግ ያለበሷቸው::

እንግዲህ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደ ሞከርኩት ባፄ ዮሐንስ ፍርደ ገምድልነትና ያመራር ስህተት የተነሳ እየተማረረና እያኮረፈ ወደ ሸዋ የሚመጣውን መኳንንት ምኒልክ በክብር እየተቀበሉ ማዕረግ ለሚፈልጉት ማዕረግ ፣ ገንዘብ ለሚሹት ገንዘብ፣ ማደሪያ ለሚሉቱ ማደሪያ እየሰጡ በማስደሰታቸው እንደ እናት ተቆጥረው <እምዬ> የሚል የቁልምጫ ስም የወጣላቸው ያነዬ እንደ ነበር ይነገራል::

ደጃዝማች ይማም ተፈሪና ቅድመ አያቴ ፊታውራሪ ወርቅነህ ይመር የራስ ወልደ ጊዮርጊስ (በኋላ ንጉሥ ተብለው ከራስ ጉግሣ ወሌ በፊት የቤጌምድር ገዥ የነበሩት) ባልደረቦች በመሆን ከግቤ ማዶ የነበሩትን አገሮች ማለትም ከፋን፣ ጅማን፣ ሊሙን. . . ወደ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲጠቃለሉ አድርገዋል:: የቅድመ አያቴ መቀመጫም ባቦ ኮሣ ማርያም ከተባለች አምባ ነበር:: ኮሣ ማርያምን የተከሏት እሳቸው ነበሩ:: ወግ ማዕረግ አይተው፣ ኑረው፣ ሙተው የተቀበሩትም ካስተከሏት ቤተ ክርስቲያን ኮሣ ማርያም ነበር::

አያቴ (ያባቴ እናት) ወ/ሮ አለሙሽ ወርቅነህ ተወልደው አፋቸውን የፈቱት በኦሮሞኛ ቋንቋ ሲሆን ካባታቸው እልፈት በኋላ ወደ አባታቸው አገር ጎንደር (ጋይንት) የሄዱት የ11 ዓመት ልጅ ሳሉ ነበር:: እኔ እንግዲህ እንደዚህ ነኝ:: እናንተስ? ስንቶቻችሁ ትሆኑ እንደ አሜባ አንድ ሴልና ባንድ የጎሣ ደም የነጠራችሁት? ጠይቁ::

እንግዲህ አፄ ዮሐንስ ያነዬ በወሎና በቤጌምድር ሕዝብ ላይ በፈፀሙት ስህተት መኗሪያ ሲያሳጡት እሳቸውን እየሸሸ ለምኒልክ የጌታ በማደሩ እሳቸው ባንድ ጎሳ (በትግራይ መኳንንትና ሠራዊት) ብቻ ተከበው ርቃናቸውን ቀሩ:: ወደፊት እንደምናየው በጎጃም ሕዝብ ላይ የወሰዱት ያልተገባ ርምጃም ርቃናቸውን ቀርተው አወዳደቃቸው ሲከፋ እናስተውላለን::





## ስህተት ሦስት
## ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ያደረጉት ስምምነት

አፄ ዮሐንስ በስህተት ሦስት የፈፀሙት ስህተት ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ያደረጉት ስምምነት ሲሆን ያልተገባና በየዋህነት የተከናወነ ነበር:: በወቅቱ ለጎንደር አድባራትና ገዳማት መቃጠልና መዘረፍ ምክንያት ሲሆን ውሎ አድሮ ደግሞ ለሰሜን ኢትዮጵያ ቀጣይነት ላለው ችግር የመሠረት ድንጋይን ያስቀመጠ ውል ነበር:: የሰዐጢ፣ የዶጋሊ፣ በመጨረሻም ሕይወታቸውን ያጡበት የመተማ ጦርነት፣ እንዲሁም ከዚያ ወዲህ ያድዋና የማይጨው ጦርነቶችና የኤርትራ መገንጠልን ጨምሮ እስከ ሕወሓት መፈጠር ድረስ ያሉት ችግሮች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የስምምነቱ ውጤቶች መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባናል:: ዛሬ እየተጎነጨነው ያለነው መራራ ጽዋ አፄ ዮሐንስ ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር በፈፀሙት የቅርቃር ስምምነት ምክንያት መሆኑን ታሪክ እየገለበጡ የሚያነቡልን አፄ ዮሐንስ የተጓዙበትን መንገድና የፈፀሟቸውን ስህተቶች መለስ ብለው በጥንቃቄ ሊያጤኗቸው ግድ ይላቸዋል:: በዚህ አጋጣሚም ያነዬ አፄ ዮሐንስ የቅኝ ገዥ ወታደሮችን ከቅኝ ተገዥዎች ጋር ተፋልመውና ከንቱ የሆነ የሕይወት ዋጋ ከፍለው ነፃ እንዳወጧቸው ሁሉ የሕወሓት ባለሥልጣናትም በዚህ ዘመን ሞቃዲሾ ድረስ ሠራዊት ልከው ያሜሪካኖችን ደም ሲበቀሉ ለትውልድ ደግሞ የደም እዳ ማስቀመጣቸውንም አብረው ሊያዩትና ሊጤኑት ይገባቸዋል::

በመሠረቱ የንጉሠ ነገሥቱ የዋህነት የጧት ወዳጅ የማታ ጠላት እንደሚሆን አለመገንዘባቸው ነበር:: በሳቸው እምነት እንግሊዞች ያፄ ቴዎድሮስ ጠላት ስለሆኑ ለሳቸው የዘለቄታ ወዳጅ የሚሆኗቸው መስሏቸው ከሚገባው በላይ እንደተለማመጧቸው ማረጋገጫው ከስምምነቱ በኋላ ለንግሥት ቪክቶሪያ የፃፉት ደብዳቤ በቂ ማሣያ ነው:: እንዲህ ይነበባል:-

*“. . .ጥንቱንም በእግዚአብሄር ፈቃድ ለመንግሥት የበቃሁት እሰዎ በሠጡኝ ነፍጥ (ጠመንጃ) ባሩድ ነው (ጥይት) ነው:: አሁን ደግሞ ይልቁንም ፈጽሞ ደስ አሰኙኝ:: ከዚህ በፊትም እናት ለልጇ እንደ ምትጨነቅ ለኔ መንግሥት ሲጨነቁ ኖረዋል!” (ተክለ ፃድቅ መኩሪያ አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት ገጽ 270)*

ወደ ስምምነቱ በቀጥታ ከመግባታችን በፊት ለግንዛቤ ያህል በትንሹም ቢሆን ወደ ኋላ መለስ ብለን ለወታደሮቹ መከበብ ምክንያት የሆነውን ማየቱ ጠቃሚ ነው።

በ1820 ዓ.ም በግብፅ የቱርክ እንደራሴ የነበረው አልባኒያዊው መሐመድ ዓሊ (ቅጥረኛ ነው) የላይኛውን ያባይ ሸለቆ ተፋሰስ ተከትለው ያሉትን አገሮች ጥንት ኑቢያ፣ ሜሮዌና ስናር ይባሉ የነበሩትን በጦር ኃይል ድል አድርጎ ባንድ ላይ አጠቃሎ <ሱዳን> የሚል አዲስ ስም በመስጠት በግብፅ ቅኝ ግዛት ሥር እንዲወድቁ አደረጋቸው። <ሱዳን> ማለትም በዐረበኛ <ጥቁር ዐረብ> እንደማለት ነው። እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሔዊት ስምምነት እስከ ተፈረመበት ድረስ ሱዳናውያን በግብፅ ቁጥጥር ሥር ነበሩ ማለት ነው።

ኋላ ላይ ደግሞ ቅኝ ግዛት በተፋፋመበት ወቅት ግብፅ ራሷ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ስትወድቅ እንግሊዝ ቀደም ሲል ምፅዋን ጨምሮ በግብፅ ይዞታዎች ሥር የነበሩትን አገሮች በሙሉ በቁጥጥሯ ሥር ማድረግ ፈለገች። በመሆኑም ቀደም ሲል ሱዳን ውስጥ ሠፍረው ከነበሩት የግብፅ ወታደሮች በተጨማሪ የራሷን ወታደሮች በመላክ ኃይሏን በማጠናከር የቅኝ ግዛት መሠረቷን ጣለች። ይህ የቅብብሎሽ አገዛዝ ደግሞ ሱዳናውያንን አንገሸገሻቸው። እናም ለነፃነታቸው ሲሉ አመፁ።

በመሪያቸው ስም (በመሐዲ) መሐዲስቶች ወይንም ድርቡሾች በመባል የሚታወቁት አማፂያን ከፍተኛ የሥንቅና የጦር መሣሪያ ክምችት ያሉባቸውን የጦር ካምቦች ከሰሳንና ገላባትን በመከበብ አስጨናቁ። ያማፂያኑ ከበባ እጅግ የተጠናከረ ስለነበር ሠብሮ ለመውጣትም ሆነ ከጀርባ ገብቶ ለማስለቀቅ የሚቻል አልነበረም። ስለዚህ የነበረው አማራጭ እንግሊዝ የሕይወትም ሆነ የቁስ ኪሣራ ሣይገጥማት በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኪሣራ የተከበቡትን ወታደሮቿን ማስለቀቅ እንደምትችል አረጋገጠች። ለዚህ ደግሞ አፄ ዮሐንስ እንደማያንገራግሩ ርግጠኞች ነበሩ። የሆነውም ይኸው ነበር።

በዚህ መሠረት በግብፅ በኩል ሜሶን ቤይ የተባለ፣ በእንግሊዝ በኩል ደግሞ የተደራዳሪዎች የቡድን መሪ የእግሊዝ የባሕር ኃይል ም/አዛዥ ሪር አድሚራል ሔዊት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ግንቦት 18 ቀን 1876 ዓ.ም የመጀመሪያውን የቃል ስምምነት ከፈፀሙ በኋላ በታሪክ "የሔዊት ስምምነት" ተብሎ የሚታወቀውን የሠነድ ፊርማ ሰኔ 3 ቀን 1876 ዓ.ም





ተፈራረሙ። ይህ ስምምነት አድዋ ላይ በመከናወኑ <"ያድዋ ስምምነት> በመባልም ይታወቃል።

ከዚህ ላይ ታዲያ መነሣት ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ ኢትዮጵያ የሕይወት መሥዋእትነት ከፍላ፣ ከጎረቤት አገር ጋርም የዘለዓለም ቁርሾ ገብታ በመልሱ ምን አገኘች? ንጉሠ ነገሥቱስ ምን ምን ጥያቄዎችን አቅርበው ነበር? የሚሉትን ስናነሳ የምናገኘው መልስ የሚያስገርም ነው። ሌላውን ዝርዝር ሁሉ ትተን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲፈፀሙላቸው ካቀረቧቸው መሀከል ሁለቱን ብቻ ጠቅሰን እንመልከታቸው:-

*1. "የከሰላ ግዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲጠቃለል"*
*2. "ከምፅዋ ወደብ ከሚሰበሰበው ቀረጥ ከግብፅ ጋር እኩል የመካፈል መብት ይኑረኝ"* የሚል ነበር።

የንጉሠ ነገሥቱን ተለማማጭነት ልብ እንበል። ዋናውን የወደብ የይገባኛል የሙብት ጥያቄ ጭራሹኑ ትተው ከወደብ የሚገኘውን ቀረጥ ከግብፅ ጋር እኩል ልካፈል ብለው የመጠየቃቸው ጉዳይ ያናድዳል። ሌላው ቀርቶ ግብፅ እንደ የመን እንኳን ቀይ ባሕርን ማዶና ማዶ አታዋስነንም። በተስፋፊነት የኛ አቅም በወነሰበት ወቅት ቱርክን ተከታ የተቀመጠች ናት። አፄ ዮሐንስ ይህን እያወቁ በዚያች አስጨናቂ አጋጣሚ ተጠቅመው <ግብፅ ወደቤን ልትለቅልኝ ይገባታል> ብለው መሟገት ሲገባቸው የእለት ፍርፋሪ ለቀማ ከወደብ ከሚገኝ የቀረጥ ገቢ እኩል ልካፈል ብለው የመጠየቃቸው ጉዳይ በጣም ያስገርማል።

እንግሊዞቹና ግብፆቹ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተው መውጫ ቀዳዳ በሚፈልጉበት ወቅት <ወደቤን ልትመልሱልኝ ይገባችኋል!> በማለት አምርረው ቢሟገቱ ኖሮ የምፅዋን ወደብ ማግኘት ይችሉ እንደነበር መገመት ይቻላል። አሻፈረን ቢሉ እንኳን በወቅቱ የግብፅና የእንግሊዝ ወታደሮች በሱዳን ዓማፂያን ተከበው ስለነበር ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመውበት ቢሆን ኖሮ ያለጥርጥር የምፅዋን ወደብም ሆነ ሌሎቹን በግብፅ ቁጥጥር ሥር የነበሩትን ሁሉ አስለቅቀው መያዝ ይችሉ እንደነበር በጊዜው ሩቤንሰን (Rubenson) የተባለው ጸሐፊ ተችቶ የጻፈውን ዶ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ ዋቢ ጠቅሰው የጻፉትን ቀጥለን እንመልከት:-

*". . .የሱዳን መሐዲስቶች ወይንም ድርቡሾች በግብፅና በእንግሊዝ ወታደሮች ላይ በብሔራዊ የነፃነት አመፅ በተነሱበት ጊዜ በኢትዮጵያ ሰሜንና ምእራብ ጠረፎች በግብፅ ወታደሮች የተያዙ ሠፍራዎችን በቀጥታ ሄደው*

*በመውሰድ ፈንታ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ በ1876 ዓ.ም ‹በዓድዋ ውል› አፄ ዮሐንስ ለብሔራዊ ነፃነታቸው በሚዋጉ እስላማውያን ላይ ለሁለቱም ማለትም ለሱዳንና ለኢትዮጵያ የጋራ ጠላቶች ከሆኑ ከግብጽና ከእንግሊዝ መንግሥታት ጋር ተባበሩ . . !" (የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ገጽ 269)*

ከስምምነቱ በፊትም ቢሆን ንጉሠ ነገሥቱ ምን ያህል ቸልተኝነት ያጠቃቸው እንደነበር ሩቤንሰን የተቸበትን ጠቅሰው ዶ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ በተመሳሳይ ገጽ ያሰፈሩት እንዲህ ይነበባል:-

*". . .በጉንደትና በጉራዕ ጦርነት አፄ ዮሐኝስና ራስ አሉላ ወራሪውን የግብፅ ጦር በታላቅ አርበኝነትና ወኔ ተዋግተዋል:: የጠላትን ጦር ከደመሰሱ በኋላ ግን በጠላት እጅ የነበረውን መሬት በቀላሉ መውሰድ ሲችሉና ሲገባቸው ለመውሰድ አልሞከሩም ወይንም አላሰቡም:: በተጨማሪም በሸንፈት ከጦር ሜዳ ለሸሸው ለግብፁ የጦር አዛዥ አፄ ዮሐንስ በራሳቸው አነሳሽነት ለሰላም ድርድር ያቀረቡትን አሳብ በጽሑፍ አስቀምጠው ከጦር ሜዳ ከተማረኩ እስረኞች ጋር ላኩለት:: አዛዡም እስረኞቹን (ምርኮኞቹን) በነፃ ካገኛቸው በኋላ አፄ ዮሐንስ ለሰላም ያቀረቡትን አሳብ በመቀበል ፈንታ ‹ከጦር ሜዳ የተማረከውን የጦር መሣሪያ ጭምር በቅድሚያ ላኩልኝ› በማለት አፌዘባቸው. . ."* እውነትም ሊፌዝባቸው የሚገቡ ንጉሥ ነበሩ:: ምርኮኞቻቸውን ይዘው መደራደር ሲገባቸው ደብዳቤ አሲዘው በመልቀቅ ምን ይዘው ነው የሚደራደሩት? ጠይቁ::

ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያ ቃሏን አከብራ፣ በታሪክ "የኩፊት ጦርነት" በመባል የሚታወቀውን በራስ አሉላ የጦር መሪነት አዝምታ፣ ከባቢዎቹን (ድርቡሾቹን) ደምስሳ የተከበቡትን ነፃ አውጥታ በስምምነቱ መሠረት በምፅዋ በኩል አስወጥታ ወደየ አገራቸው እንዲሄዱ ስታደርግ በመልሱ ግን እንግሊዝ ጣሊያንን አምጥታ ምፅዋ ወደብ ላይ በማሥፈር ለኢትዮጵያ ጠላት ተከለችላት::

## ስህተት አራት
## ራስ አሉላን ማጋዛቸው

እንደሚታወቀው የራስ አሉላ አባ ነጋ ቋሚ መፈክርና መርህ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው!" የሚል ነበር:: በመሆኑም ራስ አሉላ እንደ እሳት አለሎ እየተወረወሩ ቀደም ሲል ግብፆችን ድባቅ እየመቱ





እንደመለሷቸው ሁሉ በኋላም የንእግሊዝን የጡት ልጅ ኢጣሊያንን ሰዐጢ ላይ ድባቅ በመምታት አሣፍረው ቢመልሷትም የሩቅ ጊዜ ግቧ ኢትዮጵያን ጠቅላል መያዝ በመሆኑ አመች ጊዜና ወቅት እየጠበቀች መተንኮሷን አላቆመችም ነበር:: በመሆኑም በጥር ወር 1879 ዓ.ም (ምፅዋ በሰፈረች በሁለተኛው ዓመት) ከምፅዋ በመንቀሳቀስ ዶጋሊ ላይ ጦርነት ከፈተች:: በዚህ ወቅት አፄ ዮሐንስ መሀል አገር ነበሩ:: እንዳሁኑ ስልክም ሆነ ሬዲዮ ባለመኖሩ የእዝ ሠንሠለትን ለመጠበቅ የሚቻል አልነበረም:: በመሆኑም ራስ አሉላ ባላቸው ኃይል ከመመከት ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም:: ስለዚህ አፍጥጦ የመጣውን የጠላት ጦር ድባቅ በመምታት ካድዋ ድል ቀደምት የሆነውን የዶጋሊን ድል በታሪክ አስመዘገቡ:: ዳሩ ግን ይህ አኩሪ ድል ሊያሸልማቸው ሲገባ ተወቅሰውና ተነቅፈው ከሥልጣናቸውና ከግዛታቸው ለመሻርና ለመጋዝ ምክንያት ሆነ::

ጣሊያኖች የንጉሠ ነገሥቱን ደካማ ጎን ስለሚያውቁ "ራስ አሉላ ምንም ሣንነካው ወረረን" በማለት ገልብጠው በመጮሀቸው አፄ ዮሐንስ ከመሀል አገር ገሥግሠው ባሕረ ነጋሽ በመግባት "እኔ ሣላዝህ ጣሊያኖችን ወግተሃል!" በሚል አግዘው ለቦታው የማይመጥኑ የወንድማቸውን ልጅ ራስ ኃይለማርያምን የባሕረ-ነጋሽ እንደራሴ አድርገው በመሾም ጣሊያኖችን አስፈነደቋቸው:: በዚህ ወቅት ደግሞ ድርቡሾች የንጉሠ ነገሥቱን እግር ጠብቀው ጎንደር ከተማ ድረስ በመዝለቅ ከ44ቱ አድባራት መሀከል 40ዎቹን ኢቃጥለው መጠነ ሠፊ ዘረፋም አካሄዱ:: በድርቡሾቹ ወረራ የተበሳጨ አንድ የጎንደር ደብተራ "አላህ እነሱን ቢወዳቸው ነው ለድል ያበቃቸው!" ብሎ ማተቡን በጥሶ በመጣል በፈቃዱ ሰልሞ ከድርቡሾቹ ጋር ተቀላቅሎ መሄዱ ይነገራል::

አፄ ዮሐንስ የጎንደርን መቃጠል ሰዐጢ ላይ ከጣሊያኖች ጋር ተፋጠው እንዳሉ በሰሙ ጊዜ ንጉሥ ተከለሃይማኖትን ወርደው ድርቡሾችን እንዲበቀሏቸው አዘዟቸው::

ንጉሠ ተከለሃይማኖት የንጉሠ ነገሥቱን ትእዛዝ ተቀብለው እንዴት እንደዘመቱ ሂደቱን አለቃ ተከለ ሥላሴ ዋቅጅራ የተባሉ ሊቅ በጊዜው አብረው የነበሩ የጻፉትን ተከለ ጻድቅ መኩሪያ ዋቢ ጠቅሰው ያሠፈሩት:-

*"የጎጃም ሰው ያንጊዜ ወደ ጦርነቱ ሲሄድ አለቅጥ ጠግቦ እንደ እንቦሳ እየዘለለ የትምክህት ቃል ይናገር ነበር. . ."* ይሉና ቀከራውን እንዲህ በማለት አስቀምጠውታል:-

*"አይታሰስም ምጣድ በግምጃ*

ዘንድሮ ድርቡሽ መትረፉን እንጃ!" እያለ ነበር ወደ ፍልሚያው የሄደው (ተክለፃድቅ መኩሪያ ገጽ 449)

ፍልሚያው የተካሄደው ጥር 10 ቀን 1880 ዓ.ም ሲሆን ቦታው ደንቢያ ሣር ውሃ ላይ ነበር:: የንጉሥ ተክለሃይማኖት ጦር ሊቁ እንደ ጠቀሱት በንቀት እየፎከረና እየተሳደበ ወርዶ ቢገጥምም ባንድ ዙር ፍልሚያ ብትንትኑ ወጥቶ በያቅጣጫው ሸሸት ሆነ:: ንጉሥ ተክለሃይማኖትና አቡነ ሉቃስም ቀድመው ሸሹ:: ይህነኑ የጦርነቱን ፍፃሜ አለቃ ተክለሥላሴ ዋቅጅራ እንዲህ አስቀምጠውታል:-

*". . .የንጉሥ ተክለሃይማኖት ወንድ ልጅ በለው ተክለሃይማኖት ዳሰው በተባለው ፈረሳቸው ምርኮ በምርኮ ሆነው ከግንባር ሲመለሱ አባታቸውና ጳጳሱ ሸሽተው ሰላገኟቸው ተናደው ‹ሕኔን እንመለስ ሳይሉ ለሞት ዳርገውኝ ራስ በዛብህን ይዘው ጥለውኝ ሄዱ› በማለት ብዙ ቀን ተኳረፉ"*

በዚሁ በሣር ውሃው ፍልሚያ የሴት ልጃቸው ባል ደጃዝማች ጀንበሬ ጥሩ ሙያ ሠርተው ሲሰው ሚስታቸው ምንትዋብ ተክለሃይማኖት ከባላቸው ጋር ነበሩና ተማርከው መወሰዳቸውንና በእስላም እጅ አልበላም ብለው በርሃብ ተሠቃይተው እንደሞቱ ሊቁ ተርከዋል:: በተማረኩ ጊዜም የሚከተለውን ስንኝ መቋጠራቸውን አለቃ ተክለሥላሴ ጽፈዋል::

*"ጎጃም የምትሄዱ እንደኔ ማትቀሩ*
*ርኩስ በልታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ!"*

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ድል መሆናቸውን በሰሙ ጊዜ ቀደም ሲል ፎክረው መውረዳቸውን ሰምተው ነበርና "ፎክረህ ወርደህ ተሸንፈህ፣ ሰውን አስፈጅተህ ተመለስህ!" ብለው ከወቀሷቸው በኋላ ንጉሥ ምኒልክን "ለኔ ብለህ ሣይሆን ለሃይማኖትህና ለማተብህ ስትል ሂድና ከድርቡሾች ጋር ተዋጋ!" በማለት እንዳዘዟቸው ተክለፃድቅ መኩሪያ አለቃ ተክለሥላሴን ዋቢ ጠቅሰው በገጽ 452 አስፍረዋል::

በዚህ አጋጣሚ ለዚህ ዘመን ወጣት ልጃገረዶች ወይንም ቆንጆዎች አራት ሞገደኛ ሞግሽ ምንትዋቦችን አስተዋውቆ ማለፉ ጠቃሚ ይመስለኛል::

የመጀመሪያዋ ምንትዋብ ቋረኛዋ ያፄ በካፋ ባለቤት እቴጌ ምንትዋብ ሲሆኑ በፖለቲካው መስክ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጣሪ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል::





ሁለተኛዋ ምንትዋብ ያፄ ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዓሊ (የልጅነት ስማቸው ምንትዋብ ነበር) ለባላቸው ኮከብ አማካሪ እንደነበሩ ይተረከላቸዋል::

ሦስተኛዋ ሞገደኛ ምንትዋብ አፄ ቴዎድሮስ አባቷን፣ ባሏንና ወንድሟን የገደሉባት ስትሆን:-

*"ሺ ፈረስ ከኋላው ሸፈረሽ ከፊቱ*
*ይህን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ . . .!"*

ብላ በድፍረት ስንኝ በመቋጠር እልኳን የተወጣችው ናት::

አራተኛዋ ሞገደኛ ምንትዋብ ካባታቸውና ከባላቸው ጋር ደንቢያ ሣር ውሃ ዘምተው ቢማረኩም ሃይማኖታቸውን ለመቀየር ቀርቶ "በእስላም እጅ አልበላም!" ብለው በርሃብ ተሰቃይተው መሞታቸው ፅናታቸውን የሚያሣይ ነው::

ንጉሥ ምኒልክ ያፄ ዮሐንስን ትእዛዝ ተቀብለው የሸዋንና የወሎን ጦር አስከትለው በሚያዝያ ወር ደብረታቦር በመግባት ሠፈሩ:: የቤጌምድር ጦር ተጠቃሎ እስከሚገባላቸው ድረስም 19 ቀናት ያህል ከተቀመጡ በኋላ በመጨረሻ ጎንደር በመግባት አዘዞ ላይ ሠፈሩ::

ንጉሥ ምኒልክ አዘዞ ሠፍረው በቆዩባቸው ቀናት ውስጥ ሁለት ጊዜ ወታደራዊ ሠልፍ አድርገዋል:: የጦሩ ብዛትም ሆነ የታጠቀው መሣሪያ ከበቂ በላይ በመሆኑ ሣር ውሃ ላይ መሽጎ የነበረው የድርቡሽ ሠራዊት ገና ሣይዋጋ መቋቋም እንደማይችል አውቆ መተማ ወርዶ መመሸጉን ታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል::

ንጉሥ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥቱ ባዘዟቸው መሠረት ወርደው መግጠም ሲችሉ በራስ አሉላ አባነጋ የደረሰው የመጋዝ እጣ በኔም ላይ ሊደርስ ይችላል በሚል ሥጋት ይመሥላል የንጉሠ ነገሥቱን የመጨረሻ ትእዛዝ ለመቀበል መልእክተኞችን ላኩ::

መልእክተኞች በቅንነት ንጉሠ ነገሥቱን ደስ ያሰኙ መስሏቸው "ምኒልክ ይዘውት የተሠለፉ የሠራዊት ብዛትና የታጠቀው የጦር መሣሪያ ጥራት እንኳንስ የድርቡሽ ጦር የእንግሊዞችም ጦር አይመከተው" እያሉ በማጋነን ሲተርኩላቸው በዙሪያቸው የከበቧቸው መኳንንትም ቀድሞውንም ቢሆን ለምኒልክ ቀናነት አልነበራቸውምና ተጨማሪና የመጨረሻ ውድቀታቸውን

የሚያፋጥን ሥህተት እንዲሠሩ ገፋፏቸው:: "እንዲህ ከሆነማ ድርቡሾችን ድል አድርጎ በማረከው የጦር መሣሪያ መልሶ ሊወጋን አይደል" በሚል ሥጋት "በመጣህበት አድርገህ አገርህን ሸዋ ግባ" የሚል መልእክት አስተላለፉላቸው::

ንጉሥ ምኒልክ ባፄ ዮሐንስ ያልተጠበቀ መልስ በጣም ተገርመው በመጡበት ሳይሆን ወደ ጎጃም በመሻገር ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር በመገናኘት አፄ ዮሐንስ ከሁለት አንዳቸውን ወይንም ሁለቱንም ሊወጓቸው ከመጡ ካንድ ላይ ሆነው ሊወጓቸው ተማምለው መለያየታቸው እውነት ነው:: እንዲያውም ንጉሥ ምኒልክ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ሣር ውሃ ላይ በተማረኩባቸው የጦር መሣሪያ ምትክ ወይንም ከዚያም በላይ ሁለት ዘመናዊ መድፎችና 250 ሲናድር ጠመንጃዎችን ከበቂ ጥይቶች ጋር ሠጥተዋቸው መሄዳቸውን አለቃ ተክለሥላሴ ዋቅጅራ ጽፈዋል::

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት ጋር በመገናኘት ዶልተውባቸው ሸዋ መግባታቸውን ባወቁ ጊዜ ባሕረ ነጋሽን አዲስ ለሾሟቸው ለራስ ኃይለማርያም ትተው፣ ራስ አሉላን ካጋዙበት አስመጥተው እሳቸውን በመያዝ ገሥግሠው መቀሌ ገቡ::

ሌላው አሣዛኝ ነገር ንጉሠ ነገሥቱ መቀሌ ከመድረሳቸው ቀደም ብለው ታመው ነበርና ልጃቸው ራስ አርአያ ዮሐንስ (የዘውዲቱ ምኒልክ ባል) በሞት በመለየታቸው ሐዘናቸው መሪር እንደነበር ይነገራል:: በርግጥም በዚያች የወከባ ወቅት የልጃቸው በሞት መለየት ከባድ ፈተና እንደሚሆንባቸው ምንም ጥርጥር የለውም::

ንጉሥ ነገሥቱ ምንም እንኳን ከባድ ሐዘን ቢወድቅባቸውም ያገር ጉዳይ ደግሞ ከምንም በላይ ነውና ሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ዘውዲቱ ምኒልክን ጭምር ይዘው ቁጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ሠራዊት መርተው ደብረታቦር ገቡ::

## ስህተት አምስት

## በጎጃም ሕዝብ ላይ የወሰዱት ያልተገባ ርምጃ!

አፄ ዮሐንስ ሐምሌ እንደገባ ከደብረታቦር ተነስተው 15 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘው አሞራ ገደል ሲደርሱ ሠፈራ በማድረግ መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ጉባዔ ተቀመጡ:: የጉባዔው ዓላማ "በቅድሚያ ድርቡሽን እንምታ ወይንስ ወደ ጎጃም ዘምተን ንጉሥ ተክለሃይማኖትን፣ ከዚያ ደግሞ ወደ ሸዋ





ተሻግረን ምኒልክን ማንበርከክ" የሚል ነበር:: በመሆኑም ወደ ጎጃም እንዝመት የሚለው ሀሳብ በማመዘኑ ወደ ጎጃም ተሻገሩ::

አፄ ዮሐንስ ወደ ጎጃም ይዘውት የዘመቱት የሠራዊት ብዛት፣ እንደ ሀምሌ ጎርፍ የሚያጥለቀልቅ በመሆኑ ሕዝቡ ገርሞት:-

*"እንካሣው በምርኩዝ እውሩ በመሪ የተከተለዎ*
*እህል አይበቅልም ወይ ንጉሥ ባገርዎ"* ብሏቸዋል::

ንጉሥ ተክለሃይማኖት እንደ ተባለው አፄዮሐንስ የትግራይን ሠራዊት አግበስብሰው እንደሚመጡባቸው ያውቁ ነበርና ለረጅም ጊዜ የሚያቆይ ሥንቃቸውን፣ ምርጥ ታማኝ ሠራዊታቸውን ይዘው ሙተራ ተራራ በመውጣት ምሽግ ይዘው ጠበቋቸው::

አፄ ዮሐንስ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት የመሸጉበትን ተራራ ከበው ብዙ ቀናት በመድፍ እየደበደቡ ቢያስጨንቁም ፍንክች የሚሉ አልሆኑም:: በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ አንባው ለመውጣት የሞከሩትን ወታደሮች በናዳ እንደቲማቲም እየጨፈለቁ ፈጇቸው:: የመድፉ ጥይትም እያፏጨ ወደ ዓባይ በረሃ እየሄደ ከሚያርፍ በስተቀር አንዳች ጉዳት ሊያደርስ አልቻለም:: ካምባው ወገብ ላይ የሚያርፈውም (ጊዜው ክረምት በመሆኑ) ከጭቃው ርሳሱ እየተረፎቀ ደፍ የሚል ድምፅ ከሚያሰማ በስተቀር ጥቀርሻ የመሰለ አቧራ እያስነሳና የተደበላለቀ መብረቃዊ ድምፅ እያሰማ የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ጦር ማሸበር አልቻለም:: በዚህ የተበሳጩት ንጉሠ ነገሥት ሠራዊታቸውን በድፍን ጎጃም በማሠማራት ሰላማዊውን ሕዝብ አስመደመዱት:: ጦራቸው እጅግ በሚያሳፍርና በሚያሳዝን መልኩ ድርቡሽ በጎንደር ሕዝብ ላይ ከፈፀመው ጥፋት የከፋ ጥፋት በጎጃም ሕዝብ ላይ ፈፀመ::

ገበሬዎቹ በሬ ጠምደው ከሚያርሱበት ዘሩ እንደ ተዘራ በሬዎቹ ተፈተው ታርደው ሞፈሩና ቀንበሩ እየተፈለጠ ለሥጋ መጥበሻነት ዋለ:: የጥገት ላሞች ሳይቀሩ እየታረዱ እንቦሶቻቸው ሲያላዝኑ መስማት አንጀትን የሚያላውስ ሆነ:: ሕዝቡ በክርስቲያን ወግ እየሸሸ በያቅራቢያው ካለ ደብር የሙጥኝ ቢልም ያፄው ወታደሮች እያሣደዱ ጨፈጨፉት:: የቤተክርስቲያን በሮች፣ መቃዎች እየተፈለጡ የሥጋ መጥበሻ ሆኑ:: ፅላቶች እንዳልባሌ እቃ የትም ተጣሉ:: ልብሷን የተገፈፈችና ከብቶቿ የታረዱባት አንዲት ሴት:-

*"በላይኛው ጌታ በባልንጀራዎ*
*በቅዱስ ሚካኤል በጋሻ ጃግሬዎ*

*በጽላተ ሙሴ በነጭ አምብዛዎ*
*ጎጃምን ይማሩት ፈሪም አንለዎ!"* ብላቸዋለች። *(ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ገጽ 504-5)*

ይህነኑ ያፄ ዮሐንስን ወረራ አለቃ ተክለሥላሴ ዋቅጅራ ያይን እማኝነታቸውን ሲገልፁ፡-

*". . .አፄ ዮሐንስ ጎዛምን ላይ ሠፍሮ አምባውን ሊሠብር በጭምትና በነማይ አፋፍ መድፉን ጠመደ። ግን አልሆነለትም። ኃይለኛው መድፍ ጅብላን እያለፈ ዓባይ በረሃ ወደቀ። ቀላሉ መድፍ ደግሞ ያምባውን ገደል (ወገብ) እየመታ ቀረ። ያን ጊዜ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ወታደር (ተኳሽ) የመድፉን አረር (ጥይት) በመድፉ አፍ አስገብቶ ተረተረው! . . . ከዚህ በኋላ ያፄ ዮሐንስ ወታደር በጎዛምንና በማቻከል የተገኘውን የቤተክርስቲያን ሣንቃ እየነቀለ፣ ማገሩን እየፈለጠ አነደደው! ታቦቱንም ከመንበሩ እያወጣ በየሜዳው በጣለው ጊዜ ጳጳሱ አቡነ ሉቃስ ‹ድርቡሽን አጠፋለሁ ብለህ መጣሁ ያልከው ለጎጃም ሕዝብ አንተ ድርቡሽ ሆንክበት› አሏቸው"* በማለት የጻፉትን ተክለፃድቅ መኩሪያ በገጽ 503 አስፍረውታል። እውነትም የወረራውን አስከፊነት ሕዝቡ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

*"ጎጃም ተቃጠለ ዓባይ እስከ ዓባይ*
*ትግሬ ቅጠል ይዞ ሊያጠፋው ነወይ"*

ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ቁምነገር አለቃ ተክለሥላሴም ሆኑ አቡነ ሉቃስ ከተለመደውና ከባህላችን ባፈነገጠ መልኩ አፄ ዮሐንስን "አንተ" እያሉ ነበር የገለፆዋቸው። ምናልባትም አፄው የፈፀሙት ተግባር ከተራ የመንደር ሽፍታ ያነሰ በመሆኑ ላንድ ንጉሠ ነገሥት ሊሰጥ የሚገባውን ክብር ነፍገዋቸዋል ማለት ነው።

ንጉሠ ነገሥቱ የጎጃምን ሕዝብ በሀምሌው ምድር የቁም ሲቃይ በሚያሣዩበት ወቅት ጣሊያኖች በበኩላቸው የሳቸውን መራቅ አጋጣሚውን በመጠቀም ከምፅዋ ገሥግሠው አሥመራ በመግባት ከመረብ ምላሽ ያለውን አገር "ኤርትራ" ብለው በመሰየም አዲስ ቅኝ ግዛት ፈጠሩ።

ቀደም ሲል እሳቸው ሰዐጢ በነበሩበት ወቅት ያጎታቸው የራስ አርአያ ልጅ ደጃዝማች ደበበ አርአያ እሳቸውን ከድቶ ምፅዋ በመሄድ ለጣሊያኖች የጌታ አደሮ ነበርና ልክ እሳቸው የናፒየርን ጦር ከዘይላ ወደብ እየመሩ መቅደላ እንዳደረሱት ሁሉ ደጃዝማች ደበበ አርአያም ጣሊያኖችን ከምፅዋ ወደብ መንገድ እየመራ በማምጣት እንደራሴቸውን ራስ ኃይለማርያምን





በቀላሉ ገሎ ባሕረ-ነጋሽን በጠላት እጅ እንድትወድቅ አደረገ። የቀ.ኃ.ሥላሴ አማች ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣም ያደረገው እንዲሁ ነበር።

እንዲህ ሀቁ ይኸ ሆኖ እያለ ነው የሻዕቢያና የሕወሓት ሰዎች "ምኒልክን ኤርትራን ፈርሞ ለቋል" እያሉ አፅማቸውን የሚፈጩት። አፄ ዮሐንስ ግድግዳውን ራስ አሉላ አባ ነጋን ይዘው ወደ መሀል አገር በመምጣት በነፃ የለቀቋትን ወይንም ያስረከቧትን አገር ምኒልክ በምን አቅማቸው ነበር ያነዬ ሊያስመልሷት የሚችሉት? ለማንኛውም ይህንን በተመለከተ ኋላ ላይ የሳቸውን ታሪክ በምንተርክበት ወቅት የምናየው ይሆናል። አሁን ወደ ጎጃም እንመለስ።

ከፍ ብዬ ለመግልጽ እንደሞከርኩት ንጉሠ ነገሥቱ ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ባሰቡት መልኩ ድል አድርገው ሊማርኳቸው እንደማይችሉ ባወቁ ጊዜ ወደ ሸዋ ተሸግረው ሌላ ጥፋት ለማጥፋት ባሰቡበት ምሽት ዘውዲቱ ምኒልክ ያባታቸው እጣ ፈንታ ስላሳሰባቸው፡-

"ባለቤቴ ራስ አርአያ ቢኖሩ ኖሮ ጃንሆይና አባቴ ለጦርነት አይሰላለፉም ነበር" ብለው በመናገራቸው ይኸው ላፄ ዮሐንስ ሲነገራቸው የልጃቸው ሀዘን ገና ካንጀታቸው አልወጣም ነበርና ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ይባላል። ያች ምሽትም የሐዘን ምሽት ሆና ማምሸቷ ይተረካል።

ከዚህ በኋላ አፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ የመዝመታቸውን ጉዳይ ጠብ ርግፍ አድርገው በሙተው ዘውዲቱ ምኒልክን ደረጃዋን በጠበቀች በቅሎ፣ በመኳንንት አሣጅበው፣ ከንጉሥ ምኒልክ ጋርም እንዲያስታርቋቸው ለራስ ዳርጌ ደብዳቤ ጽፈው ወደ ሸዋ ላኳቸው።

አፄ ዮሐንስ ሠራዊታቸው በጎጃም ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ጥፋት ለራስ ዳርጌ በጻፉት ደብዳቤ በፀፀት መልክ እንዲህ ነበር ያሉት፡-

*". . .በኔም፣ በድሃውም (በሕዝቡ) ኃጢዓት እንደሆነ አይታወቅም አገሩን (ጎጃምን) ሣጠፋው ከራመሁ . . ."* (ተክለፃድቅ መኩሪያ ገጽ 442)

የሆነ ሆኖ በዘውዲቱ ምኒልክ አነጋገር ምክንያት ወደ ሸዋ ሊያደርጉት የነበረውን ጉዞ ሠርዘው ፊታቸውን ወደ መተማ ማዞራቸውን እናስተውላለን።

አንዳንድ አዛውንቶች ግን ሐሳባቸውን የቀየሩት "በዘውዲቱ ንግግር ሣይሆን በጳጳሱ ባቡነ ሉቃስ ውግዘት ሕሊናቸው ተነክቶ ነው" ይላሉ። ሌሎች ደግሞ "ንጉሠ ነገሥቱ ፊታቸውን ወደ መተማ ያዞሩት በዘውዲቱ

ንግግርም፣ ባቡኑ ውግዘቶም አይደሉም:: ንጉሥ ምኒልከ ያፄ ዮሐንስን ሃይማኖተኛነት ያውቁ ስለነበር ባሕታውያንን ወደ ጎጃም በመላከ "*. . .‹ወደ ሸዋ የሄደህ እንደሆነ ንጉሥ ምኒልከን ድል ታደርጋለህ፤ በነፍስህ ግን ትጎዳለህ:: ወደ መተማ የሔደህ እንደሆነ ግን በሰማዕትነት ትሞታለህ በነፍስህም ትጠቀማለህ› ሲሏቸው ‹በሥጋየ ተጠቅሜ በነፍሴ ከምጎዳ ሞት ይሻለኛል› ብለው ወደ መተማ ሔዱ. . .*" ሲሉ ይተርካሉ:: (*ተክለፃዲቅ መኩሪያ ገጽ 536*) ወደ መተማ ለመዝመት ጉዞ በጀመሩ ጊዜ ሕዝቡ:-

*"ዘንድሮ ንጉሡ በድል ቢመለሱ*
*አውነትም ጎጃሜ ጎልደፏል ምላሱ!"* ብሏቸዋል::

ከስንኞቹ የምንረዳው ቁምነገር በሀምሌው ምድር ያሰቃዩት ሕዝብ ደጀን ሊሆናቸው ሲገባ ረግሞና አውግዞ የሸኛቸው መሆኑን ነው::

አፄ ዮሐንስ መተማ እንደ ወረዱ በቀጥታ ተጣድፈው ወደ ጦርነት አልገቡም ነበር ይባላል:: የኃይላቸውን መሣሣት፣ የባሕር-ነጋሽን በጣሊኖች እጅ መውደቅ አውቀው ስለነበር በርቅ ለመጨረስ ብዙ ሙከራዎችን አድርገው ነበር:: ዳሩ ግን የድርቡሾቹ መሪ በንቀትና በማንጓጠጥ "ርቅ ልናደርግ የምንችለው በመጀመሪያ ሃይማኖተዎትን ቀይረው እስልምናን ሲቀበሉ ብቻ ነው" ሲላቸው እንደ አፄ ዮሐንስ ላለ ለሃይማኖቱ ቀናዒ ንጉሥ ምን ያህል ሊጎመዝዛቸው እንደሚችል መገመቱ አይከብድም:: በዚህ እልህና ብስጭት ሣይሆን አይቀርም በመሪነታቸው ከርቀት ሆነው ማዋጋት ሲችሉና ሲገባቸው እንደ አንድ ወታደር ከመሀል ገብተው በጀግንነትና በኩራት ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል:: ሕዝቡ ግን እንደ አንድ ወታደር መሀል ገብተው መዋጋታቸውን በመንቀፍ በጊዜው የሚከተለውን ብሏቸዋል:-

*"አፄ ዮሐንስ ምኝ ናቸው*
*እኛም ሁላችን ናቅናቸው*
*ንጉሥ ቢሏቸው በመሀሉ*
*ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ!"*

ያም ሆነ ይህ አፄ ዮሐንስ ስህተቶቻቸውን ሁሉ መተማ ወርደው ላገራቸው ዳርድንበር አንገታቸውን በመስጠት በደማቸው አጥበዋቸው አልፈዋል:: ያ ጊዜም የራሱን ጊዜ ሆኖ አልፏል:: በተረፈ ግን ለኤርትራ መገንጠልም ሆነ እስካሁን ከፍለን ላልጨረስናቸው እዳዎች የተጋለጥነው <"የሔዊት ስምምነት ምክንያት ነው> ስንል ከባዶ ተነስተን አይደለም:: ቢያንስ ካሥር ያላነሱ መሠረታዊ ነጥቦችን ይዘን ነው::





1ኛ. አፄ ዮሐንስ ከሪር አድሚራል ሔዊት ጋር ጥቅም በማያገኙበት ጉዳይ ባይፈርሙ ኖሮ እንግሊዝ ጣሊያንን አምጥታ ምፅዋ ላይ ባላሠፈረች ነበር::

2ኛ. ጣሊያን ምፅዋ ወደብ ባትቀመጥ ኖሮ ዶጋሊ ላይ ጦርነት ባልከፈተች ነበር:: በመከፈቷ ግን ድባቅ ተመታ በውጤቱ ለራስ አሉላ መሻር ምክንያት ሆና በሩ ተከፈተላት::

3ኛ. በማይመለከታቸውና በማያገባቸው ጉዳይ ገብተው መሃዲስቶች ለነፃነታቸው ሲሉ የከበቧቸውን የቅኝ ገዥ ወታደሮች ተዋግተው በማስለቀቃቸው ለጎንደር አድብራት መቃጠልና መዘረፍ ምክንያት ባልሆኑ ነበር::

4ኛ. የጎንደር አድባራት መቃጠልና መዘረፍ ለንጉሥ ተክለሃይማኖት አማች መገደልና ለሴት ልጃቸው መማረክም ሆነ ጠቅላላ ሽንፈት ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ለመቃቃርም ሆነ ለጭራሹ መለያየት ምክንያት ሆነ::

5ኛ. የሔዊት ስምምነት ሌላው ውጤት ለጎጃም ሕዝብ በንጉሡ ነገሥቱ ሠራዊት መመዝበሩና የደጀኑን ሕዝብ ድጋፍ ያጡበትና ርቃናቸውን የቀሩበት መሆኑ ነበር::

6ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ የሣቸውን እግር ጠብቀው ጣሊያኖቹ በደጃዝማች ደበበ አርአያ መሪነት አሥመራ ገብተው ከመረብ ምላሽ ያለውን አገር <ኤትር> ብለው በመሰየም ቅኝ ግዛት አድርገው መያዝ ባልቻሉ ነበር:: ያድዋ ጦርነት መከተልም የሥምምነቱ ውጤት ነበር::

7ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ የድርቡሾቹ መሪ ለሰላም እጆቻቸውን ሲዘረጉለት በበቀል ተነሳስቶ <በመጀመሪያ ሲሰልሙ ነው ድርድር ማድረግ የምንችለው> ብሎ ባይልከባቸው ኖሮ ምናልባትም በእልህና በብስጭት እንደ አንድ ተራ ተዋጊ ወታደር ከመሀል ገብተው በጥይት ተመተው መውደቅ ባልቻሉ ነበር::

8ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ ባምስት አመቱ ያርበኝነት ወቅት ኢጣሊያ ወጥታ በነፃ አውጭ ስም እንግሊዝ ገብታ አሥር ዓመት በመቆየት ሌላ መርዝ ዘርታ ባልወጣች ነበር::

9ኛ. የሔዊትን ስምምነት ባይፈርሙ ኖሮ ሻዕቢያና ጀብሐ የሚባሉ ተገንጣይ ቡድኖች ሊፈጠሩ ባልቻሉ ነበር::

፲ኛ. ሻዕቢያ የተባለ ድርጅት ባይፈጠር ኖሮ የመገንጠል ጥያቄ አይኖርም ነበር። የመገንጠል ጥያቄ ካልኖረም ሕወሓት የሚባል የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት አይፈጠርም ነበር። የዚህ ድርጅት መፈጠር ግን የሔዊት ስምምነት የመጨረሻ ውጤት ነው ባይባልም ለጊዜው ኤርትራን አሥገንጥሎ የባሕር በር በላያችን ላይ አዘግቶብናል። ለዚህም ነው ገና ከፍለን ያልጨረስናቸው እዳዎች እንዳሉብን ለመጠቆም የሞከርኩት።

<><><>





# ዳግማዊ አፄ ምኒልክ



*ዳግማዊ አፄ ምኒልክ*

አፄ ምኒልክ ወደ ሥልጣን በወጡበት ወቅት ባገር ውስጥ ካፄ ቴዎድሮስና ካፄ ዮሐንስ ጋር ሲነፃፀር ሰላም ነበር ማለት ይቻላል። ይህ ማለት ግን ግዛትን ለማስፋፋት ሲሉ በምሥራቅ፣ በደቡብና በምእራብ ኢትዮጵያ የሰበሰ ፍልሚያ አላካሄዱም ማለት አይደለም። ኃይለኛ የሥልጣን ተፎካካሪ አልገጠማቸውም ለማለት እንጅ።

ባገር ውስጥ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል በውጭ ያለው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ሁሉም ነገር ተጠናቋል ማለት ይቻላል። ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን ከኢትዮጵያና ከላይቤሪያ በስተቀር ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገዋቸዋል። የኢትዮጵያ አጎራባች አገራት ሱዳን፣ ኬንያና ኡጋንዳ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ሲወሉ ከፊል ሶማሊያ በእንግሊዝ ይዞታ ስር ቀሪው ደግሞ በኢጣሊያን ተይዟል። ጅቡቲ በፈረንሳይ